አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3541 | ቅዳሜ መስከረም 24 ቀን 2018 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር




# "የሀገራችንን ማንሠራራት ለማረጋገጥ በፈተናዎች ሳንበገር ተግተን እንስራ"

**ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)**

3



ፎቶ- ከገፀ ድር

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓልን አስመልክቶ የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት ሲያስተላልፉ

## የኢትዮጵያን ከፍታ ማሳያዎች

4




ፎቶ- ከገፀ ድር

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የኦጋዴን ፈሳሽ የተፈጥሮ ጋዝ ፕሮጀክት የመጀመሪያ ዙር ባስመረቁበት ወቅት

## "ዜጎች ላይ ምሬት የሚፈጥሩ አሰራሮችን ማስተካከል ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው"

20



ፎቶ በገነት ወንድሙ

የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አቶ ዮናስ አለማየሁ

## ለኪነ ጥበባዊ ፈጠራ ዕድል የሚሰጠው በዓል

30



ፎቶ ከፋይል

የኢሬቻን እሴቶች በመጠቀም ከተሳሉ ስዕሎች ጥቂቶቹ



ፎቶ- ከገፀ ድር

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓልን አስመልክቶ የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት ባስተላለፉበት ወቅት

# የኢሬቻ በዓል

## "የሀገራችንን መልከ-ብዝሃነት እና ጥልቅ ውበት ለመላው ዓለም ካስተዋወቁ በዓላት መካከል አንዱ ነው"

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ**

**በሳህሉ ብርሃኑ**

የኢሬቻ በዓል የሀገራችንን መልከ-ብዝሃነት እና ጥልቅ ውበት ለመላው ዓለም ካሳዩ እና ካስተዋወቁ በዓላት መካከል አንዱ ስለመሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ተናገሩ፡፡

ለ2018 የኢሬቻ በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት ያስተላለፉ ከንቲባ አዳነች እንዳሉት በዩኔስኮ የተመዘገበው የኦሮሞ ገዳ ሥርዓት አካል የሆነው የኢሬቻ በዓል የሀገራችንን መልከ ብዝሃነት እና ጥልቅ ውበት ለመላው ዓለም ካሳዩ እና ካስተዋወቁ በዓላት መካከል አንዱ ነው፡፡

ኢሬቻ በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ ለፈጣሪ ምስጋና የሚቀርብበት፤ ከሰው ጋር ሰላም፣ ፍቅር እና አብሮነት የሚከናወንበት፤ አዲስ ተስፋና ብሩህ ዘመን የሚበሰርበት በዓል መሆኑንም ከንቲባ አዳነች አቤቤ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

# የመሻገር ጉዞ ተምሳሌትነት

- የበዓሉ እሴቶች ኢትዮጵያ ወደ ልማት፣ ዘላቂ ሰላምና ብልፅግና ለመሸጋገር ለምታደርገው ጥረት ተምሳሌት መሆን እንደሚችል ተጠቁሟል

**በስንታየሁ ምትኩ**

የኦሮሞ ህዝብ ዕለታዊ ህይወቱን፣ በሰው ልጅ መካከል፣ በሰውና አካባቢው፣ በፍጥረታትና ፈጣሪ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚመራበት ፍልስፍና አለው። ይህም በገዳ የአስተዳደር ስርዓት የሚገለፅ ሲሆን ለዘመናትም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን ሲመራበት እንደኖረ የታሪክ ማስረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

ዛሬና ነገ የገዳ ስርዓት አንድ አካል የሆነው

ወደ ገጽ 19 ዞሯል



# ርዕሰ አንቀፅ



## የአደባባይ በዓላት የአንድነታችን መስታወቶች ናቸው!

ኢትዮጵያውያን ብዝሃ ማንነታችንን በአንድነት አጠናክረን ፈተናዎችን የተሻገርን፣ በጋራ ክንዳችን ድሎችን ያስመዘገብን ህዝቦች ነን፡፡ ከጥንትም ጀምሮ አያቶቻችን በተባበሩባቸው ጉዳዮች ሁሉ ድሎችን ተጎናፅፈዋል፡፡ ለአብነትም ያለ አግባብ ሊወርሩን የመጡትን የውጭ ተስፋፊ ኃይሎች በጉንደት እና ጉራ በተባበረ ክንዳቸው አሳፍረው መልሰዋል፡፡ ይህንኑ ድል አድራጊነት በዓድዋ እና ካራማራ አውደ ውጊያዎች ደግመውታል፡፡ በቅርብ ጊዜ ታሪካችንም ለመላው የአፍሪካ ሀገራት ተምሳሌት የሚሆነውን ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በራሳችን ገንዘብ፣ ጉልበትና እውቀት አሳክተናል፡፡ ይህም በመተባበራችን እና ለጋራ ዓላማ በጋራ በመሰለፋችን ያገኘው ውጤት ነው፡፡ ድሎቹ አስተሳሳሪዎቻችን ሆነውም ዘመናትን ይሻገራሉ፡፡

ብዝሃ ማንነታችን የገነቧቸው የአደባባይ በዓላት ደግሞ በጋራ የምናከብራቸውና እርስ በርስ ያስተሳሰሩን አንድነታችን የሚገለጥባቸው መስታወቶቻችን ናቸው፡፡ የመስቀል ደመራ፣ ኢሬቻ ጥምቀት፣ ሻደይ፣ አሸንድዬ፣ ሶለል፣ ጎቤ፣ ሽኖዬ፣ ፊቼ ጨምበላላ እና ዮዮ ጊፋታ ከእነዚህ እሴቶቻችን መካከል ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ዛሬ በሆራ ፊንፊኔ፣ ነገ ደግሞ በሆራ አርሰዴ በድምቀት የሚከበረው የኢሬቻ በዓል አንዱ የእርስ በእርስ በተሳሰሪያ ገመዳችን ነው፡፡ የኢሬቻ በዓል ሁለት ጊዜ ይከበራል፤ እነዚህም የክረምት ወራት እንዳበቃ የሚከበረው ኢሬቻ መልካ እና በዓመቱ አጋማሽ ላይ የሚከበረው ኢሬቻ ቱሉ ናቸው።

ኢሬቻ ቱሉ በበጋ ዝናብ ወቅቱን ጠብቆ እንዲዘንብ የኦሮሞ ሕዝብ ወደ ተራራ ወጥቶ ፈጣሪውን የሚለምንበት ነው። "ይህን ተራራ የፈጠርክ ፈጣሪ ወቅቱን የሰላም አድርግልን፣ የሰላም ዝናብ አዝንብልን፣ ጎርፍን ያዝልን፣ የተዘራው ፍሬ እንዲያፈራ እንለምንሃለን" እያለ ፈጣሪን የሚማፀንበት ነው፡፡

ኢሬቻ መልካ ደግሞ "ከክረምቱ አስፈሪ ነጎድጓድ እንኳን ወደ ብርሃን አወጣኸን። ብራውን ሰላም አድርግልን" በማለት በሐይቆችና ጅረቶች ዙሪያ ምስጋናን በማድረስ የሚከበር ነው። ኢሬቻ የመስማማትና የአንድነት በዓል ነው። ይህ በዓል ከኦሮሞ ህዝብ ባሻገር ከመላው የኢትዮጵያ ክፍሎች የመጡ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች የሚሳተፉበት የሰላም እና የአብሮነት ተምሳሌት የሆነ የምስጋናና የፍቅር በዓል ነው፡፡

የምስጋና በዓል የሆነው ኢሬቻ በህዝቦች መካከል መቀራረብን፣ ፍቅርንና እርቅን ለማምጣት የሚያግዝ እሴት ነው። በዓሉ ከልጅ እስከ አዋቂ፣ ሴት ወንድ ሳይባል ያለ ልዩነት በድምቀት የሚከበር ነው።

ታድያ ኢሬቻን ጨምሮ ሌሎች የአደባባይ በዓሎቻችን የአንድነታችን መስታወቶች በመሆናቸው ጠንካራ ማህበራዊ ትስስርና መስተጋብርን በመካከላችን ያሰፍናሉ፡፡ ከዚህ ባሻገርም ቀላል ግምት የማይሰጥ ኢኮኖሚያዊ በረከትን ያጎናፅፉናልና ይህን ጉልህ ፋይዳቸውን በመገንዘብ መንከባከብና እሴቱን ጠብቆ ለቀጣይ ትውልድ እንዲተላለፍ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

# የእኔ እይታ

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።

## በበቂ ደረጃ ያልተሸጡት የአደባባይ በዓሎቻችን

**ወርቅነህ ዓለማየሁ**

ቱሪዝም በሀገራችን ገና ተቆፍሮ እንዳልወጣ መዓድን ነው ብል ያጋነንኩ መስሎ አይታየኝም። ይህንን ስል ግን ጭላንጭሉ የለም ማለቴ አይደለም። እንዲያውም በቅርቡ የተከናወኑ ሀገራዊ ፕሮጀክቶች ዘርፉን እንዳነቃቁት አምናለሁ፡፡ በተለይ በገበታ ለሀገር፣ ገበታ ለሸገር እና ገበታ ለትውልድ የተከናወኑ የልማት ስራዎች እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ እየተከናወኑ የሚገኙት የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማቶች አበረታች ውጤቶችን እያስገኙ ነው ማለት እችላለሁ፡፡

በቅርቡ የኢፌዴሪ የቱሪዝም ሚኒስቴር ይፋ ያደረገው ሪፖርትም ይህን አቋም ይደግፍልኛል፤ በሪፖርቱ መሠረት ከ2023 እስከ 2024 ባለው ጊዜ ብቻ ሀገራችን ከ1 ሚሊዮን 148 ሺህ በላይ የውጭ ቱሪስቶችን በማስተናገድ ወደ ኢኮኖሚዋ ፈሰስ የሆነ 4 ነጥብ 3 ቢሊዮን ዶላር አግኝታለች፤ ካለን እምቅ ሀብት ጋር ሲነፃፀር ብዙ ርቀት መጓዝ የሚጠበቅብን ቢሆንም ጅምሩ ግን የሚናቅ አይደለም፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ የአደባባይ በዓላትን መነሻ ባደረገ ቱሪዝም ቀላል የማይባል ገንዘብ ይንቀሳቀሳል፤ እ.ኤ.አ በ2023 ብቻ 1 ነጥብ 665 ትሪሊዮን ዶላር እንደተንቀሳቀሰ መረጃዎች ያመላክታሉ። ይህ የገንዘብ ፍሰት እስከ 2030 ድረስ ወደ 2 ነጥብ 2 ትሪሊዮን ዶላር ያድጋል ተብሎ ይጠበቃል። ታድያ በዩኔስኮ የማይዳሰስ የባህል ቅርስ መዝገብ ላይ በርካታ የአደባባይ በዓላትን ያስመዘገበችው ኢትዮጵያ ከዚህ ሀብት ምን ያህል ተጠቅማለች የሚለው ነጥብ ሲነሳ በብዙ ያነጋግራል፡፡

ቀድመው የነቁ እና የቱሪዝሙን ዘርፍ ያሳደጉ ሀገራት በአደባባይ በዓላት ብቻ ከፍተኛ ገቢን ወደ ካዝናቸው ያስገባሉ። ምሳሌ ጠቅሰን ብናይ እንኳን ከዓለም አቀፍ የቱሪዝም ገቢ ከፍተኛውን ድርሻ ከያዙት ሀገራት መካከል ዩናይትድ ስቴትስ በየዓመቱ ከዘርፉ በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር ታገኛለች። ትልልቅ የባህል፣ የስፖርት እና የሙዚቃ ፌስቲቫሎች በማሰናዳት በመቶ ቢሊዮን የሚቆጠር ዶላሮችን ገቢ ታደርጋለች።

ፈረንሳይም ከፍተኛ ጎብኚ የምትቀበል ሀገር ስትሆን ከቱሪዝም በዓመት በመቶ ቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ዶላሮችን ታገኛለች። ብራዚልም ከዘርፉ የሚገኘው ጥቅም ከፍተኛ ተጋሪ ናት፤ በብራዚል የሚካሄደው የሪዮ ካርኒቫል (Rio Carnival) በዓለም ትልቁ ካርኒቫል ሲሆን፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን ይስባል። በዚህ ፌስቲቫል ሆቴሎች እንኳን ከመጨናነቃቸው የተነሳ እስከ 200 በመቶ የዋጋ ጭማሪ እንደሚያደርጉ መረጃዎች ያመላክታሉ።

የአደባባይ በዓላት ባለፀጋዋ ኢትዮጵያ እንደ መስቀል ደመራ፣ ጥምቀት፣ ኢሬቻ፣ ፊቼ ጫምባላላ፣ ዮዮ ጊፋታ፣ አሸንዳ፣ ሶለል፣ ጎቤ እና ሽኖዬን የመሳሰሉ እሴቶች እያሏት በበቂ ደረጃ ሳትጠቀም መቅረቷ ያስቆጫል።

አዲስ አበባን እንደ ስሟ አበባ አስመስለን አስጊጠን ለእንግዶች ምቹ አድርገናታል፤ እንደ ላል ይበላ አብያተ ክርስቲያናት፣ አክሱም ሐውልት፣ ጥያ ትክል ድንጋይ፣ ሆልቀ ሶፍ ኡመርን፣ ዳሎልን የመሳሰሉ ነባር የቱሪዝም መስህቦችን በማደስ እና በመሠረተ ልማት ከማልማት ባሻገር ጨበራ ጩርጩራን፣ ጎርጎራ ኢኮ ቱሪዝምን፣ ደንዲ ወንጪ ኢኮ ቱሪዝምን፣ ቤኑና መንደርን የመሳሰሉ አዳዲስ ሀብቶች ተዘጋጅተው ለአገልግሎት በቅተዋል፡፡ እነዚህ ጥረቶች የቱሪዝሙን ዘርፍ እንዳነቃቁት ይሰማኛል፤ ነገር ግን የአደባባይ በዓላትን በበቂ ደረጃ አስተዋውቆ ወደ ጥቅም ከማስገባት አንፃር ያለው ክፍተት መታረም እንዳለበት ይሰማኛል፡፡

ስለዚህ የሚመለከታቸው አካላት በሙሉ ተባብረው በዚህ ረገድ ያሉብንን ክፍተቶች መድፈን ይኖርብናል፡፡ የአደባባይ በዓሎቻችንን በዓለም አቀፍ መድረኮች በበቂ ደረጃ አስተዋውቀን ያለንን እምቅ ሀብት ወደ ገንዘብ መቀየር አለብን እላለሁ፡፡

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እየተዘጋጀች

ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን
የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ

ግንቦት 1985 ዓ.ም
ተመሰረተች

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት
በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜልባ ፕሪንቲንግ ፐብሊሺንግ ኤንድ ፓኬጂንግ ሼር ካምፓኒ

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ለይላ መሀመድ
አብርሃም ገብሬ
ፋንታነሽ ተፈራ
ሄለን ጥላሁን

**ዋና አዘጋጅ**
ምህረቱ ፈቃደ
Mehretu@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 34/55

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

# “የሀገራችንን ማንሠራራት ለማረጋገጥ በፈተናዎች ሳንበገር ተግተን እንስራ”

**ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር)**

**በሳህሉ ብርሃኑ**

የአገራችንን ማንሠራራት ለማረጋገጥ በፈተናዎች ሳንበገር ተግተን እንስራ ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጠየቁ

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ይህን ያሉት ለ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት ባስተላለፉበት መልዕክታቸው ሲሆን፣ የኢሬቻ እሴቶች የሆኑትን ሰላም፣ ምህረትና አንድነትን አጥብቀን በመያዝ የሀገራችንን ማንሠራራት ለማረጋገጥ በፈተናዎች ሳንበገር ተግተን እንድንሠራ አደራ ለማለት እወዳለሁ ብለዋል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓልን አስመልክቶ የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት ሲያስተላልፉ

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመልዕክታቸው፣ ኢሬቻ የኦሮሞ የምስጋና ስርዓት መሆኑን ገልፀው፣ ኦሮሞ የሰው ዘር አፍርቶ የሚባዛው የተዘራው ሞቶ በመነሣት ፍሬ የሚያፈራው በፈጣሪ ድጋፍና እርዳታ ነው ብሎ ያምናል ብለዋል፡፡

ለዚህ ነው ኢሬቻ ሲደርስ ኦሮሞ ልበ ንፁህ የሆነውን ታላቅ ፈጣሪ ላደረገለት ሁሉ በማመስገን ለሚመጣው ጊዜ ደግሞ ምህረትን በመለመን ውዳሴ የሚያቀርበውም ብለዋል በመልዕክታቸው፡፡

አክለውም፣ በጥንት የኦሮሞ ፍልስፍና ውስጥ ኦሮሞ ለውሃ ትልቅ ስፍራ አለው። ውሃ የንጽህና ምንጭ፣ የፍጥረትና የህይወት መሠረት ነው ብሎ ያምናል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፣ ለዚህም ነው ሲፀልይ ፈጣሪ አምላክ፣ የፍጥረታት አምላክ፣ የቡርቃ ወላቡ (የወላቡ ምንጭ) አምላክ ብሎ ነው የሚፀልየው በማለት አብራርተዋል፡፡

የዘንድሮው ኢሬቻ ኢትዮጵያ የዜጎቿን የኢነርጂ ፍላጎት ለማሟላት የዓባይን ወንዝ በመገደብ ታላቁን የህዳሴ ግድብ ባስመረቀችበት ማግስት የሚከበር መሆኑ ደስታችንን ድርብ ያደርገዋል ሲሉም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) አስረድተዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) አያይዘውም፣ ኦሮሞ መልካ የሌለው ህዝብ ራስ እንደሌለው ህዝብ ነው እንደሚል የባህር በር የሌላት ሀገር ኑሮ የሌላት ሀገር ናት ብለን ለህዝባችን ብልጽግና ስንል በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ የባህር በር ለማግኘት እየሠራን እንገኛለን ብለዋል፡፡

አክለውም፣ በዚህ ረገድ እያደረግን ያለነው እንቅስቃሴ በዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት በማግኘት ላይ ነው፡፡ ባለፉት ዓመታት አዲስ እሳቤ በሆነው የመደመር ፍልስፍና በመመራት ሀገር ያላትን ሀብት፣ ልምድና እውቀት ከህዝባችን ጋር በመሆን ቁርጠኛና በሳል አመራር በመስጠት፣ ፈጣሪም አግዞን በበርካታ ችግሮች ውስጥ ሆነን አስደናቂ ለውጦችን አስመዝግበናል ሲሉም በመልዕክታቸው አመላክተዋል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓልን አስመልክቶ የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት ባስተላለፉበት ወቅት

## የኢሬቻ ... ከገጽ 1 የዞረ

መልዕክት ገልፀዋል፡፡

የኦሮሞ ህዝብ ከሌሎች ወንድም እህት ህዝቦች ጋር በመሆን ባካሄደው መራር ትግል ከተቀዳጃቸው ድሎች መካከል አንዱ የኢሬቻ ሆረ ፊንፊኔን ክብረ በዓል በጥንታዊ ስፍራው ማክበር መቻል መሆኑንም ገልፀው፣ ይህም ባለፉት 7 ዓመታት በከፍተኛ ድምቀት ባህላዊ እሴቱን እና ቱፊቱን ጠብቆ በመዲናችን አዲስ አበባ እየተከበረ ይገኛል ብለዋል፡፡

በዓሉን የመዲናዋ አጠቃላይ ህዝብም ከወንድም እህቱ የኦሮሞ ህዝብ ጋር በአብሮነት የሚያከብረው ታላቅ በዓል ስለመሆኑ ያወሱት ከንቲባዋ ሌሎች የአደባባይ በዓላት ሲከበሩ ለበዓላቱ ድምቀት እና ባማረ መልኩ መጠናቀቅ እንደሚያደርገው ሁሉ አብሮነትን፣ ወንድማማችነትን፣ እህትማማችነትን በሚያጸና መልኩ በከተማዋ ውስጥ ከሚኖሩ የኦሮሞ ሕዝቦችም ሆነ በእንግድነት ከሚመጡት ወገኖቹ ጋር በመሆን በዓሉ እሴቱን ጠብቆ እንዲከበር ስለመደረጉ ገልፀዋል፡፡

እንደዚሁም በመንገድ ጽዳት፣ በአደባባይ ማስዋብ እና በሌሎችም በርካታ በጎ ፈቃድ ስራዎች ከምንጊዜውም በላቀ መልኩ ለሀገር ገጽታ ግንባታ፣ ለዘላቂ ቱሪዝም መስህብነት፣ ለከፍተኛ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በሚያመች መልኩ በሕብረ ብሔራዊ አንድነት መንፈስ ዝግጅት ስለመደረጉም አስረድተዋል።

በከተማዋ የአደባባይ በዓላት ሲከበሩ ለመላው የከተማዋ ነዋሪ በዓላቱ ከዋዜማው አንስቶ እስኪጠናቀቁ ድረስ በተለያዩ የበጎ ፈቃድ ተግባራት በመሳተፍ እያበረከተ ላለው እጅግ የላቀ ሚና ምስጋና ያቀረቡት ከንቲባ አዳነች አቤቤ፣ ይህ ተግባር ውብ እና ድንቅ ባህሎቻችን ከእኛ አልፈው ለመላው ዓለም የምናበረክታቸው፣ የእኛነታችን መለያ ጌጥ ስለመሆናቸው ተናግረዋል፡፡

አያይዘውም እንደወትሮው ሁሉ የዘንድሮውን የኢሬቻ በዓል ባህላዊ እሴቱን ጠብቆ ባማረ መልኩ ለማክበር የተደረገውን ቅድመ ዝግጅት ከዋዜማው ጀምሮ በጋራ በሚከናወኑ ተግባራት የከተማዋን የሰላም ተምሳሌትነት፣ የህዝባችንን የሰላም ዘብነት እና እንግዳ ተቀባይነት በማረጋገጥ ይሆናል ብለዋል በማጠቃለያ መልዕክታቸው።

# የኢትዮጵያን ከፍታ ማሳያዎች

**"ህልማችን ሩቅ ነው፤ ተስፋችን የሚጨበጥ ነው"**

**ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)**

**በመለሰ ተሰጋ**

የተመጣጠነ ልማት እኩልነትን ያፀናል፣ ሀገራዊ አንድነትን ያሳድጋል፣ ዕድገቱ ዘላቂና ሁሉን አቀፍ እንዲሆን ያደርጋል። ሀገራት በሁለንተናዊ መልኩ ጠንካራ ሆነው መቀጠል የሚችሉት ያላቸውን ሀብት በሚገባ ሲጠቀሙና ሁሉን አቀፍ የሆነ የኢኮኖሚ መንገድን መጠቀም ሲችሉ መሆኑን ከሃያ በላይ የፖለቲካል ኢኮኖሚ እና የፖለቲካል ርዕዮተ ዓለም የምርምር መፅሐፍትን ያሳተሙት ጀርመናዊው ኢኮኖሚስት አልበርት ኦቶ ሂርሽማን እ.ኤ.አ በ1958 "The Strategy of Economic Development" በሚል ርዕስ ባሳተሙት መፅሐፍ ላይ አስፍረውታል፡፡

በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት ትምህርት ክፍል ተባባሪ ፕሮፌሰር ይንገስ አለሙ (ዶ/ር) እንደሚሉትም ያደጉ ሀገራት የተከተሉት አዋጭ መንገድ ወደ ራስ መመልከትን፣ ያላቸውን ሀብት በሚገባ ማወቅን እና ከፍ ላለ ሀገራዊ ዕድገት መጠቀምን ነው፡፡ በዚህም አሜሪካ፣ ቻይና፣ ብራዚል፣ ጀርመን እና ሌሎቹም ሀገራት በኢኮኖሚ ከፍ ማለት ችለዋል፡፡ ኢኮኖሚ ደግሞ ሌሎቹንም መስኮች በበላይነት የመምራት ትልቅ አቅምን ይሰጣል፡፡

በመሆኑም ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ ሁሉንም የኢትዮጵያ አካባቢዎች ያካለለ፣ ያለንን ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ሀብት ያገናዘበ፣ ሀገርን በኢኮኖሚም ሆነ በሌሎች ዘርፎች ማላቅ የሚያስችሉ ስራዎች እየተከናወኑ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ባሳለፍነው ረቡዕ መስከረም 21 ቀን 2018 ዓ.ም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ተገኝተው በዓመት 111 ሚሊዮን ሊትር ማምረት የሚችለውን የኦጋዴን ፈሳሽ የተፈጥሮ ጋዝ ፕሮጀክት የመጀመሪያ ዙር ማስመረቃቸውን፣ የታላቁ ህዳሴ ግድብ መጠናቀቅን፣ አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ የሀገሪቱ ከተሞች እየተከናወኑ ያሉ ልማቶችን፣ ከመደበኛው መንገድ ባሻገር በበጋ መስኖ እየተመረተ ያለውን ስንዴ እና በሌሎች መስኮችም እየመጡ ያሉ ለውጦችን በዋቢነት በመጥቀስ ኢትዮጵያ በርግጥም ወደ ከፍታዋ ምዕራፍ እየተሻገረች ስለመሆኑም ተናግረዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) በሶማሌ ክልል የኦጋዴን ፈሳሽ የተፈጥሮ ጋዝ ፕሮጀክት የመጀመሪያ ዙር ምርቃት፣ ሁለተኛ ዙር ማስጀመሪያ እንዲሁም የዩሪያ የአፈር ማዳበሪያ ፋብሪካ የመሰረተ ድንጋይ ማስቀመጣቸውን አስመልክቶ ባስተላለፉት መልእክትም፣ "ዛሬ ለኢትዮጵያዊያን ሁሉ የሚያኮራ ታሪካዊ ሁነት ተፈፅሟል፤ የሁለት አሻጋሪ ፕሮጀክቶች የመሠረት ድንጋይ አስቀምጠናል" ብለዋል፡፡

አክለውም፣ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ከዳንጎቴ ግሩፕ ጋር በመተባበር የሚገነባው የዩሪያ ማዳበሪያ ፋብሪካና በጎልደን ኮንኮርድ ግሩፕ የሚገነባው የጎዴ ነዳጅ ማጣሪያ ፋብሪካ የመሠረት ድንጋይ መቀመጡን ተናግረዋል፡፡

የኦጋዴን ፈሳሽ የተፈጥሮ ጋዝ ፕሮጀክት፣ የተመረቀው የመጀመሪያ ዙር በዓመት 111 ሚሊዮን ሊትር ማምረት የሚችል፣ የተጀመረው ሁለተኛ ዙር በዓመት 1 ነጥብ 33 ቢሊዮን ሊትር የማምረት አቅም ያለው ሲሆን፣ በሌላ በኩልም 1 ሺህ ሜጋ ዋት ኃይል የማመንጨት አቅም ያለው መሆኑን የጠቅላይ ሚኒስትር ፅሕፈት ቤት በይፋዊ ገፀ ድሩ ባሰፈረው መረጃ ተመላክቷል፡፡

የጎዴ ነዳጅ ማጣሪያ ከሂላል የነዳጅ ስፍራ ድፍድፍ ነዳጅ በማውጣት፣ በማጣራትና በማጠራቀም በዓመት 3 ነጥብ 5 ሚሊየን ቶን የማምረት አቅም እንዳለውም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ጠቅሰዋል፡፡ በሌላ በኩል የማዳበሪያ ፋብሪካው ከካሉብ የጋዝ ስፍራ በማውጣት እና 108 ኪሎ ሜትር የማጓጓዣ ቱቦ በመጠቀም በዓመት 3 ሚሊዮን ቶን አምርቶ እንደሚያቀርብም ገልፀዋል፡፡

እነዚህ ፕሮጀክቶች የኢንዱስትሪ እድገትን ከማሳየት በላይ ናቸው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ እድሎቻችንን የመጠቀም፣ ትብብሮችን የማጠናከርና ሰላምን የማጽናት የጋራ ኃላፊነታችንን የሚያሳዩ መሆናቸውም ገልፀዋል።

ኢትዮጵያዊያን ሁሉ በህብረት እና በአንድነት ለእድገት መሰባሰባቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጥሪ ያቀረቡት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ይህን ስናደርግም እውነተኛውን የኢትዮጵያዊ ማንነት መንፈስ በሚያከብር መንገድ በዓለም መድረክ የኢትዮጵያን ሥፍራ ከፍ እናደርጋለን ብለዋል ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)።

"ህልማችን ሩቅ ነው፤ ተስፋችን የሚጨበጥ ነው፤ የገባንበትን ጥልቅ እንቅልፍ ህዳሴ በንጋት አንቅቶናል" ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፣ ርዕያችን እንደ ኢትዮጵያዊ እና አፍሪካዊ ጠቃሚ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የተተከለ መሆኑን ማስታወስ እንደሚገባም ጠቁመዋል፡፡

በዚህ መንፈስ የሶማሌ ክልል መንግስት በቱሪዝም አዳዲስ እድሎችን እየከፈተ እንደሚገኝም ጠቅሰው፣ ወደ መጠናቀቂያ ምዕራፍ በደረሰው የገበታ ለሀገር ፕሮጀክት ለምስራቁ የሀገራችን ክፍል አዲስ ዋጋ የጨመረ እድል እየፈጠረ መሆኑን ገልፀው፣ በአጠቃላይም የተመለከቱት የሥራ እድገት በጂግጂጋ እና በመላው ክልሉ የሚስተዋለውን መነቃቃት የሚያሳይ ስለመሆኑም ተናግረዋል፡፡

በርግጥም ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ በተለያ ክልሎች ሰፊ መነቃቃቶች እየተፈጠሩ እና ያልተነኩ አቅሞች ጭምር እየታዩ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ። ለአብነትም ግብርና ሚኒስቴር ጥር 14 ቀን 2017 ዓ.ም ይፋ ባደረገው መረጃ መሰረት በፊት ጾሙን ሲያድር የነበረው ለም የአፋር ክልል መሬት በመስኖ ስንዴ ልማት ፕሮግራም አማካኝነት እየለማ ይገኛል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር
ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የኦጋዴን ፈሳሽ የተፈጥሮ ጋዝ ፕሮጀክት የመጀመሪያ ዙር ባስመረቁበት ወቅት

ኢትዮጵያ በገፀ-ምድርና በከርሰ-ምድር ውሃ የታደለች እና ለመስኖ ምቹ ስነ-ምህዳር ቢኖራትም ግብርናው በተለይ ሰብል ልማቱ በዝናብ ላይ ጥገኛ ሆኖ መቆየቱ ለምግብ ዋስትናው ችግር እንደ አንዱ ምክንያት ሊጠቀስ ይችላል ይላል መረጃው፡፡

በሶማሌ ክልል የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ከዳንጎቴ ግሩፕ ጋር በመተባበር የሚገነባው የዩሪያ ማዳበሪያ ፋብሪካ መሰረተ ድንጋይ በተቀመጠበት ወቅት የዳንጎቴ ግሩፕ ባለቤት አሊኮ ዳንጎቴ ባስተላለፉት መልዕክት አሁን ላይ ኢትዮጵያ ኢንቨስተሮችን መሳብ የምትችል ሀገር ሆናለች፤ ለዚህም የሀገሪቱ መንግሥት ያደረገው ጥረት የሚደነቅ ነው ብለዋል።

በቅርቡ የተጠናቀቀው ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ በመመረቁ የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት ያስተላለፉት አሊኮ ዳንጎቴ ግድቡን በራስ አቅም መገንባት መቻሉ እኛ አፍሪካውያን በራሳችን ምንም ነገር ማድረግ እንደማያቅተን ማሳያ መሆኑን መስክረዋል፡፡

በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት ትምህርት ክፍል ተባባሪ ፕሮፌሰር ይንገስ አለሙ (ዶ/ር) የዳንጎቴ ግሩፕ ባለቤት አሊኮ ዳንጎቴ ኢትዮጵያ ለአፍሪካ የመቻል ማሳያ መሆኗን መጥቀሳቸው ትክክል መሆኑን አንስተው፣ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በኢትዮጵያ እየተከናወኑ ያሉ ልማቶች የሀገርን ከፍታ በፅኑ መሰረት ላይ የመገንባት የሚያስችሉና በርግጥም ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ሁለንተናዊ ተምሳሌት እየሆነች መምጣቷን የሚያመላክቱ መሆናቸውን እና ይህንንም ዓለም እያደነቀው ስለመሆኑም ተናግረዋል፡፡

ጀርመናዊው ኢኮኖሚስት አልበርት ኦቶ ሂርሽማን እ.ኤ.አ በ1958 "The Strategy of Economic Development" በሚል ርዕስ ባሳተሙት መፅሐፍ "ለምን ሚዛናዊ ልማት አስፈላጊ ሆነ?" ለሚለው ጥያቄ ቀጣዮቹን አበይት ነጥቦች ያነሳሉ፡፡ በሁሉም አካባቢዎች ያሉ ሀገራዊ ሀብቶችን በጥናት ላይ ተመስርቶ ለማልማት፣ ሚዛናዊ ልማትን ለማምጣት፣ በየአካባቢው ያሉ ያልተነኩ እምቅ ሀብቶችን ተጠቅሞ ሀገርን በፅኑ መሰረት ላይ ለመገንባትና ከፍ ለማድረግ ሁሉንም አካባቢዎች እና ሀብቶች ታሳቢ ያደረገ ሚዛናዊ ልማት እንደሚያስፈልግ ጠቅሰዋል፡፡

የተለያዩ አካባቢዎች የተለያዩ ጥንካሬዎች እንዳሏቸው የጠቀሱት ጀርመናዊው ኢኮኖሚስት አልበርት ኦቶ ሂርሽማን ለአብነትም እንደ አካባቢው ሁኔታ ግብርና፣ ቱሪዝም፣ ማኑፋክቸሪንግ ወይም ዲጂታል ፈጠራን በማበረታታት እና በመጠቀም የሀገርን ሁለንተናዊ ከፍታ በአስተማማኝ መሰረት ላይ ለመገንባት ያግዛል ብለዋል፡፡

ለአብነትም ቻይና የባህር ዳርቻን ብልጽግና ከሌሎች አካባቢዎች ልማት ጋር ለማመጣጠን በዋና ዋና የመሠረተ ልማት ፕሮጄክቶችን በምዕራባዊ ክፍሎቿ ኢንቨስት በማድረግ እና ሁሉንም የሀገሪቱን አካባቢዎች አቅም በመለየትና በመጠቀም አሁን ላለችበት ከፍታ መሰረት እንደጣለች በዋቢነት ጠቅሰዋል፡፡

በሌላ በኩልም የህንድ ዕድገት ምንጭ ይኸው ሚዛናዊ ተሳትፎና ልማት መሆኑን የጠቀሱት ጀርመናዊው ኢኮኖሚስት፣ ህንድ ሁሉንም የሀገሪቱን ክፍሎች የሚያስተሳስሩ የኢንዱስትሪ ኮሪደሮችን ፈጠረች በዚህም ከፍታዋን ጨመረች፡፡ ብራዚልም ዕድገት ክልላዊ የማኑፋክቸሪንግ እና የከተማ ልማት ማበረታቻዎችን በማድረግና ምቹ አሰራርን በመፍጠር ሚዛናዊ ኢኮኖሚን በመገንባት መሰረት ያለው ዕድገት ማስመዝገቧን ጀርመናዊው ኢኮኖሚስት በመፅሐፋቸው አስፍረዋል፡፡

ካደጉ ሀገራት ልምድ በመነሳት ኢትዮጵያም እየተከተለች ያለው የኢኮኖሚ መስመር እና እየተከናወኑ ያሉ ታላላቅ ልማቶችን ዋቢ በማድረግ የኢትዮጵያን ከፍታ አይቀሬነት በርግጠኝነት መናገር እንደሚቻልም ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ቆይታ ያደረጉት በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት ትምህርት ክፍል ተባባሪ ፕሮፌሰር ይንገስ አለሙ (ዶ/ር) ተናግረዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION
INDUSTRY DEVELOPMENT BUREAU

## እንኳን ለኢሬቻ በዓል አደረሳችሁ!

በሀገራችን ከዘመን አቆጣጠር አንፃር የወራት መጀመሪያ ተደርጎ የሚታወቀው የመስከረም ወር ነው። ወሩ በሀገራችን የዘመን አቆጣጠር የዘመን መለወጫ ብቻ ሳይሆን ትልልቅ ኃይማኖታዊ እና ህዝባዊ የአደባባይ በዓላት የሚከወንበትም ነው። ከምናከብራቸው የአደባባይ በዓላት ውስጥ ኢሬቻ አንዱ ነው፡፡

ኢሬቻ የኦሮሞ ሕዝብ የገዳ ስርዓት አንዱ አካል የሆነ ህዝባዊ በዓል ነው። ክረምቱ አልፎ ብራ ሲሆን ተፈጥሮን የፈጠረ ፈጣሪ የሚመሰገንበት የምስጋና በዓል ነው። የኦሮሞ ሕዝብ ጥልና ክርክርን በይቅርታ ተሻግሮ፣ በንጽሕና ፈጣሪውን የሚያመሰግንበት የሰላምና የፍቅር በዓል ነው።

በመሆኑም በዓሉ እሴቱን እና ትውፊቱን ጠብቆ እንዲከበር ከተማ አስተዳደራችን ላለፉት ዓመታት ሲሰራ መቆየቱን እያስታወስን፤ የዘንድሮው የኢሬቻ በዓልም እንደባለፉት ዓመታት ሁሉ በሰላም እና በፍቅር በተመሳሳይ መንገድ እንዲከበር ማድረግ ይገባል።
እንደ ኢሬቻ አይነት የአደባባይ በዓላት በሕዝቦች መካከል መቀራረብን፣ መተሳሰብን፣ መረዳዳትን፣ ሕብረ ብሔራዊ ወንድማማችነትና እህትማማችነት እንዲያብብ ያደርጋሉ፡፡

ኢሬቻን ጨምሮ የአደባባይ በዓላት የደስታና የፌሽታ የምስጋና በዓላት ብቻ ሳይሆኑ ለኢኮኖሚው መነቃቃትም የራሳቸው ፋይዳ ያላቸው በመሆናቸው ለከተማችን እድገት የራሱ አዎንታዊ ድርሻ ያበረከታልና በልዩ ልዩ ዝግጅት በድምቀት መከበሩ ቀጥሏል።

በመሆኑም ኢሬቻ ብዙ ህዝብ ወደ አደባባይ ወጥቶ የሚከበር በዓል እንደመሆኑ ሁላችንም በፍቅር፣ በመተሳሰብ፣ በአብሮነት እና በአንድነት ማክበር ይገባናል።



አቶ ጃንጥራር አባይ
የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ እና
የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ

**መልካም
የኢሬቻ በዓል**
Ayyaana Gaarii

GRAND AFRICAN ORGANIZATIONAL AND LEADERSHIP AWARD ORGANIZATION

## እንኳን ለኢሬቻ በዓል አደረሳችሁ!

ግራንድ አፍሪካን የተቋማትና የአመራር ሽልማት ድርጅት በሀገራችን በአምራችነትም ሆነ በአገልግሎት ሰጪነት የሰሩ ተቋማት ለሀገር እና ለህዝብ ለሰሩት ስራ ምስጋና፣ ሽልማትና እውቅና በመስጠት የላቀ ስራ በመስራት እንዲዘልቁ ለማድረግ የተቋቋመ ብቸኛ የሽልማት ድርጅት ነው፡፡

አቢሲኒያ የኢንደስትሪ ሽልማት ድርጅት የአቢሲኒያ የከፍተኛ ክብር ሎሬቶች ሽልማት ድርጅት እህት ኩባንያ በመሆኑ ተደራቢ ስም ላለመጠቀምና ኢትዮጵያ የአፍሪካ ዋና መቀመጫ በመሆኗ ራዕያችንም የአፍሪካን ተቋማት እንዲያቅፍ በመደረጉ ስሙ ግራንድ አፍሪካን የተቋማትና የአመራር ሽልማት ድርጅት በሚል ተቀይሯል፡፡

የ2017 ዓ.ም ተሸላሚዎች የሚሸለሙበት ቀን ጥቅምት 2 ቀን 2018 ዓ.ም እና ጥቅምት 9 ቀን 2018 ዓ.ም ሲሆን የሽልማቱ ስፍራ በዓድዋ ድል መታሰቢያ ፓን አፍሪካ አዳራሽ ነው፡፡ ግራንድ አፍሪካን የተቋማትና የአመራር ሽልማት ድርጅት በሚል መጠሪያ ይጠራል፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ ስልክ 0911-510783 /0930-329134 ይደውሉ።**



**ትጉኃንን እንሸልማለን!
መልካም በዓል!**

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የስራና ክህሎት ቢሮ
Addis Ababa City Administration
Labor and Skills Bureau

## እንኳን ለ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ! አደረሰን!



ከሁሉ አስቀድሜ የሰላም፣ የእርቅና የአብሮነት መገለጫ ለሆነው የኢሬቻ በዓል በሰላም እና በጤና አደረሳችሁ፣ አደረሰን ለማለት አወዳለሁ። ኢትዮጵያችን የየራሳቸው እሴትና ትውፊት ያላቸው በርካታ ሀገር በቀል እምነቶችና ጥንታዊ ኃይማኖቶች ተቻችለው በአንድነት የሚኖሩባት የብዝሃነት ምድር እንደሆነች ይታወቃል። በዩኔስኮ ከተመዘገቡ እና ኢትዮጵያ ለዓለም ካበረከተቻቸው የማይዳሰሱ ከ15 በላይ ቅርሶች መካከል አንዱ የሆነው ገዳ ስርዓት መገለጫ ኢሬቻ ነው።

የኢሬቻ በዓል የሰው ልጅ በተፈጥሮ ያለውን አንድነትና አብሮ መኖርን እያደነቀ ለፈጣሪው ምስጋና የሚያቀርብበት ልዩ በዓል ነው። ኦሮሞ ከገዳ ስርዓት በወረሰው እሴት መሠረት ክረምቱ አልፎ መስከረም ሲጠባ የክረምቱን ጨለማ አሳልፈህ ማሳውን አሳምረህ፣ ብርሀን ስላሳየህን ፈጣሪ ምስጋና ይግባህ ብሎ እርጥብ ሳር በመያዝ ወደ መልካ(ወንዝ) በማቅናት ኢሬቻን ያከብራል።

ይሁንና ኢሬቻና መሰል የምስጋናና የዕርቅ በዓላት ትውፊታቸውን እና እሴታቸውን ጠብቀው እንዳይከበሩ ለብዙ ዘመናት የተለያዩ ጫናዎች ሲደረግባቸው ቆይቷል። የለውጡ መንግስታችን ባለፉት ሰባት ዓመታት ኢሬቻና መሰል ጠቃሚ በዓላት ህብረ-ብሔራዊ አንድነታችንን በሚያጠናክር መልኩ ትውፊታቸውን ጠብቀው ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲሸጋገሩ ለማድረግ ከህዝቡ ጋር በመተባበር በልዩ ሁኔታ ሲሰራ ቆይቷል/እየሰራም ይገኛል።

በቀደሙት ስርዓቶች ከፍተኛ ጫና ሲደረግባቸው ከነበሩ የታላቁ የኦሮሞ ህዝብ በዓላት መካከል አንዱ የሆነው ኢሬቻ ቀድሞ ወደ ሚከበርበት ቦታ በመመለስ ባህልና ወጉን ጠብቆ እንዲከበር ማድረግ ተችሏል። ይህም በከተማችን አዲስ አበባና በአጎራባች የኦሮሚያ ክልል ከተማ ነዋሪዎች መካከል ያለውን ማህበራዊ መስተጋብር እንዲጠናከር ከማድረጉ ባሻገር በዓሉ በአዲስ አበባ መከበር መጀመሩ ለከተማችን ነዋሪዎች የሥራ ዕድል በመፍጠር ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን ማስገኘት ችሏል። ሁላችንም እንደምናውቀው በዓሉን ለማክበር በ100ሺዎች የሚቆጠሩ ህዝቦች ወደ ከተማችን ገብተው በሚወጡበት ጊዜ በሆቴልና ንግድ ዘርፍ ከተሰማራው ጀምሮ በተለያዩ የገቢ ማስገኛ ተግባራት ላይ የሚገኙ የከተማችን ነዋሪዎች በመቶ ሚሊዮኖች ገቢ ማግኘት የሚችሉበት ሁኔታ እየተፈጠረላቸው መጥቷል።

የዘንድሮው ሆራ ፊንፊኔ በዓል ታላቁ የህዳሴ ግድባችንን በተባበረ ክንዳችን አጠናቀን ባስመረቅንበትና በዚህም ሀገራችን ኢትዮጵያ በቀጠናው ያላትን ጂኦ-ስትራቴጂካዊ ቁመና ማደስ በጀመረችበት ማግስት የሚከበር መሆኑ በዓሉን የተለየ ያደርገዋል። ይህም የማንሰራራታችን መገለጫ የሆነው የህዳሴ ግድባችንን ማጠናቀቃችን ኢሬቻና መሰል በዓላት ህብረ-ብሔራዊ አንድነታችንን በማጎልበት ጠንካራ ሀገረ-መንግስት ለመገንባት የሚኖራቸው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑን ከግምት ውስጥ አስገብተን በዓላቱን ይበልጥ ለማስተዋወቅ ጠንክረን እንድንሰራ ያደርገናል።

ሌላው የዘንድሮውን ኢሬቻ በዓል የተለየ የሚያደርገው በሁለት ዙር በተከናወነው የኮሪደር ልማትና የወንዝ ዳርቻ ልማት ከተማችን አዲስ አበባ ለነዋሪዎቿ ምቹ፣ ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጪ ሀገር ጎብኚዎች ደግሞ ምርጧ የቱሪስት መዳረሻ ከተማ ማድረግ በቻልንበት ጊዜ ላይ የሚከበር መሆኑ ለበዓሉ ልዩ ድባብ እና ምቾት የሚፈጥር መሆኑ ነው።

የዘንድሮው የኢሬቻ በዓል ልክ እንደ ሁልጊዜው ህብረ-ብሔራዊ አንድነታችንን የምናጠናክርበትና አብሮነታችንን አጉልተን የምናሳይበት የሰላም፣ የዕርቅና የብልፅግና እንዲሆንልን እመኛለሁ።

**አቶ ጥራቱ በየነ፤ በምክትል ከንቲባ ማዕረግ**

**የአዲስ አበባ ስራና ክህሎት ቢሮ ኃላፊ**

---

## GreenLife
### Speciality Dental Clinic

**እንኳን ለ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል አደረሳችሁ!**

15+ Years







**የሚለው ግሪን ላይፍ ዴንታል ክሊኒክ ሳይሳቀቁ ይሳቁ ይላችኋል!**

**የምንሰጣቸው አገልግሎቶች**

- ኮስሞቲክስ - DENETSTRY እና ROOT CANAL TERAPY
- CAD-CAM በመጠቀም በፍሎራይድ የተጠቁ ጥርሶችን ፍፁም ውብትን እናላብሳለን
- የተለያዩ የብሬስ አማራጮችም አሉን
- የተነቀሉና የወለቁ ጥርሶችን በ IMPIANT እንተክላለን

**Dr. Robera Chala**
Senior Expert Dental Surgeon

**ይደውሉ**
0988212222
www.Greenlifethiopia.com

**አድራሻ**
**ቦሌ አትላስ መብራቱን እንደተሻገሩ ራካን ህንፃ 2ኛ ፎቅ**

ኢሬቻ ለኢትዮጵያ ማንሰራራት!

# በቂርቆስ ክፍለ ከተማ አስተዳደር



## እንኳን ለኢሬቻ የአብሮነት በዓላችን በሰላምና በጤና አደረሳችሁ!!

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈጻሚ
ምስክር ነጋሽ (ዶ/ር)

የከተማችን መሐል የሆነችው ቂርቆስ ኃይማኖታዊ፣ ባህላዊና የተለያዩ በዓላቶች የሚከበሩበት ቦታ እንደመሆኑ መጠን ክፍለ ከተማችንን ለየት ያደርገዋል። የዘንድሮውን የኢሬቻ በዓል ስናከብር በተለያዩ ዘርፎች ድርብ ድል የተጎናፀፍንበት ስመጥሩን የዐባይ ውኃ ፍትሐዊ በሆነ አግባብ ለመጠቀምና ዘመን ተሻጋሪ ምኞታችንን ዕውን ለማድረግ በመንግስታችንና በህዝባችን ሀገራዊ አቅም የተቀናጀና ያላሰለሰ ከፍተኛ ጥረት ገንብተን የፍሬው ተቋዳሽ ለመሆን የቻልንበት “የነፃነታችን ዓርማ”! የሆነውን ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድባችንን የተለያዩ ሀገራት መሪዎች በታደሙበት በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን በዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተመርቆ ሀገራችን ኢትዮጵያም ከስም ባለፈ በዓባይ ውኃ የመጠቀም ሀገራዊ መብቷንና ሉዓላዓዊነቷን ልክ እንደ አደዋ ድል ሁሉ ከፍ ያደረገችበት እና ይህንንም ያረጋገጠችበት ከመሆኑም ባሻገር ሌሎች ትላልቅ ፕሮጀክቶችን ለመገንባት የተበሰሩበት የሀገራችንን የማንሰራራትና ከፍታ በአንፀባራቂ ድል የጀመርንበት በመሆኑ ልዩ ያደርገዋል፡፡

የህብረ- ብሔራዊነታችን ምሰሶ እና የአብሮነታችን ዋነኛ ማሳያ የሆነው ኢሬቻ ሆራ በዓላችን የአባ-ገዳ ስርዓት መገለጫ ከሆኑት መካከል የምስጋና እና የምልጃ በዓል ሲሆን፤ የተከበረውና የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ባለቤት የሆነው ሰፊው የኦሮሞ ህዝብ ሁሉን ማድረግ ለሚችል ፈጣሪ  ዋቃ - አምላክ ምስጋናና ክብር የሚያቀርብበት ስርዓት ከመሆኑም ባሻገር መላ ህዝባችን ላገኘው ፀጋ፣ በረከት፣ ሰላም፣ ደስታ፣ ጤና፣ ዕድሜ፣ ፍቅርና ክብር ለአንድ ዋቃ - አምላክ ምስጋና የሚያቀርብበት የዕፁብ ድንቅ ዕሴታችን ክብረ- በዓል ነው!!

ኢሬቻ ከዘመን ወደ ዘመን ከአንድ ወቅት ወደ ሌላ ወቅት በሰላም ያሸጋገረውን ዋቃ - አምላኩን የሚያመሰግንበትና የክረምቱ ጭጋግ አልፎ ብራ ሲሆን፣ ወንዞች ጎድለው ምድር አረንጓዴ ለብሳ በአበቦች ስትዋብ፣ ክረምቱ ወደ ፀደይ ሲሸጋገር፣ የተዘራው ሰብል ሲያሸት፣ መጭው ዘመን የሰላም፣ የደስታ፣ የፍቅር፣ የአብሮነት እንዲሆን የሚለመንበት፣ የተጣላ የሚታረቅበት፣ የተራራቀ የሚቀራረብበት፣ ፈጣሪ የሚመሰገንበት፣ የምርቃት፣ የምስጋና፣ የተማፅኖ፣ የእርቅ፣ የይቅርታ፣ የፍቅር፣ የአንድነት፣ የወንድማማችነትና እህትማማችነት የበረከትና የቃል-ኪዳን ታላቅ በዓል ነው።

የተከበራችሁ የክፍለ ከተማችን ነዋሪዎች የኢሬቻ ክብረ- በዓል የመታደስ እና የመሰባሰብ የብርሃን ምልክት እና የማይናወጥ የህብረ- ብሔራዊነታችን ምሰሶ ከመሆኑም በላይ በበዓሉ አዲስ ተስፋ ይሰነቃል ፈጣሪያችንም ይመሰገናል፡፡

በብዝሃነት አጊጣና ተውባ በትጉህ እጆች ያበበችው የአዲስ ፈርጥ ጉዞ ላይ ያለችው ቂርቆስ ክፍለ ከተማችን ወደ ጋራ ቤታቸው ፊኒፊኔ የሚመጡ እንግዶቿን ከዚህ በፊት ስታስተናግድ  ከነበረው ከፍ ባለ ዝግጅት ተቀብላ  በተለመደው ኢትዮጵያዊ ጨዋነት ለማስተናገድ የእንግዶቿን መምጣት በጉጉት እየተጠባበቀች ትገኛለች፡፡

በአጠቃላይ፡- ይህን የአደባባይ በዓል ስናከብር ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ልዩ ትኩረት በመስጠት ክብረ- በዓሉ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ሁሉም የኃይማኖት አባቶች፣ አባ ገዳወች፣ ሐደ ስንቄዎች፣ የሐገር ሽማግሌዎች፣ ወጣቶች፣ ሴቶች ሁሉም የህብረተሰባችን ክፍሎች በበዓሉ ለመታደም የሚመጡ እንግዶቻችንን በትህትና በመቀበል የበኩላችሁን የላቀ አስተዋፅኦ ትወጡ ዘንድ የክፍለ ከተማው አስተዳደር በአክብሮት ለማስገንዘብ ይወዳል፡፡
በድጋሜ እንኳን ለኢሬቻ ክብረ በዓል በሰላም አደረሳችሁ፡፡ በዓሉም የሰላም፣ የፍቅር፣ የጤና፣ የብልፅግና እና የማንሰራራት ዘመን እንዲሆንልን የክፍለ ከተማው አስተዳደር መልካም ምኞቱን በአክብሮት ለመግለፅ ይወዳል!!





መልካም በዓል!!

## ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ክፍት የስራ መደቦች ላይ ሥራ ፈላጊዎችን አወዳድሮ በኮንትራት ለመቅጠር ይፈልጋል፡፡

| ተ.ቁ | የሥራ መደቡ መጠሪያ | ደረጃ | ደመወዝ | ጥቅማ ጥቅም | ተፈላጊ የትምህርት ዓይነትና ደረጃ | | አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ | የሚያስፈልገው የሰው ኃይል ብዛት | የሥራ ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | የትምህርት ዓይነት | የትምህርት ደረጃ | | | |
| 1 | የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ፈረቃ አስተባባሪ ባለሙያ I | VIII | 6,940 | የቤት ኪራይ ድጎማ አበል በወር 1500 ብር | ማኔጅመንት እና አቻ፣ ትራንስፖርት ማኔጅመንት እና አቻ፣ የሰው ኃይል አስተዳደር እና አቻ፣ ፐብሊክ አድሚንስትሬሽን እና አቻ፣ ቢዝነስ አድሚንስትሬሽን እና አቻ | የመጀመሪያ ዲግሪ | 0 ዓመት | 15 | መሥሪያ ቤቱ የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት በሚሰጥበት ቦታ /በሾላ ቁጥር ሁለት፣ በጀሊ ባር፣ በባሻ ወልዴ፣ በአፍሪካ ህብረት እና በቴዎድሮስ አደባባይ/ |
| 2 | የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ሰራተኛ I | VI | 6,058 | የቤት ኪራይ ድጎማ አበል በወር 1500 ብር | ማኔጅመንት እና አቻ፣ ትራንስፖርት ማኔጅመንት እና አቻ፣ አካውንቲንግ እና አቻ፣ ሰርቬይንግ እና አቻ፣ ማርኬቲንግ እና አቻ፣ ኢኮኖሚክስ እና አቻ፣ ኮምፒውተር ሳይንስ እና አቻ፣ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ/ ሳይንስ እና አቻ፣ ቢዝነስ አድሚንስትሬሽን እና አቻ | የኮሌጅ ዲፕሎማ ወይም 10+3 ዲፕሎማ ወይም ሌቭል III | 0 ዓመት | 54 | |
| 3 | የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያ I | VI | 6,058 | የቤት ኪራይ ድጎማ አበል በወር 1500 ብር | ኮምፒውተር ሳይንስ፣ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ/ ሳይንስ | የኮሌጅ ዲፕሎማ ወይም 10+3 ዲፕሎማ ወይም ሌቭል III | 0 ዓመት | 10 | |
| 4 | ፎርማን | X | 7,934 | የቤት ኪራይ ድጎማ አበል በወር 1250 ብር | ሲቪል ኢንጂነሪንግና አቻ፣ ኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂና አቻ፣ ኮንስትራክሽን ማኔጅመንትና አቻ | ሌቭል IV እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /COC/ ያለው/ያላት | 4 ዓመት | 1 | በዋናው መ/ቤት |
| 5 | የቀለም ማሽን ዋና ኦፕሬተር | IX | 7,424 | የቤት ኪራይ ድጎማ አበል በወር 1250 ብር | ኤሌክትሮሜካኒካል ቴክኖሎጂና አቻ፣ ማኑፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂና አቻ፣ ፕሮዳክሽን ቴክኖሎጂና አቻ | ሌቭል IV እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /COC/ ያለው/ያላት | 4 ዓመት | 2 | በዋናው መ/ቤት |
| 6 | የቀለም ማሽን ረዳት ኦፕሬተር | VIII | 6,940 | የቤት ኪራይ ድጎማ አበል በወር 1500 ብር | ኤሌክትሮሜካኒካል ቴክኖሎጂና አቻ፣ ማኑፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂና አቻ፣ ፕሮዳክሽን ቴክኖሎጂና አቻ | ሌቭል IV እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /COC/ ያለው/ያላት | 2 ዓመት | 2 | በዋናው መ/ቤት |
| 7 | የቦይለር ማሽን ዋና ኦፕሬተር | IX | 7,424 | የቤት ኪራይ ድጎማ አበል በወር 1250 ብር | ኤሌክትሮሜካኒካል ቴክኖሎጂና አቻ፣ ማሽን ቴክኖሎጂና አቻ፣ ማኑፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂና አቻ፣ ፕሮዳክሽን ቴክኖሎጂና አቻ | ሌቭል IV እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /COC/ ያለው/ያላት | 4 ዓመት | 2 | በዋናው መ/ቤት |
| 8 | የቦይለር ማሽን ረዳት ኦፕሬተር | VIII | 6,940 | የቤት ኪራይ ድጎማ አበል በወር 1500 ብር | ኤሌክትሮሜካኒካል ቴክኖሎጂና አቻ፣ ማኑፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂና አቻ፣ ፕሮዳክሽን ቴክኖሎጂና አቻ | ሌቭል IV እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /COC/ ያለው/ያላት | 2 ዓመት | 2 | በዋናው መ/ቤት |
| 9 | ዋና የቅየሳ ባለሙያ | VIII | 6,940 | የቤት ኪራይ ድጎማ አበል በወር 1500 ብር | ሰርቬይንግ ቴክኖሎጂና አቻ | ሌቭል IV እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /COC/ ያለው/ያላት | 2 ዓመት | 2 | በዋናው መ/ቤት |
| 10 | ረዳት የቅየሳ ባለሙያ | VII | 6,485 | የቤት ኪራይ ድጎማ አበል በወር 1500 ብር | ሰርቬይንግ ቴክኖሎጂና አቻ | ሌቭል IV እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /COC/ ያለው/ያላት | 0 ዓመት | 2 | በዋናው መ/ቤት |
| 11 | የመንገድ ብሎወር ማሽን ኦፕሬተር | IX | 7,424 | የቤት ኪራይ ድጎማ አበል በወር 1250 ብር | ኤሌክትሮሜካኒካል ቴክኖሎጂና አቻ፣ ማሽን ቴክኖሎጂና አቻ፣ ማኑፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂና አቻ፣ ፕሮዳክሽን ቴክኖሎጂና አቻ | ሌቭል IV እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /COC/ ያለው/ያላት | 2 ዓመት | 2 | በዋናው መ/ቤት |

**ማሳሰቢያ**

- አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ 10 /አስር/ ተከታታይ የሥራ ቀናቶች ብቻ ማመልከት ይችላሉ፡፡
- የምዝገባ ቦታና ስዓት ከ 22 ወደ መገናኛ በሚወስደው መንገድ መከሊት ህንፃ 10ኛ ፎቅ የሰው ኃይል አስተዳዳር ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 06 በሥራ ሰዓት ጠዋት ከ2፡30 - 6፡30 ሰዓት ከሰዓት ከ7፡30 - 11፡30 ሰዓት ድረስ
- በምዝገባ ወቅት አመልካቾች ዋናውን የትምህርት ማስረጃ ኦረጅናል ከማይመለስ ፎቶ ኮፒ ጋር ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት የሚቀርብ የሥራ ልምድ ማስረጃ የሥራ ግብር የተከፈለበት መሆኑን የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡
- ከደረጃ III እስከ ደረጃ V የትምህርት ደረጃ ያላቸው አመልካቾች የሙያ ምዘና የብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ (COC) ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- የሥራ ቦታ አዲስ አበባ በዋናው መ/ቤት፣ በቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች እና መሥሪያ ቤቱ የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት በሚሰጥበት ቦታ

**ስልክ ቁጥር 0913045587**

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን**

# ኢሬቻን በዩኔስኮ የማስመዝገብ ፋይዳዎች


ፎቶ ከገፀ ድር
የምስጋናና የእርቅ በዓል የሆነው ኢሬቻ በዩኔስኮ መመዝገቡ ሀገራዊ ጥቅሙን የበለጠ ከፍ ያደርገዋል

በመለሰ ተሰጋ

ቅርስ ያለፈውን መልካም ስኬትና እውነት ማስቀጠያ ድልድይ፣ ዛሬን ማጣፈጫ ቅመም፣ ለመጭው ትውልድ የምናስተላልፈው ቋሚና ሕይወት ያለው ሐውልት ነው፡፡ የቅርሶቻችን ምንጭ የሆኑት ባህልና ተፈጥሮ ደግሞ የማይተኩ የሰው ልጅ የመኖር አብነቶች ናቸውና ሊጠበቁ ይገባል፤ ይላል የተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) ቅርስን በዓለም አቀፍ ደረጃ መመዝገብና እውቅና መስጠት ለምን አስፈለገ ሲል በይፋዊ ገፀ ድሩ ባሰፈረው መረጃ፡፡

ዓለማችን በድንቃ ድንቅ ነገሮች የተሞላች የሰው ልጆች ውብ በረከት ናት። ከታሪካዊ ከተሞች፣ ቤተ መንግስቶች እና ካቴድራሎች እስከ አስደናቂ ተራሮች፣ የዝናብ መፍለቂያ ደኖች እና ውቅያኖሶች፣ በህብረ ቀለማት ያሸበረቁ ባህሎችን የመሳሰሉ ታላላቅ ሀብቶች የሰው ልጆች ሁሉ ናቸው።

ይሁን እንጂ የተፈጥሮ አደጋዎች፣ ጦርነቶች፣ የአየር ንብረት ለውጥ፣ ቅርሶችን ታሳቢ ያላደረጉ ልዩ ልዩ ግንባታዎች እና መሰል አደጋዎች የቅርሶችን ሕልውና እየተፈታተኑት እንደሆነም በመረጃው ተመላክቷል፡፡

ይህንንም ተከትሎ በዓለማችን በየትኛውም ጥግ ያሉ ባህላዊና ተፈጥሯዊ ቅርሶች ክብርና ከፍታቸው ተጠብቆ ዓለም አቀፍ የሰው ልጆች ሁሉ ሀብት ይሆኑ ዘንድ ለመመዝገብና ለመጠበቅ እ.ኤ.አ 1972 የወጣውን የዩኔስኮ ኮንቬንሽን (የዓለም ቅርስ ስምምነትን) መሰረት በማድረግ 190 ሀገራት ስምምነቱን አፅድቀውታል፡፡

የዓለም ቅርስ ኮሚቴ በፓሪስ ባካሄደው 47ኛው ዓመታዊ ጉባኤ ዩኔስኮ 26 አዳዲስ የባህልና የተፈጥሮ ቦታዎችን በዓለም አቀፍ ቅርስነት መዝገብ ውስጥ አካቷል። ዩኔስኮ እ.ኤ.አ ሐምሌ 17 ቀን 2025 ባወጣው ጋዜጣዊ መግለጫ መሰረት በ170 ሀገራት ያሉ 1 ሺህ 248 ቅርሶችን በዓለም ቅርስ መዝገብ አስፍሯል፡፡

የዩኔስኮ ዋና ዳይሬክተር ኦድሪ አዙሌይ የዓለም ቅርስ ኮሚቴ በፓሪስ ባካሄደው 47ኛው ዓመታዊ ጉባኤ ላይ ባደረጉት ንግግርም "ቅርሶችን በዓለም ሀብትነት ማስመዝገብ ከብሔራዊ ድንበራቸው የተሻገሩ የባህላዊና የተፈጥሯዊ ፀጋዎች የሰው ልጆች ሁሉ ወካይ የሆኑ ልዩ ቅርሶችን የመጠበቅ እና የማስተዋወቅ ተግባር ነው" ብለዋል ።

ቅርስ አንድን ሀገር በየዘመናቱ ያለፈችባቸውን ስልጣኔ፣ ባህል፣ ወግ፣ ታሪክ፣ እሴት እና ማንነት ማሳያ ነው። ኢትዮጵያ ደግሞ የብዝሃነት አምባ በመሆኗ በርካታ ባህላዊና ተፈጥሯዊ ቅርሶች ባለቤት ናት፡፡ ቅርሶቿን በዩኔስኮ በማስመዝገብ በአፍሪካ ቀዳሚ ናት፡፡

በዩኔስኮ በዓለም ቅርስነት ከተመዘገቡ ቅርሶች መካከል የአክሱም ሐውልት፣ የላልይበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት፣ የመስቀል በዓል፣ የጌዴኦ መልክዓ ምድር፣ የኮንሶ የእርከን ስራ፣ የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ፣ የጎንደር ቤተ-መንግስት፣ የጢያ ትክል ድንጋይ፣ የታችኛው አዋሽ ሸለቆ፣ የሐረር ጀጎል ግንብ፣ ፍቼ ጫምባላላ እና የገዳ ሥርዓትን መጥቀስ እንችላለን፡፡

የገዳ ስርዓት አካል የሆነውና ደማቅ ታሪክ፣ ማራኪ ውበት ያለው በተለይ ከአደባባይ በዓላት መካከል በርካታ ህዝብ የሚታደምበት ውበትና ፍቅር አብሮነትና ይቅርታ በህብረ ብሔራዊነት ደምቆ የሚታይበትን የኢሬቻ በዓል ራሱን ችሎ በተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ ሳይንስና ባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) የዓለም ቅርስ ሆኖ እንዲመዘገብ የተለያዩ ስራዎች በመከናወን ላይ መሆናቸውን በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ እና የባህል ዘርፍ ኃላፊ አቶ ደራራ ከተማ ይናገራሉ፡፡

አቶ ደራራ እንደሚሉት በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ በየዓመቱ ለሁለት ጊዜ የሚከበረው የኢሬቻ በዓል የምስጋናና የእርቅ በዓል ተደርጎ ይወሰዳል። ኢሬቻ ከኦሮሞ ህዝብ ባሻገር የትኛውም የህብረተሰብ ክፍል የሚሳተፍበት የሰላምና አብሮነት ተምሳሌት የሆነ በዓል ነው፡፡

በዓሉ በህዝቦች መካከል መቀራረብን፣ ፍቅርንና እርቅን ለማምጣት የሚያግዝ እሴት ያለው በመሆኑ በተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ ሳይንስና ባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) የዓለም ቅርስ ሆኖ እንዲመዘገብ ለማድረግ ለሁለት ዓመታት ያህል የፈጀ ጥናት እየተደረገ ሲሆን ኢሬቻ ካለው ድንቅ እሴት አንፃርም በዩኔስኮ መመዝገቡ አይቀሬ ነው ብለዋል፡፡

ኢሬቻ የምስጋና ቀን ነው። ይህ በዓል በሁለት ቦታዎች እንደሚከበር የሚናገሩት አቶ ደራራ፣ ቦታዎቹም በሐይቆችና ወንዞች እንዲሁም በተራራዎች ላይ ነው። አንደኛው በክረምቱ መግቢያ ወቅት ላይ ሲሆን፣ ክረምቱን በሰላም አሻግረን፣ ውኃ እና እርጥቡን አትንሳን ተብሎ ፈጣሪን የሚለምኑበት፣ በተራሮች አናት ላይ የሚደረግ ነው። እርሱም ኢሬቻ ቱሉ ይባላል፡፡

ሁለተኛው ደግሞ "ከክረምቱ አስፈሪ ነጎድጓድ እንኳን ወደ ብርሃን አወጣኸን። ብራውን ሰላም አድርግልን" በማለት በሐይቆችና ጅረቶች ዙሪያ ምስጋናን በማድረስ የሚከበር ነው። ኢሬቻ የመስማማትና የአንድነት በዓል ነው። የክረምቱን የጨለማ ወራት አልፈን ወደ ብርሃን የምንወጣበት ነው ተብሎም ምስጋና ይቀርብበታል፤ ደስታም ይገለጽበታል።

ኢሬቻ በዩኔስኮ መመዝገቡ እንደ ሀገር የሚኖረው ፋይዳ ትልቅ መሆኑን የሚናገሩት አቶ ደራራ፣ ኢሬቻ በክረምቱ ጎርፍና ጭጋግ አሊያም አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የነበሩ ሰዎች በብዛት ከተለያየ ቦታ ተሰባስበው አንድ ቦታ ላይ የሚገናኙበት አጋጣሚ በመሆኑ የተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና መሰል ጥቅሞች አሉት፡፡ ለአብነትም ሰዎች ካሉበት ቦታ ተነስተው በዓሉን ለማክበር ወደ ማክበሪያ ቦታ ይንቀሳቀሳሉ። በዚህ እንቅስቃሴያቸው ውስጥ ከመነሻቸው ጀምሮ እስከ መዳረሻቸው ለምግብ እና ለመጠጥ፣ ለመኝታ እንዲሁም ለተለያዩ አልባሳትና ጌጣጌጦች ወጪ ያወጣሉ። ይህም ከፍተኛ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንዲፈጥር የሚያስችል በዓል መሆኑን አንዱ ማሳያ ነው ብለዋል፡፡

ከዚህም በላይ ልዩ የሚያደርገው ኢሬቻ ሁሉም ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ተወክለውበት የሚከበር አንድነትን የሚያጠናክር በዓል ነው፡፡ ይህንን የባህል መስተጋብር ለማየት የሚመጣው ዜጋ ቁጥርም ቀላል አይደለም፡፡

ይህንን ደማቅ የኢሬቻ በዓል ከገዳ ስርዓት ማሳያነት ባለፈ ራሱን ችሎ በተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ ሳይንስና ባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) ለማስመዝገብ በጥናት የተደገፈ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን አቶ ደራራ ይናገራሉ፡፡

ዩኔስኮ በዓሉን ለማስመዝገብ የሚያስቀምጣቸውን መስፈርቶች ለሟሟላት የሚያስችሉ ጥናቶች እየተደረጉ መሆኑንም የሚናገሩት አቶ ደራራ ዩኔስኮ ከሚያስቀምጣቸው መስፈርቶች አንፃር እንደሚመዘገብ እርግጠኛ ሆኖ መናገር ይቻላል ብለዋል፡፡

እንደ ዩኔስኮ መረጃ ከሆነ አንድን ቅርስ በዓለም ቅርስነት ለማስመዝገብ በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ያለው ጠቀሜታ፣ ዓለም አቀፍ እሴትነቱ፣ የተፈጥሮ ክስተት አሊያም ውበት፣ በዓለም ቅርስ ኮሚቴ በጂኦግራፊያዊ እና በታሪክ ተለይቶ የሚታወቅ እና መሰል መስፈርቶችን ያሟላ መሆን እንዳለበት ያስቀምጣል። ከዚህ አንፃርም ኢሬቻ የዩኔስኮን መስፈርቶች በሚገባ የሚያሟላ በመሆኑ መመዝገቡ አይቀሬ ነው ብለዋል፡፡

አንድ ቅርስ በዩኔስኮ ከተመዘገበ በርካታ ጥቅሞች እንዳሉት የተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ ሳይንስና ባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) ይፋ ያደረገው መረጃ ያትታል፡፡ ለአብነትም የሀገር ውስጥ እና የውጭ ቱሪስቶች ቁጥር የበለጠ ይጨምራል፣ ረዘም ላለ ጊዜ እንዲቆዩም ያደርጋቸዋል፤ ኢኮኖሚን ያነቃቃል፤ ከዩኔስኮ የዓለም ቅርስ ፈንድ እና ከሌሎች ዓለም አቀፍ ለጋሾች ድጋፍ ያስገኛል፤ ለቅርሶቹ ጠንካራ የህግ ጥበቃ እና የፖሊሲ ድጋፍ እንዲኖር ያደርጋል፤ የማህበረሰቡን ተሳትፎና ማህበራዊ መስተጋብር የበለጠ ያጎለብታል፤ በሀገራት መካከል ጠንካራ መስተጋብር እንዲኖር እና ዓለም አቀፍ ገፅታን በተጠናከረ መልኩ ለማስተላለፍ ይረዳል።



## ኢሬቻ የመቻቻል፣ የአብሮነት፣ የህብርና የሠላም ምልክት!

ቱባ ባህላዊ እሴቶቻችን ደምቀን የምናጌጥባቸውና የምንኮራባቸው የኅብራዊ መልኮቻችን ነፀብራቆች፣ የወል ሀብቶቻችን ናቸው፡፡

በዓሉ የመተሳሰብ፣ የአብሮነት፣ የሠላምና የፍቅር እንዲሆን መልካም ምኞታችንን እየገለፅን በዓሉን ስናከብር ምንጊዜም እንደምናደርገው ለተቸገሩ እና የእኛን ድጋፍ ለሚሹ ሁሉ አብሮነታችንን በማሳየት እንዲሆን እንጠይቃለን፡፡

## መልካም በዓል!

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር**
**የኅብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን!**

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ
CLEANSING MANAGMENT AGENCY
— ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION —

እንኳን ለ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል በሰላም፣ በፍቅርና በጤና አደረሳችሁ እያለ፤ ኤጀንሲው አዲስ አበባ ከተማ በ2022 ፅዱና የደረቅ ቆሻሻ ዑደታዊ ምጣኔ ሐብቷን ተግባራዊ ያደረገች የአፍሪካ ሞዴል ከተማ ሆና ማየትን ራዕይ ሰንቆ በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል።

አዲስ አበባ በኮሪደር ልማቱ እያመጣች ያለው ለውጥ ቀጣይነት እንዲኖረው የጽዳት ስራውም ተጠናክሮ እየተሰራ ይገኛል።

የከተማችን ጽዳት ዘላቂነት ሊረጋገጥ የሚችለው በሕብረተሰቡ ተሳትፎ በመሆኑ ሁሉም የከተማዋ ነዋሪ በጽዳት ስራው የድርሻውን እንዲወጣ መልዕክታችንን እናስተላልፋለን።



**አቶ ገዛኸኝ ዴሲሳ**
**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር**



## መልካም በዓል!




የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ
Addis Ababa City Administration Health Bureau

## እንኳን ለ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል አደረሳችሁ !

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ የሰላም፣ የአንድነት፣ የምስጋና እና የወንድማማችነት በዓል ለሆነው የ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል እንኳን በሰላም እና በጤና አደረሳችሁ እያለ መልካም ምኞቱን ይገልጻል!!

የኢሬቻ በዓል በከተማችን አዲስ አበባ መስከረም 24 ቀን በታላቅ ድምቀት በሆረ ፊንፊኔ የሚከበር እና በ25 ደግሞ በቢሾፍቱ ከተማ በሆራ አርሰዴ የሚከበር ሲሆን በዓሉ በርካታ የሀገር ውስጥና የውጭ ቱሪስቶች ጭምር በሚገኙበት በድምቀት የሚከበር በመሆኑ ለሀገራችን ብሎም ለከተማችን ትልቅ ኩራትና ድምቀት ነው።

በዓሉ በሰላም እና በጤና እንዲከበር ቢሮው አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ለሚያጋጥሙ ማንኛውም የጤና ጉዳዮች አገልግሎት የሚሰጡ በሁሉም የከተማው መግቢያ 13 ጊዜያዊ እና አንድ ተንቀሳቃሽ ክሊኒክ እንዲሁም በቂ የጤና ባለሙያዎችን፣ አምቡላንሶችን ፣ አስፈላጊውን የህክምና ግብዓቶችን በማሟላት ለአገልግሎት ዝግጁ አድርጓል፡፡

በተጨማሪም በከተማዋ በሚገኙ ሁሉም የጤና ተቋሞቻችን የህክምና አገልግሎት ማግኘት የሚቻል ሲሆን በተለይም በዓሉ በሚከበርበት በሆራ ፊንፊኔ እና አካባቢው በተዘጋጁ ጊዜያዊ የህክምና መስጫ ቦታዎች፣ በዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል እና በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል አስፈላጊውን የህክምና አገልግሎት ለመስጠት ዝግጁ መሆናቸዉን ቢሮው ይገልጻል፡፡

**መልካም የኢሬቻ በዓል!**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ



ባህል እና ኪነ ጥበብ ቢሮ
አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

## እንኳን ለኢሬቻ በዓል አደረሳችሁ!

የአዲስ አበባ ባህል እና ኪነ-ጥበብ ቢሮ እንኳን ለ 2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ እያለ፤ መልካም ምኞቱን ሲገልጽ በታላቅ ደስታ ነው! ቢሯችን አዲስ አበባ ከተማ የብዝኃ ባህል ማዕከል እንደመሆኗ የመቻቻልና የአብሮነት ከተማ እንድትሆን፣ የሀገራችንን መልካም ባህላዊ እሴቶች እና ቅርሶች ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ እንዲቻል እና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሀገራችንን እና የመዲናችንን መልካም ገጽታ ከፍ በሚያደርግ መልኩ በርካታ ስራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል እና ኪነ-ጥበብ ቢሮ ዘርፉን ከማሳደግና ከማስተዋወቅ አንጻር ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት እየሰራ የሚገኝ ሲሆን ከዚሁ ጋር ተያይዞ በከተማችን የሚገኙ አማተር የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎችን በማቋቋም፣ በማደራጀት፣ በማሰልጠንና በማብቃት እንዲሁም የኪነ-ጥበብ ማህበረሰቡ ከተማችንን የሚመጥን ስራዎችን በማዘጋጀት ለህብረተሰቡ ተደራሽ በማድረግ ረገድ አበረታች ውጤቶችን አስመዝግቧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መዲናችን አዲስ አበባ የዕደ-ጥበብ ስራዎች ማዕከል እንድትሆን እና ዘርፉ ተመራጭ እንዲሆን የማጠናከርና የመደገፍ ስራ እየሰራ ይገኛል፡፡ በዚሁ አጋጣሚ ሁሉም በከተማችን የሚገኙ የኃይማኖት ተቋማት፣ የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች፣ የዘርፉ ባለድርሻ አካላት እንዲሁም ነዋሪዎች ከጎናችን በመሆን ለከተማችን የባህል እና የኪነ-ጥበብ ዘርፍ መጠናከር የድርሻችሁን እንድትወጡ ጥሪያችንን እያስተላለፍን በዓሉ የሰላም፣ የጤና፣ የመደጋገፍ እና የአብሮነት እንዲሆን እንመኛለን!

መልካም በዓል

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል እና ኪነ ጥበብ ቢሮ



## ኢሬቻ ለሀገር ማንሰራራት!

## IRREECHA: Olka' insa Biyyaaf!!

### እንኳን ለ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ!

የአዲስ አበባ ከተማ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በከተማ አስተዳደሩ ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 መሠረት በአዋጅ ቁጥር 77/2014 ተጠሪነቱ ለከተማው ምክር ቤት ሆኖ እንደገና የተቋቋመ ሲሆን በከተማ አስተዳደሩ ስር ባሉ በመንግሥት ተቋማት እና ልማት ድርጅቶች አምስት የኦዲት ዓይነቶች ማለትም የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት፣ የክዋኔ ኦዲት፣ የገቢ ኦዲት፣ የአካባቢ ኦዲት እና ልዩ/የማጭበርበር ኦዲት እያከናወነ ይገኛል፡፡

ከመ/ቤታችን ዓላማ አንዱ በከተማ አስተዳደሩ ሥር በሚገኙ የመንግስት ተቋማት ውስጥ ለተለያዩ የልማት ሥራዎች የተመደበው በጀት ግልጽነት እና ተጠያቂነት ባለው ሁኔታ ለህዝብ ጥቅም መዋሉን በማረጋገጥ ስለ ሁኔታው ለከተማ አስተዳደሩ ምክር ቤት መረጃ መስጠት በመሆኑ ስለ ከተማ አስተዳደሩ ዕቅዶች አፈጻጸም እና በጀት አጠቃቀም ውጤታማነት አስተማማኝ መረጃ አግኝቶ በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር ምክር ቤቱን የሚያግዝ ጠንካራ የኦዲት ሥርዓት በመዘርጋት፣ አገልግሎቱን አስፍቶ መንግስት የያዘው ዘላቂ የልማትና የመልካም አስተዳደር ዓላማዎች እንዲሳኩ አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል፡፡

ለወደፊቱም የተሰጡንን ህዝባዊ ኃላፊነቶች በአግባቡ በመወጣት የህዝብ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በትጋት የምንሰራ መሆናችንን እየገለፅኩ መላው የከተማችን ነዋሪዎች ውስን የሆነውን የመንግስትና የህዝብ ሀብት ከብክነት ለመከላከል ለምናደርገው ጥረት ከጎናችን እንዲሆን ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡




የአዲስ አበባ ከተማ ዋና ኦዲተር መ/ቤት
አቶ አመንቴ መቻሉ ኢሬቻ ለሀገር ማንሰራራት!



# ኢሬቻን አድማቂዎቹ አልባሳት

* አልባሳቱ የጋራ ማንነትና ትስስርን ለማጠናከር እንደሚያገለግል ተገልጿል

**በሳህሉ ብርሃኑ**

ኢሬቻ ምስጋና፣ ሰላምና መቻቻልን ዓብይ ትኩረቱ በማድረግ በአደባባይ የሚከበር በዓል ነው፡፡ በተለይ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በአደባባይ ደምቀው ከሚከበሩ በዓላት መካከል አንዱ መሆን የቻለው ኢሬቻ ከማህበራዊ ፋይዳው ባለፈ የቱሪዝም መስህብ በመሆን እና ማንነትን በማስተዋወቅ ረገድም የራሱን ጉልህ ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡

የኢሬቻ በዓል ትውፊታዊ ዳራን በተመለከተ የተሰሩ ጥናቶች እንደሚያመላክቱት፣ የኦሮሞ ሕዝብ ያለ ፆታ፣ ዘር እና የእድሜ ልዩነት በዓሉን ለዘመናት በጋራ ሲያከብር ቆይቷል። የኢሬቻ በዓልን ለማክበር የሚወጣው ታዳሚ እንደ ሳር እና አበባ ያለ እርጥብ ነገር በእጁ ይዞ ነው። የበዓሉ ታዳሚ የየአካባቢውን ባህል፣ አልባስና አጊያጊያጥ የሚያስተዋውቅበት መድረክ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል በዓሉ፡፡

በኢሬቻ በዓል ላይ በባህላዊ አልባሳት የተሸቀረቀሩ ወጣቶች ይበልጥ የዐይን ማረፊያዎች ሆነው መመልከት እየተለመደ መጥቷል፡፡ የመጡበትን አካባቢ የሚያንጸባርቁ አልባሳት የለበሱ፣ በቡድን ሆነው በተመሳሳይ የባህል አልባሳት ያሸበረቁ ወጣቶች፣ በአንገትና እጃቸውን እጅግ በተዋቡ ባህላዊ ጌጣጌጦች የተዋቡ ሴቶችም የኢሬቻ በዓል ልዩ ድምቀቶች ናቸው፡፡

ኢሬቻ ከኦሮሞ ሕዝብ ማንነት ጋር በጥብቅ የተሳሰረ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የኖረ ታላቅ በዓል ነው የሚሉት ደግሞ የኦሮሞ አባ ገዳዎች ህብረት ዋና ጸሐፊ እና የቱለማ አባ ገዳ ጎበና ሆላ ናቸው፡፡ በዓሉ በሚከበርበት ወቅት የሚለበሱ ባህላዊ አልባሳት የየአካባቢውን ማንነት በማስተዋወቅ ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። አልባሳቱ ከውበት በላይ የሆኑ ጥልቅ ትርጉሞችን ይይዛሉ ያሉት አባ ገዳ ጎበና፣ በተለይ የሕዝቡን ታሪክ፣ እሴቶች እና የማንነት እንደሚያንፀባርቁ ገልፀዋል።

በቋሚነት በኢሬቻ በዓል እንደሚታደሙ የተናገሩት አቶ ግርማ ቱፋ በበኩላቸው፣ ኢሬቻን የሚያደምቁት ባህላዊ አልባሳት ከኛ አልፈው የውጭ ሀገር ጎብኚዎችን ሳይቀር ይማርካቸዋል። እነዚህ አልባሳት የቱሪዝም ማዕከል ሆነው የሚያገለግሉ ሲሆን፣ የኦሮሞን ሕዝብ ባህል ለዓለም ሕዝብ ለማስተዋወቅ ትልቅ አስተዋፅኦ እያደረጉ ነው ብለዋል። ጎብኚዎች ስለ ልብሶቹ ታሪክና ትርጉም በመጠየቅ፣ የኦሮሞን ባህል የበለጠ ለመረዳትና ለማድነቅ ይነሳሳሉ ሲሉም አክለዋል።

በእርግጥም በኢሬቻ ወቅት የሚለበሱ አልባሳት እንዲሁ በዘፈቀደ የተመረጡ አይደሉም። እያንዳንዱ ልብስ፣ እያንዳንዱ ቀለም እና እያንዳንዱ ጥልፍ የራሱ የሆነ ታሪካዊ እና ባህላዊ ትርጉም አለው። ለምሳሌ ነጭ ልብሶች የንጽህና፣ የሰላም እና የአዲስ ጅማሬ ምልክት ናቸው። እነዚህ አልባሳት በኢሬቻ በዓል ወቅት በብዛት የሚለበሱ ሲሆን፣ የኦሮሞን ሕዝብ በጎ እና ሰላማዊ አኗኗርን የሚያንጸባርቁ ናቸው:: እንደዚሁም የጥልፍ ሥራዎች በኦሮሞ ባህል ውስጥ ከፍተኛ ትርጉም አላቸው። የተለያዩ የእፅዋት እና የእንስሳት ቅርጾችን የሚያሳዩ ጥልፎች፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የመጣውን ጥበብ ያንፀባርቃሉ።

በሌላም በኩል እነዚህ አልባሳት አንድ ወጣት ወንድ ወይም ሴት ወደ አዋቂነት ደረጃ ሲሸጋገር፣ በትዳር ሲጣመር ወይም ማህበራዊ ደረጃው ሲቀየር የሚለብሳቸው ናቸው፡፡ ከዚህ አንፃርም አልባሳቱ የተለያዩ ትርጉሞችን ሊይዙ ይችላሉ። የተለያዩ የጌጣጌጥ ዓይነቶች አልባሳቱን የበለጠ ማራኪ ከማድረግ ባለፈ የባለቤታቸውን ማህበራዊ ደረጃ፣ ሀብት እና የቤተሰብ ታሪክ ማሳያ ተደርገውም ይወሰዳሉ።

በኢሬቻ በዓል የሚለበሱ ባህላዊ አልባሳት እንደሌሎች ባህላዊ ቅርሶች ሁሉ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉ ናቸው። አባቶች እና እናቶች ልጆቻቸውን በበዓሉ ወቅት ምን አይነት ልብስ መልበስ እንዳለባቸው ሲያስተምሩ፣ የልብሶቹን ትርጉም እና አስፈላጊነት አብረው ያስተላልፋሉ። ይህ ሂደት ባህሉ ዘመናትን ተሻግሮ እንዲቀጥል ትልቅ አስተዋፅኦ ያደርጋል።

የኢሬቻ በዓል በሚከበርበት ወቅት የሚታየው የአልባሳት ትዕይንት ዘመናዊው ትውልድም ይህንን በዓል እየተቀበለና እየተንከባከበ መሆኑ አንድ ማሳያ ስለመሆኑም አባ ገዳ ጎበና ሆላ ይገልጻሉ። ብዙ ወጣቶች በበዓሉ ላይ ለመታደም ባህላዊ አልባሳትን በመልበስ፣ በባህሉ የመኩራራት ስሜት ይሰማቸዋል ሲሉም አክለዋል አባ ገዳ ጎበና፡፡ በእርግጥም አባ ገዳው እንደሚሉት የኢሬቻን ማንነት በማህበራዊ ሚዲያ እና በሌሎች የዘመናዊ መገናኛ ብዙኃን አማካኝነት እንዲተዋወቅ ትልቅ መድረክ ፈጥሯል። የልብሶቹ ውበት በፎቶና ቪዲዮ አማካኝነት በስፋት እየተሰራጨ ነው።

ምንም እንኳን የኢሬቻ አልባሳት ባህሉን በማስተዋወቅ ረገድ ትልቅ ሚና ቢጫወቱም፣ አንዳንድ ፈተናዎችም ያጋጥሟቸዋል። ለምሳሌ የዘመናዊነት ተፅዕኖ በባህላዊው የአልባሳት ምርት ላይ ሊመጣ ይችላል የሚለው አንዱ ስጋት ነው። አንዳንድ ሰዎች ባህላዊ ጥልፎችን እና ዲዛይኖችን ከዘመናዊ ቁሶች ጋር በማቀላቀል የመነሻውን ትርጉም ሊለውጡ ይችላሉና ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል ሲሉ አባ ገዳ ጎበና ሆላ መክረዋል። አክለውም፣ እነዚህ እርስ በእርስ ለመተዋወቅ ትልቅ ዕድል የሚፈጥሩት አለባበሶች ስርዓቱን የተከተሉ መሆን ይኖርባቸዋል ሲሉም አሳስበዋል፡፡

ከውበት በላይ የሆኑት እነዚህ አልባሳት፣ ባህሉን በማስተዋወቅ፣ ትውልዶችን በማገናኘት እና የቱሪዝም ፍሰትን በመጨመር ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል የሚሉት ደግሞ የባህልና ሰላም ተመራማሪ ወሰን ባዩ (ዶ/ር) ናቸው። እነዚህን አልባሳት መንከባከብ እና ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ የኦሮሞን ባህል ከትውልድ ትውልድ ለማሸጋገር አስተዋጽኦቸው ከፍተኛ ነው ብለዋል።













ፎቶ ከገፀ ድር

ልዩ ልዩ አልባሳቱ የማህበረሰቡ የእርስ በእርስ መስተጋብር ከማጎልበቱም በላይ ለቱሪዝም ዕድገት ሚናው የጎላ እንዲሆን ያደርጋል

የበዓሉ አከባበር በብዙ ረገድ እጅግ አስደሳች እንደሆነ ገልፀው፣ በተለይ ልዩ ልዩ አልባሳቱ የማህበረሰቡ የእርስ በእርስ መስተጋብር ከማጎልበቱም በላይ ለቱሪዝም ዕድገት ሚናው የጎላ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ከዚህ ባለፈም እንደ ኢሬቻ ያሉ የመሳሰሉ የአደባባይ በዓላት ለሀገር ግንባታ ሂደት እጅግ ጉልህ አስተዋጽኦ ማድረግ ይችላሉ ብለዋል የባህልና ሰላም ተመራማሪ ወሰን (ዶ/ር)፡፡

የባህልና ሰላም ተመራማሪ ወሰን (ዶ/ር) ተጠናክሮ እንዲቀጥል ሊሰራባቸው ይገባል ካሏቸው ጉዳዮች መካከል የባህላዊ አልባሳት አምራቾችን እና ዲዛይነሮችን ማበረታታት እና ድጋፍ ማድረግ የሚለው ተጠቃሽ ነው። በተመጣጣኝ ዋጋ የባህላዊ አልባሳትን የሚያመርቱ ማህበራትን ማቋቋም። ወጣቶችን ስለ አልባሳቱ ታሪክ እና ትርጉም ለማስተማር ባህላዊ የትምህርት መርሃ ግብሮችን ማዘጋጀት ይገባል ይላሉ።

ቀይ፣ ጥቁርና ነጭ ቀለማት ያላቸው አልባሳት በአንድ ላይ በህብር ሆነው ሲመጡ በፍጥነት ለኢትዮጵያዊ ተመልካች የኦሮሞ ባህል አልባሳት ቀለማትን ምስል ይከስታሉ። በኦሮሞ ባህላዊ አልባሳት ላይ በተደጋጋሚ የሚስተዋለው የኦዳ ዛፍ ምልክት ነው። ይህ የኦዳ ዛፍ ምልክት በቀሚሶች፣ ሱሪዎችና ኮቶች ላይ በሕትመት ጥበብ ገብቶ ተጨማሪ ፈርጥ በመሆን ሲያገለግልም ይስተዋላል። በአዲስ ዓመት መባቻ በመስቀል እና በተለይም ኢሬቻ በዓል የባህል አልባሳቱ በብርቱ ተፈላጊ እየሆኑ የመጡትም ለዚሁ ነው፡፡

እንደ የባህልና ሰላም ተመራማሪ ወሰን (ዶ/ር) ማብራሪያ፣ ኢሬቻም ሆነ ሌሎች የአደባባይ በዓላት በባህርያቸው ዜጎችን በአንድ መድረክ የሚያሰባስቡ በዓላት ናቸው፡፡ ዜጎች በዓሉን ለማክበር በአንድ መድረክ ላይ ሲገናኙ ይበልጥ መገነዛዘብ ይጀምራሉ፡፡ የባህል ልውውጥ ከማድረጋቸውም በላይ ኢትዮጵያ በተለያዩ ባህሎች ያሸበረቀች ውብ ሀገር መሆኗን ይረዳሉ፡፡

የባህልና ሰላም ተመራማሪ ወሰን (ዶ/ር) እንደመስቀልና ኢሬቻ ያሉ በዓደባባይ የሚከበሩ በዓላትን አንድምታ አስመልክተው ባጋሩን ሙያዊ ማብራሪያ የኢትዮጵያውያን የእርስ በእርስ መስተጋብር በስፋት የሚንጸባረቅባቸው በዓላት ናቸው ብለዋል፡፡

ኢሬቻን አድማቂዎቹ የባህል አልባሳት በዚህ ደረጃ ተፈላጊነታቸው እየጨመረ ከመጣ ኢኮኖሚያዊ አበርክቷቸውም ቀላል አይደለም። የሀገር ባህል አልባሳት ከማስተዋወቅ ባለፈ በኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንዲሆኑና በኢሬቻ እና በሌሎች በዓላት የሀገር ባህል ልብሶችን የመልበስ ልማድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል፡፡

ከጨለማ ወደ ብርሃን፣ ከክረምት ወደ ጸዳል ላሻገረ አምላክ ምስጋና የሚሰጥበት የኢሬቻ በዓል ክረምቱን ከበረዶ፣ ከጎርፍና ከውርጭ በሰላም አልፈው ወደ ብርሃን ሽግግር የሚደረግበት ጊዜ በመሆኑ በተለይ የኦሮሞ ህዝብ ፈጣሪውን አንድ ላይ ሰብሰብ በማለት ያመስግናል። በዓሉ ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በዓለም ዙሪያ በሚኖሩ የኦሮሞ ተወላጆች ዘንድ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው። ይህ በዓል ባህላዊ አልባሳትን በመልበስ የጋራ ማንነትን እና ትስስርን ለማጠናከር እንደ መድረክ ያገለግላል።

# ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ክፍት የስራ መደቦች ላይ ሥራ ፈላጊዎችን አወዳድሮ **በቋሚነት** ለመቅጠር ይፈልጋል፡፡

| ተ.ቁ | የሥራ መደቡ መጠሪያ | ደረጃ | ደመወዝ | ጥቅማ ጥቅም | ተፈላጊ የትምህርት ዓይነትና ደረጃ | | አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ | የሚያስፈልገው የሰው ኃይል ብዛት | የሥራ ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | የትምህርት ዓይነት | የትምህርት ደረጃ | | | |
| 1 | ከፍተኛ ትራፊክ ተቆጣጣሪ | XI | 8,474 | የቤት ኪራይ ድጎማ አበል በወር 1250 ብር፣ የሞባይል ስልክ ክፍያ አበል በወር 200 ብር እና የትራንስፖርት አበል በወር 400 ብር | ህግ እና አቻ፣ ትራንስፖርት ስተዲ እና አቻ፣ ማኔጅመንት እና አቻ ፣ አርባን ማኔጅመንት እና አቻ፣ ጅኦግራፊ እና አቻ፣ ቢዝነስ ማኔጅመንት እና አቻ፣ ኢኮኖሚክስ እና አቻ፣ ፐብሊክ ማኔጅመንትና አቻ፣ አርባን ፕላኒግ እና አቻ፣ ሶሺዮሎጂ እና አቻ፣ ሊደርሺፕ እና አቻ፣ ማኔጅመንት እና አቻ፤ ኢጁኬሽናል ማኔጅመንትና አቻ፣ ኢጁኬሽናል ሳይንስና አቻ | የመጀመሪያ ዲግሪ | 4 ዓመት | 100 | በቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች |
| 2 | መካከለኛ ትራፊክ ተቆጣጣሪ | IX | 7,424 | | | የመጀመሪያ ዲግሪ | 2 ዓመት | 90 | በቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች |
| 3 | ጀማሪ ትራፊክ ተቆጣጣሪ | VIII | 6,940 | የቤት ኪራይ ድጎማ አበል በወር 1500 ብር፣ የሞባይል ስልክ ክፍያ አበል በወር 200 ብር እና የትራንስፖርት አበል በወር 400 ብር | | የመጀመሪያ ዲግሪ | 0 ዓመት | 19 | በቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች |
| 4 | ኤክስክዩቲቭ ሴክሬታሪ I | IX | 7,424 | የቤት ኪራይ ድጎማ አበል በወር 1250 ብር እና የማትጊያ አበል በወር 800 ብር | የጽሕፈትና የቢሮ አስተዳደር /ሴክሬተሪያል ሳይንስና ኦፊስ ማኔጅመንት | የኮሌጅ ዲፕሎማ ወይም 10+3 ዲፕሎማ ወይም ሌቭል III | 4 ዓመት | 15 | በዋናው መ/ቤት እና በቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች |
| 5 | ሴክሬታሪ II | VIII | 6,940 | የቤት ኪራይ ድጎማ አበል በወር 1500 ብር እና የማትጊያ አበል በወር 800 ብር | የጽሕፈትና የቢሮ አስተዳደር /ሴክሬተሪያል ሳይንስና ኦፊስ ማኔጅመንት | የኮሌጅ ዲፕሎማ ወይም 10+3 ዲፕሎማ ወይም ሌቭል III | 2 ዓመት | 2 | በዋናው መ/ቤት |
| 6 | ሹፌር I | VI | 6,058 | የቤት ኪራይ ድጎማ አበል በወር 1500 ብር | የቀለም ትምህርት | 12ኛ/10ኛ ክፍል ያጠናቀቀ እና 3ኛ መንጃ ፈቃድ ያለው | 0 ዓመት | 5 | በዋናው መ/ቤት እና በቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች |

**ማሳሰቢያ**

- አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ 10 /አስር/ ተከታታይ የሥራ ቀናቶች ብቻ ማመልከት ይችላሉ፡፡
- የምዝገባ ቦታና ስዓት ከ 22 ወደ መገናኛ በሚወስደው መንገድ መክሊት ህንፃ 10ኛ ፎቅ የሰው ኃይል አስተዳዳር ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 06 በሥራ ሰዓት ጠዋት ከ2፡30 - 6፡30 ሰዓት ከሰዓት ከ7፡30 - 11፡30 ሰዓት ድረስ
- በምዝገባ ወቅት አመልካቾች ዋናውን የትምህርት ማስረጃ ኦረጅናል ከማይመለስ ፎቶ ኮፒ ጋር ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት የሚቀርብ የሥራ ልምድ ማስረጃ የሥራ ግብር የተከፈለበት መሆኑን የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡
- ከደረጃ III እስከ ደረጃ V የትምህርት ደረጃ ያላቸው አመልካቾች የሙያ ምዘና የብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ (COC) ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- የሥራ ቦታ አዲስ አበባ በዋናው መ/ቤት፣ በቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች

**ስልክ ቁጥር 0913045587**

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን**

ጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል
Gullele Botanic Garden

## እንኳን ለ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ የሚለው፤ ጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል



ሊያሳካቸው ከተቋቋመባቸው ዋና ዋና ዓላማዎች አንዱ በሆነው የምርምር ዘርፍ የዕፅዋት ብዝሀ-ህይወት ሀብታችንን ለመጠበቅ ብሎም ለሚቀጥለው ትውልድ ማስተላለፍ እንዲቻል በተፈጥሮ ወይም በማህበራዊ ሳይንስ ጥናት ከመስራት ጎን ለጎን በዘርፉ የተሰማሩ ሌሎች ባለድርሻ አካላትና ተመራማሪዎችን በመሳብ ላይ ይገኛል፡፡

ማዕከሉ የሀገር በቀል ዕፅዋትን በተለይ ለመጥፋት የተቃረቡትን በማስቀደም በመንከባከብና በማልማት ብሎም የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማስፋት ለአረንጓዴ ስፍራዎች ማስዋቢያነት ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ ረገድም ጉልህ ድርሻውን እየተወጣ ይገኛል፡፡

ወደ ጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል ጎራ ይበሉ እያልን የኢሬቻ በዓል የሰላም፣ የደስታና የፍቅር እንዲሆንላችሁ እንመኛለን፡፡፡

# መልካም በዓል!

## ጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል

**አድራሻ፡- ከአዲሱ ገበያ ወደ ዊንጌት በሚወስደው መንገድ ከሸጎሌ ቀለበት በስተቀኝ፡፡**
**ዕፅዋትን ይመልከቱ ንጹህ አየር ይተንፍሱ!**

WPDAA

## እንኳን ለ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ!!

ኤጀንሲያችን ለተገልጋዮች ተገቢው አገልግሎት በፍትሐዊ መንገድ ለመስጠት ከመቼውም ጊዜ በላይ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡

በተያዘው በጀት ዓመትም የከተማችንን ህብረተሰብ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ሲሆን ለአብነትም የመስሪያ ቦታዎችን በማልማት፣ በመቆጣጠር፣ በማስተዳደር፣ በፍትሐዊ መንገድ በማስተላፍና ለታለመላቸው ዓለማ እንዲውሉ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ስለሆነም ከዚህ ቀደም ለኤጀንሲያችን ስኬት አስተዋፅኦ ስታበረክቱ ለነበራችሁ አካላት በሙሉ ምስጋና እያቀረብኩኝ፣ ለወደፊቱም ከጎናችን ሆናችሁ እንደምታግዙን በመተማመን፣ ወንድማማችነት እና እህትማማችነት ለሚጠናከርበት፣ የሰላም እሴት ለሚገነባበት መተሳሰብ ለሚዳብርበትና ፈጣሪ ለሚመሰገንበት የኢሬቻ በዓል እንኳን በሰላም አደረሰን!! አደረሳችሁ!!

ወ/ሮ አይዳ አወል
የአዲስ አበባ የመስሪያ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር

ኢሬቻ ለሀገር ማንሰራራት!!





የጉለሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር
Gullele Subcity Adminstration

## እንኳን ለ2018 ዓ.ም
## የኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ!!



አቶ ወልዴ ወገሴ
የጉለሌ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈጻሚ

ለመላው የኦሮሞ ህዝብና ለኢትዮጵያውያን እንኳን ለኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ የሚለው የጉለሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር፤ የኢሬቻ በዓል በኦሮሞ ማህበረሰብ ዘንድ ለዘመናት ሲከበር መቆየቱን የታሪክ ምሁራን ይናገራሉ። ኢሬቻ ማመስገን ሲሆን፤ ከክረምት ወደ በጋ ስላሸጋገርከኝ አመሰግናለሁ፤ በማለት ፈጣሪ የሚመሰገንበት የአብሮነትና የወንድማማችነት በዓል ነው።

በጉለሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ኢሬቻ ሲከበር ብዝሀ ኢትዮጵያዊነትን ከፍ በሚያደርግና ባህላዊ ቱውፊቱን በመጠበቅ በሰላም፣ በአብሮነትና በወንድማማችነት መከባበርን መሰረት ያደረገ የተለያዩ ባህሎች መገኛ የኩሩ ህዝብ ታላቅ ሀገር መሆኗን ለአለም የምናሳውቅበት ነው።

በዓሉን በጋራ ስናከብር በሁለንተናዊ ሀገራዊ ለውጥ ውስጥ በመሆን በተግባር የሚታዩ ፕሮጀክቶች የተሰሩበት፣ ህዝባዊ ተጠቃሚነት የተረጋገጠበትና ድህነትን ተሻጋሪ ለአፍሪካ ሀገራት ዳግም ተምሳሌት የሆንበት፣ የህዳሴ ግድብ መጠናቀቅ ስኬትና ተድላ ውስጥ ሆነን ነው፡፡

በዓሉን በመከባበር፣ በወንድማማችነት፣ አብሮነታችንን በሚያጠናክር መልኩ በጋራ እንድታሳልፉ እየጠየቅኩ መልካም በዓል እንዲሆንላችሁ እመኛለሁ!!



## መልካም የኢሬቻ በዓል!!





ከነማ ፋርማሲዎች ድርጅት
KENEMA PHARMACIES ENTERPRISE

ኢሬቻ ለኢትዮጵያ ማንሰራራት!



## እንኳን ለ2018 ዓ.ም
## የኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ

ለከነማ ፋርማሲዎች ድርጅት አመራሮች፣ ሰራተኞች እና ተገልጋዮች እንኳን 2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ እያልን ድርጅታችን ባለፉት 42 ዓመታት ለከተማችን እና ለአካባቢው ነዋሪዎች የመድሐኒትና የህክምና መገልገያ መሳሪያዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ላይ ይገኛል፡፡

በተለይም ድርጅታችን በ2018 ዓ.ም "ከነማ በአዲስ ጎዳና" በሚል መርህ የአዲስ ምዕራፍ የቃል-ኪዳን ስምምነት በመፈጸም ከተማችንንና ህዝባችንን የሚመጥን አገልግሎት ለመስጠት አገልግሎታችንን በቴክኖሎጂ /ERP/ በማዘመን የመድሐኒት አቅርቦት ችግርን በዘላቂነት ለመፍታት የጅምላ ንግድ በመጀመርና ሞዴል ፋርማሲ ቤቶችን በመክፈት ህዝባችንን ለማገልገል ዝግጅታችንን አጠናቀን ወደ ተግባር ገብተናል።

**አቶ ሰይፈ ደምሴ**
**የከነማ ፋርማሲዎች ድርጅት**
**ዋና ስራ አስኪያጅ**



አቶ መስፍን አሰፋ
የአዲስ አበባ ንግድ ሥራዎች ድርጅት
ዋና ዳይሬክተር



BTE

## እንኳን ለ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ! አደረሰን! የሚለው የአዲስ አበባ ንግድ ሥራዎች ድርጅት

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በደንብ ቁጥር 152/2015 ዓ.ም የተቋቋመ መንግስታዊ የልማት ድርጅት ሲሆን የተለያዩ ምርቶችን በከተማዋ ለሚገኙ የመሠረታዊ ሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራት፣ ለአገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና ለሸማቹ ህብረተሰብ በተመጣጣኝ ዋጋ በማሰራጨት ገበያ ማረጋጋትን ተልዕኮው አድርጎ እየሰራ መሆኑን በታላቅ ደስታ ይገልጻል፡፡

ድርጅቱ ለህዳሴ ግድብ ምርቃትም እንኳን ደስ አላችሁ እያለ፤ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች፡- የግብርና እና ኢንዱስትሪ ምርቶችን ማቅረብ፣ የምርት ሽያጭና ስርጭት፣ የንፁህ ጤፍ እንጀራ፣ የእንጀራ ድርቆሽ፣ ንፁህ ጤፍ ዱቄት፣ የዳቦ ምርት፣ የተለያዩ የባልትና ውጤቶችን ማዘጋጀት መሆኑን እየገለፀ በዓሉ የሰላምና የጤና እንዲሆን ልባዊ ምኞቱን ይገልጻል፡፡

# መልካም በዓል!
**የአዲስ አበባ ንግድ ሥራዎች ድርጅት!**

አድራሻ፡-
ዋና መስሪያ ቤት ፒያሳ እሪ በከንቱ፣ ጀሞ 1፣ ለሚ ኩራ ወረዳ 2 እና 4፣
ጉለሌ እንጦጦ ፓርክ፣ አቃቂ ቃሊቲ ገበያ ማዕከል



የዓድዋ
ድል መታሰቢያ
ADWA
VICTORY MEMORIAL

## እንኳን ለ2018 የኢሬቻ በዓል በሠላም አደረሳችሁ!

“ኢሬቻ ለሀገር ማንሰራራት” በሚል መሪ ቃል ለሚከበረዉና በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ በታላቅ ጉጉት ለሚጠበቀዉ የዘንድሮ ኢሬቻ በዓል እንኳን በሰላም አደረሳችሁ እያልኩ የዘንድሮው የኢሬቻ በዓል እንደ ሁልጊዜው የኦሮሞ ሕዝብ ባሕል፣ ወግና መልካም እሴቶች ሁሉ በውበትና በድምቀት ጎልተው የሚታዩበት የሰላም፣ የፍቅር እና የደስታ በዓል እንዲሆን መልካም ምኞቴን እየገለፅኩ በድጋሚ እንኳን አደረሳችሁ እንኳን አደረሰን እላለሁ።

**ግሩም ግርማ**
**የዓድዋ ድል መታሰቢያ ዋና ዳይሬክተር**






## እንኳን ለ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ!

በዓሉ የሠላም፣ የፍቅር፣ የመተሳሰብ እና የብልፅግና እንዲሁም እጅ ለእጅ ተያይዘን ከተማችን አዲስ አበባን የምናበለጽግበትና የምናዘምንበት እንዲሆንልን እመኛለሁ፡፡

ውድ የከተማችን ነዋሪዎች ተቋማችን የአዲስ አበባ ከተማ ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የነዋሪውን ፍላጎት ማዕከል ያደረጉ አገልግሎቶችን ማለትም በከተማችን ለሚሠሩ ግንባታዎች ፈቃድ መስጠት፣ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎችና ባለሙያዎች ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት መስጠት፣ በከተማው መዋቅራዊ ፕላን መሠረት በሚገነቡ ግንባታዎች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣ ሕንፃዎች ለተፈቀደላቸው ዓላማ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ የመጠቀሚያ ፈቃድ መስጠት፣ በከተማችን የሚሠሩ የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎች የግንባታ ቅንጅት፣ ፈቃድና ክትትል ዙርያ የሚሠሩ ሥራዎች እንዲሁም የውጭ ማስታወቂያ ፈቃድና ቁጥጥር አገልግሎት አሠጣጥ ሥራዎችን በማዕከልና በየደረጃው በሁሉም ክፍለ ከተሞች በሚሰጠው የአገልግሎት እርከን መሠረት ለውድ ደንበኞቻችን እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ በቀጣይም አገልግሎቱን ይበልጥ አጠናክረን የምናገለግላችሁ መሆኑን እየገለጽን በድጋሚ በዓሉ የሠላም፣ የፍቅርና የደስታ እንዲሆንላችሁ ከልብ እመኛለሁ፡፡

ኢ/ር ሕይወት ሳሙኤል
በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር!

# የመሻገር ... ከገጽ 1 የዞረ

ኢሬቻ በአዲስ አበባና ቢሾፍቱ ከተሞች በታላቅ ድምቀት ይከበራል። በኢሬቻ ሆረ ፊንፊኔ እና ሆረ አርሰዴ በዓላት በተለያዩ የሀገሪቱ ማዕዘናት የሚኖሩ የኦሮሞና የተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች፣ በውጭ ሀገራት ጭምር የሚኖሩ ሰዎች ተሰባስበው "መሬሆ ... መሬሆ..." እያሉ ፈጣሪን የሚያመሰግኑ ዜማዎችን እየዘመሩ፣ ሳርና አደይ አበባ በመያዝ ወደ መልካ (ወንዝ) በመውረድ ፈጣሪን ያመሰግናሉ። ሴቶችም ሲንቄ ይዘው፣ ጫጩ ደርበው፣ ጨሌ አድርገው፣ ለምለም ሳር ይዘው፣ በባህላዊ አልባሳት አጊጠው ከሌሎች የበዓሉ ተሳታፊዎችና አባገዳዎች ፊት በመሆን ይሄዳሉ፡፡



ፎቶ-ከገፀድር

በርካታ ህዝብ በመሰባሰብ የሚያከብረው የሆረ ፊንፊኔ ኢሬቻ በዓል በከፊል

አቶ ከበደ አበራ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 አስኮ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ነዋሪ ናቸው፡፡ የኢሬቻ በዓል በጉጉት የሚጠብቁት በዓል እንደሆነና በየዓመቱ በሚከናወኑት የሆረ ፊንፊኔና ሆረ አርሰዴ ኢሬቻ በዓላት እንደሚሳተፉ ይናገራሉ፡፡ ብዙውን ጊዜም ከቤተሰብና ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ተመሳሳይ ቀለምና ዲዛይን ያላቸው ባህላዊ አልባሳት በመልበስ፣ ተውበውና ደምቀው፣ እየጨፈሩና እየተጫወቱ በደስታ ያከብራሉ፡፡

ኢሬቻ አስቸጋሪው የክረምት ወራት አልፈው በብራ፣ ወንዞች በሚጎድሉበትና ሰማዩ በሚጠራበት ወቅት የሚከናወን በዓል ነው፡፡ ሩቅ ቦታ የሚኖር፣ ሳይገናኝ የቆየ ቤተሰብ፣ ጓደኛና ወዳጅ ዘመድ መልካ (ወንዝ) ላይ የሚገናኙበትና ለፈጣሪ ምስጋና የሚያቀርቡበት ትልቅ ደስታን የሚፈጥር በዓል እንደሆነ አቶ ከበደ ይገልጻሉ፡፡

ኢሬቻ ሰላም፣ ፍቅር፣ አንድነትና የህዝቦች አብሮነት የሚታይበት በዓል ነው፡፡ የኦሮሞ ህዝብ ከዓመት ወደ ዓመት ላሸጋገረው ፈጣሪ ምስጋና የሚቀርብበት፣ ያለ እምነት፣ ዘር፣ ፆታና ሌሎች ልዩነቶች ሁሉም የሚሳተፍበትና የሚገናኝበት በዓል ነው፡፡ የተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦችም የሚሳተፉበትና ወንድማማችነትና እህትማማችነትም የሚታይበት እንደሆነ አቶ ከበደ ያነሳሉ፡፡

"ኢትዮጵያውያን አውጥተን ብንጠቀማቸው ለሰላም፣ እርቅና ለልማት ተምሳሌት የሚሆኑ ባህሎች አሉን" የሚሉት አቶ ከበደ፣ በኢሬቻ በተለያዩ አካባቢ የሚኖሩ የኦሮሞ ማህበረሰብ፣ የተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በፍቅርና በአንድነት በመሰባሰብ የሚያከብሩት በዓል መሆኑ ብዙ ቁምነገር ያስተምራል። አንድነት፣ መተባበርና ፍቅር ሲኖር የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ከኢትዮጵያ አልፎ ለአፍሪካ ኩራት የሆነው ታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ሁነኛ ማሳያ ነው ብለዋል፡፡

አንድነት አሸናፊነት ነው፡፡ አያት ቅድመ አያቶቻችን ኢትዮጵያን ሊወር የመጣን ጠላት በአንድነት በመቆም አሸንፈዋል። የአሁኑ ትውልድ የህዳሴ ግድብን በመገንባት ዳግማዊ ዓድዋን ሰርቷል፡፡ በቀጣይም የጋራ የሚያደርጉንን ባህሎች በማክበርና በመጠበቅ እንዲሁም ከእነዚህ ትምህርት በመውሰድ የኢትዮጵያን አንድነት ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡ የሚያቀራርቡንን እሴቶች በማውጣትና ለወጣቱ ትውልድ በማስተማር፣ በአንድነትና በፍቅር በመቆም በልማቱም ሆነ በሌላው መስክ አሸናፊ በመሆን ሀገርን ወደተሻለ ደረጃ ማድረስ ይቻላል፡፡ ከዚህ አኳያ እያንዳንዱ ጠንክሮ መስራትንና ሰላምን በማስቀደም መንቀሳቀስ እንዳለበት አቶ ከበደ ያስረዳሉ፡፡

የኢሬቻ በዓልን ከሚናፍቁና በየዓመቱ ተሳትፎ ከሚያደርጉት መካከል ሌላኛው የሳንሱሲ አካባቢ ነዋሪው አቶ ሽመልስ በቀለ ናቸው፡፡ በዓሉን ከቤተሰብና ጓደኞቻቸው ጋር በመሆን በባህል አልባሳት አምረውና ደምቀው ያከብሩታል፡፡ በርካታ ሰዎች ከተለያየ አካባቢ የሚሰባሰቡበት በመሆኑ በቦታ ርቀት ለረጅም ጊዜ ሳያገኙአቸው የቆዩ ጓደኞቻቸው ጋር የሚገናኙበት፣ ከአዳዲስ ሰዎች ጋርም የሚተዋወቁበትና ወዳጅነት የሚመሰርቱበት፣ በጋራ ለፈጣሪ ምስጋና የሚቀርብበት በዓል መሆኑም የተለየ ደስታ የሚፈጥርባቸውና በጉጉት እንዲጠብቁት እንደሚያደርጋቸው ይናገራሉ፡፡

ኢሬቻ የኦሮሞ ህዝብ ሰላምን፣ ፍቅርንና አብሮነትን የሚገልፅበት እንደሆነ የሚያነሱት አቶ ከበደ፣ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የራሳቸው የሆነ የማንነት መገለጫዎችን ማወቅ፣ ማክበርና ማድነቅ ቢቻል ፍቅር፣ አንድነትና አብሮነት እየተጠናከረ ይሄዳል፡፡ የሀገሪቷን መልካም ገፅታ በመገንባት፣ የተለያዩ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ያስገኛል፡፡

## ኢሬቻና ተምሳሌትነቱ

ኢሬቻ በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ እንደዘመን መለወጫ የሚታይ በዓል ነው፡፡ የኦሮሞ አባ ገዳዎች ህብረት ዋና ጸሀፊ እና የቱለማ አባ ገዳ ጎበና ሆላ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት፤ ኢሬቻ የኦሮሞ ህዝብ ከጨለማ ወደ ብርሃን በሚሸጋገርበት፤ የክረምቱ ጭጋግና ደመና ተገፍፎ፣ ሞልተው የነበሩት ወንዞችና ጅረቶች ጎድለው ሰዎች መገናኘት በሚችሉበት ወቅት የሚከበር እና ለፈጣሪ ምስጋና የሚቀርብበት በዓል ነው፡፡ በክረምት ከሚኖር ብርድ፣ ጎርፍ፣ የመሬት መንሸራተትና ሌሎች አደጋዎች ታልፎ ወደ ብራ (ፀደይ) ላሸጋገረው፣ መሬቱ አረንጓዴ ሸማ በሚለብስበት፣ አበባ በሚያብብበት፣ አዝርዕት በሚያሸቱበት ወቅት ወደ መልካ (ወንዝ) በመውረድ ለፈጣሪ ምስጋና እና ልመና በማቅረብ በታላቅ ድምቀት የሚከበር ነው፡፡

"ከድቅድቅ ጨለማ ወደ ብርሃን፤ ከሌሊት ወደ ቀን፣ ከችግር ወደ ተስፋ ያሸጋገርከን፣ ከድፍርሱ ወደ ንጹህ ውሃ ያበቃኸን፣ አዝርዕትን ያበቅልክ፣ አበባዎች እንዲያብቡ ያደረክ፣ ያበበው እንዲያፈራ ተስፋ የሰጠኸን ፈጣሪ (ዋቃ) ምስጋና ይገባሃል" በማለት የሚመሰገንበት በዓል እንደሆነ የሚናገሩት ደግሞ በወለጋ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋዎችና ጥናት ተቋም ትምህርት ክፍል የተግባራዊ ሥነ ልሳን (የፎክሎር) መምህርና ተመራማሪ ግርማ በቀለ (ዶ/ር) ናቸው፡፡

ክረምት ወንዞች ከአፍ እስከ ገደፋቸው የሚሞሉበት፣ ድልድይ በውሃ የሚወሰድበትና የሚፈርስበት፣ ወዲህና ወዲያ ማዶ ያለ ወዳጅ ዘመድ የማይገናኝበት፣ ሀይለኛ ውሽንፍር፣ ጨለማ እንዲሁም ችግር ያለበት ወቅት ነው። ታዲያ ኢሬቻ ሲመጣ ዝናቡ በርቶ፣ ወንዞች ጎድለው፣ ጭጋጋማው አየር ተገፍፎ፣ ተለያይቶ የቆየው የሚገናኝበት፣ የሚጠያየቅበት፣ የሚመካከርበት፣ ወደ አንድነት የሚመጣበት፣ ተስፋ የሚሰነቅበት፣ ሰላምና ጤናን የሚመኝበት፣ መጪው ትውልድ በባህሉ የሚከናወነውን ወግና ስርዓት የሚማርበትን እድል እንደሚፈጠር ግርማ (ዶ/ር) ያነሳሉ፡፡

በኢሬቻ የኦሮሞ ህዝብ ከልጅ እስከ አዋቂ በመሰባሰብ፣ 'መሬሆ ... መሬሆ ' እያለ በእጁ እርጥብ ሳርና አበባ በመያዝ ፈጣሪን እያመሰገነ ወደ ወንዝ ይወርዳል። ግርማ (ዶ/ር) እንደሚገልፁት፤ ኢሬቻ ሰላም፣ ፍቅር፣ ሀይል፣ አንድነት፣ መተባበር፣ እርቅ የሚታይበት በዓል ነው። በኢሬቻ ሰላም እንዲመጣና ያበበው እንዲያፈራ ለፈጣሪ ልመና ይቀርባል። የሚለመነውም በምድር ላይ ለሚኖር የሰው ልጅና ፍጥረታት ሁሉ ነው፡፡

መከፋፈል፣ መለያየትና ጥላቻ አይደገፍም፡፡ የኦሮሞ ህዝብ የራሱን ብቻ ሳይሆን ሌሎችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች አቅፎ በመከባበርና በመደጋገፍ ይኖራል፤ በዓላት በሰላም እንዲከበሩ ያደርጋል፤ ያከብራል ይላሉ ግርማ (ዶ/ር)፡፡

እንደሀገርም ባለፉት ዓመታት ሰላም ለማምጣት ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ በፌዴራል መንግስትና ህወሓት መካከል የተፈረመው የሰላም ስምምነት አንጻራዊ ሰላም የተፈጠረበትን ሁኔታ ማንሳት ይቻላል። ሰላም፣ መተባበር፣ አንድነት በመኖሩና ከልብ በመሰራቱ በተለያዩ የልማት መስኮችም በተጨባጭ የሚታዩና ተስፋ ሰጪ ውጤቶች መገኘታቸውን ከሰላም አኳያ ያነሳሉ፡፡

ኢሬቻ የእርቅ ምልክትም ነው። የተጣላና ያኮረፈ ሰው ወደ ኢሬቻ አይሄድም፡፡ ምክንያቱም በኢሬቻ ወንዙ ሳይቀር ከድፍርስ ወደ ንጹህ መልክ የሚቀየርበት ስለሆነ፤ ሰውም በልቡ ቂም ቋጥሮ፣ የሻከረ ሀሳብ ይዞ ንፁህ ወደሆነው ወንዝ አይሄድም፤ በንፁህ ልብ ወደ ንጹህ ውሃ ነው የሚሄደው፡፡ ቂም ተይዞ ተስፋ አይሰነቅም፤ አንድነትም አይመሰረትም። የተጣሉ ወይም የተኳረፉ ወገኖች ሲታረቁ ባዶ እጃቸውን ሳይሆን እርጥብ ሳር ይዘው ወደ ወንዙ (መልካው) በመሄድ እንደሚያከብሩት ግርማ (ዶ/ር) ያስረዳሉ፡፡

ኢሬቻ ፍቅር የሚታይበትም በዓል ነው። ሰዎች በፍቅር ተሰባስበው፤ በመከባበር፣ በመደጋገፍና በአንድነት ፈጣሪያቸውን ይለምናሉ፡፡ ይህ የኢሬቻ እሴትም ኢትዮጵያ ወደ ልማት፣ ዘላቂ ሰላምና ብልፅግና ለመሸጋገር የምታደርገው ጥረት ተምሳሌት መሆን እንደሚችል ግርማ (ዶ/ር) ያነሳሉ። "ኢሬቻ የሰላም፣ የምስጋና፣ የፍቅር፣ የአንድነት ተምሳሌት ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን የኢሬቻንም ሆነ ሌሎች በዓላትን እሴቶች መረዳትና ማክበር ቢችሉ ችግርም ሆነ ጦርነት አይኖርም፤ አንድነታችን ይጠናከራል፡፡ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ባህልና እሴቶች አስተማሪ ናቸው።" ይላሉ፡፡

ኢሬቻ ከጨለማ ወደ ብርሃንና ተስፋ የመሸጋገር ተምሳሌት ነው። ኢትዮጵያም ከድህነት ለመውጣት፤ ልማትና ብልፅግናን ለማምጣት በኢሬቻ የሚታየው የአንድነት እሴቶችን መያዝ ያስፈልጋታል፡፡ እዚህ ላይ አንድነት ሲባል አንድ አይነትነት ማለት ሳይሆን የተለያየ እምነት፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ የፖለቲካ አመለካከትና ክህሎት ያላቸው ሰዎች ለአንድ የጋራ ጉዳይ በጋራ መቆም ነው፡፡ እንደ ሀገርም ኢትዮጵያውያን በአንድነት ሲቆሙና ሲተባበሩ ምን ማሳካት እንደሚችሉ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የሚሰጠው ትምህርት ትልቅ እንደሆነ ግርማ (ዶ/ር) ያስረዳሉ። በዓባይ ወንዝ ላይ ልማት የማካሄድ የዘመናት ጥያቄ ምላሽ እንዲያገኝ ኢትዮጵያውያን ከዳር እስከ ዳር፣ ከሊቅ

ወደ ገጽ 40 ዞሯል

# “ዜጎች ላይ ምሬት የሚፈጥሩ አሰራሮችን ማስተካከል ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው”

**የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አቶ ዮናስ አለማየሁ**

- **አዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት የስማርት ከተማነት ጉዞን እንደሚያሳልጥ ተገልጿል**

**በሄለን ጥላሁን**

የዘመነና የተቀላጠፈ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት አንዱ የስልጡን ከተማ (ስማርት ሲቲ) መለያ መስፈርት ነው። አገልግሎት አሰጣጣቸውን ማዘመንና ማቀላጠፍ የቻሉ ከተሞች ያስቀመጡትን ርዕይ ለማሳካት አግዟቸዋል፡፡ በመዲናችን አዲስ አበባ በተግባር ሥራ የጀመረው አዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት እንደ ሀገር ለተያዘው የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓትን የማዘመን ውጥን ወሳኝ ስንቅ ይሆናል፡፡

ዝግጅት ክፍላችን በቦታው ተገኝቶ ባደረገው ምልከታ በሰበሰበው መረጃ መሰረት፤ በዚህ ተቋም ሥራ ከመጀመሩ አስቀድሞ፤ የሀገር ፍቅር ስሜትን በመላበስ ሙያተኞች ዩኒፎርም ልብሳቸውን እንደለበሱ የኢትዮጵያ ህዝብን ብሔራዊ መዝሙር በመዘመር፣ ሠንደቅ ዓላማ የመስቀል ተግባርን በመደበኛነት ሁሌም ይፈፅማሉ፡፡ ከዚያም በሀገር ፍቅር መንፈስ፣ በብርቱ የሥራ ፍላጎት፣ በአገልጋይነት ወኔ ወደ ሥራቸው ይሰማራሉ፡፡ በግብዓትና በቴክኖሎጂ በተደራጀው የሥራ ክፍላቸው ገብተው፣ ከወንበራቸው ይሰየማሉ። ኮምፒዩተሮቻቸውን ከፍተውም ተገልጋዮችን እንዳመጣጣቸው በክብር ያስተናግዳሉ፡፡

አገልግሎቱ አስፈላጊ የሆኑ የቴክኖሎጂ ግብዓቶች ተሞልተውለት፣ ለተገልጋይና ሠራተኛ ምቹ የሥራ አካባቢ ተመቻችቶለት እንዲሁም ብቁ የሰው ሃይል ተደራጅቶለት ጳጉሜን 5 ቀን 2017 ዓ.ም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አማካኝነት ስራውን በይፋ ጀምሯል፡፡ ስለሚሰጡ አገልግሎቶች ማብራሪያ እና የተሟላ መረጃ የሚሰጠው የኤሌክትሮኒክስ የወረፋ መያዣ ወደየትኛው መስኮት መሄድ እንዳለብዎት ይጠቁምዎታል፡፡ ይህ ግር ካለዎት ደግሞ፤ አጋዥ የሠው ኃይል የፈለጉትን መረጃና ማብራሪያ ይሠጥዎታል፡፡

የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አቶ ዮናስ አለማየሁ ለዝግጅት ክፍላችን እንዳስረዱት፣ ዘመናዊ የመንግስት አገልግሎትን ለመገንባት ጠንካራና አዲስ የስራ ባህል መከተል ያስፈልጋል። አዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት 13 ተቋማትን በማካተት፣ 107 የዲጂታል አገልግሎቶችን በአንድ ማዕከል እየሰጠ ይገኛል።

## አዲስ መሶብ ምንድ ነው?

አዲስ መሶብ የአንድ መስኮት አገልግሎት በአንድ ጣራ ስር የተለያዩ የመንግስት አገልግሎቶችን በማጣመርና የዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የሚሰጥ አገልግሎት ስለመሆኑ ዋና ዳይሬክተሩ አቶ ዮናስ ተናግረዋል። “የአሠራር ስርዓቱ ዜጎች የዲጂታል አማራጮችን በመጠቀም በቀላሉ የተለያዩ የተቋማትን አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችል ነው፡፡ በአገልግሎት አሰጣጥ ረገድ በተለይ ዜጎች ላይ ምሬት የሚፈጥሩ አሰራሮችን ፈትሾ ማስተካከል ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው። ለዚህ ቁርጠኝነታችን አንዱ ማሳያ የሆነው የአዲስ መሶብ የአንድ መስኮት አገልግሎት ደግሞ የመዲናዋን ነዋሪ ችግር የሚቀርፍ ነው፡፡ በተለይም ባለጉዳዮች ወደተለያዩ ቢሮዎች የሚያደርጉትን ምልልስ፣ ረጅም የወረፋ ጥበቃ እና ከወረቀት ጋር ተዛማጅ የሆኑ ስራዎችን የሚያስቀር ነው” ብለዋል።

በአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ውስጥ 13 ተቋማት ማለትም ንግድ ቢሮ፣ ገቢዎች ቢሮ፣ ስራ እና ክህሎት ቢሮ፣ መሬት ልማት እና አስተዳደር ቢሮ፣ ቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ፣ ፕላን እና ልማት ቢሮ፣ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ፣ የሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ፣ የግንባታ ፈቃድ እና ቁጥጥር ባለስልጣን፣ የቤቶች ኮርፖሬሽን፣ የኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ የአሽከርካሪ እና ተሽከርካሪ ፈቃድ እና ቁጥጥር ባለስልጣን፣ የትራፊክ ማናጅመንት ባለስልጣን ተካትተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከክፍያ አኳያ የሚያግዙ እንደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ስኬት ባንክ፣ የኢትዮ ቴሌኮም፣ የኢትዮጵያ



ፎቶ-በገነት ወንድሙ
የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አቶ ዮናስ አለማየሁ

ፖስታ አገልግሎት፣ የብሔራዊ መታወቂያ እንዲሁም የሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ አገልግሎት እንደሚገኙበት አቶ ዮናስ ገልፀዋል፡፡

ይህ አገልግሎት የአዲስ አበባን የስማርት ከተማነት ጉዞ የሚያሳልጥ ወይም የሚያግዝ ነው፡፡ “የአዲስ አበባ ስማርት ሲቲ ዕቅድ” ጥናት ተጠንቶ ወደ ትግበራ ከገባ ሰነባብቷል፡፡ ይህ ዕቅድ በውስጡ ካካተታቸው የስማርት ሲቲ ስድስት ዋና ዋና ምሰሶዎች መካከል አንዱ ስማርት

ወደ ገጽ 40 ዞሯል

## ምን ልርዳዎ?

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአዲስ መሶብ ከሚሰጡ 13 አገልግሎቶች አንዱ ንግድ ቢሮ ነው። በአዲስ ሞሶብ የሚሰጠው አገልግሎት በንዑስ ተግባራት የተቀመጠ ነው። እነዚህም ፡-**
**የተጣመሩ አገልግሎቶች**

1. አዲስ የንግድ ምዝገባ እና አዲስ የንግድ ሥራ ፈቃድ፣ (በአንድ ላይ)
2. አዲስ የንግድ ምዝገባ፣ አዲስ የንግድ ሥራ ፈቃድ እና የንግድ ስም ምዝገባ (ሦስቱን በአንድ ላይ)

### የንግድ ምዝገባ

1. አዲስ የንግድ ምዝገባ፣
2. የንግድ ምዝገባ ማሻሻያ፣
3. የንግድ ምዝገባ ምትክ፣
4. የንግድ ምዝገባ ስረዛ፣

### የንግድ ሥራ ፈቃድ

1. አዲስ የንግድ ሥራ ፈቃድ፣
2. የንግድ ሥራ ፈቃድ ማሻሻያ፣
3. የንግድ ሥራ ፈቃድ እድሳት፣
4. የንግድ ሥራ ፈቃድ ምትክ፣
5. የንግድ ሥራ ፈቃድ ስረዛ፣

### የንግድ ስም

1. የንግድ ስም ምዝገባ፣
2. የንግድ ስም ማሻሻያ፣
3. የንግድ ስም ምትክ፣
4. የንግድ ስም ስረዛ ናቸው፡፡

**ምንጭ፡- አዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት**

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ የሚቀርብ

# የፌዴራል ገቢ ግብር አዳዲስ ይዘቶችና ማሻሻያዎች

## ክፍል ሁለት

በደርብ ምሳየ (ዐቃቤ ሕግ)

**ባለፈው ሳምንት ዕትም የገቢ ግብር ምንነትና ዓላማ እንዲሁም የፌዴራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 1398/2017 ያመጣቸውን አዳዲስ ይዘቶች አስነብበናችኋል። ቀሪውን ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅተናል**



- **ገቢን ማጣመር ወይም በአንድነት ማጠቃለል**

አዋጅ ቁጥር 979/2008 ገቢ የሚጣመረው በተመሳሳይ ሰንጠረዥ ውስጥ የሚገኝ ገቢ ሲሆን ብቻ ነበር። በዚህ አዋጅ መሰረት አንድ ግብር ከፋይ ግለሰብ ከሁለም ሰንጠረዦች የሚያገኛቸው ገቢዎች በዜሮ ምጣኔ ቅንፍ ስር የሚወድቁ ገቢዎች ከሆኑ ከግብር ነፃ የሚሆንበት ሁኔታ ሲፈጠር ነበር። ይህ ደግሞ የግብር ፍትሐዊነት መርሕን የሚጥስና የግብር መሰረትን የሚሸረሽር ነበር። ይህን ችግር የሚፈታ በፌዴራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 1395/2017 በሰንጠረዥ 'ሀ, ለ, ሐ" ውስጥ ሆነው በዜሮ ምጣኔ የሚያርፉትን ገቢዎች በማጣመር ወይም በአንድነት በማጠቃለል እንዲከፍል የሚደረግበት ድንጋጌ ተካትቷል። በዜሮ ምጣኔ ከግብር ነፃ የሚፈቀደው አንድ ጊዜ ብቻ ነው።

### ከኢትዮጵያ ውጭ የሚደረግ የሀብት ዝውውር ላይ ግብር ማስከፈል

የውጭ ሀገር ኩባንያዎች በኢትዮጵያ ውስጥ አክስዮን በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ የሚከፈለውን ግብር ላለመክፈል ኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ስራ የሚሰራው ኩባንያ ባለቤት የሆነው ኩባንያ የታክስ ጫና በሌለባቸው ሀገራት በማቋቋም ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ኩባንያ አክስዮን ሳይነካ በውጭ ሀገር ያቋቋሙትን አክስዮን ብቻ በመሸጥ ከኢትዮጵያ ታክስ ይሸሻል።

በመሆኑም በዚህ ዓይነት አደረጃጀት ታክስ ላለመክፈል የሚደረገውን ጥረት ለመከላከል አክሲዮኑ የተላለፈው በውጭ ሀገር የሚገኝ ድርጅት ካለው ሀብት ውስጥ 50% በላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ከሆነ የዚህ ድርጅት አክስዮን እንደማስተላለፍ ተቆጥሮ ግብር እንዲከፍልበት ማድረግ የሚያስችል ድንጋጌዎች ተካትተዋል።

### ግብርን አስቀድሞ ማስከፈል

አንዳንድ ግብር ከፋዮች በግብር ዓመቱ የሚያገኙትን ገቢ በተለያየ መንገድ በማባከን፣ መክፈል የሚገባቸውን ግብር እንዲከፍሉ በተጠየቁ ግዜ የጥሬ ገንዘብ እጥረት ያጋጥማቸውና በታክስ አሰባሰብ ሂደቱ ላይ ችግር ሲፈጥሩ ይስተዋላል። በተገቢው ጊዜ አለመክፈል ሕብረተሰቡ ማግኘት ያለበትን ተገቢውን የመንግስት አገልግሎት እንዳያገኝ ምክንያት ይሆናል። እነዚህን ችግሮች የሚፈታ በአዋጁ አንቀፅ 89 እንደሚከተለው ተደንግጓል፡-

የደረጃ 'ሀ' ግብር ከፋዮች ባለፈው የግብር ዓመት የከፈሉትን ግብር መሰረት በማድረግ በየሦስት ወሩ 25% እንዲከፍሉ ይደረጋል።

የደረጃ 'ለ' ግብር ከፋዮች ከተያዘው የግብር ዓመት በፊት በነበረው የግብር ዓመት የከፈሉትን የግብር ዓመት 25% እንዲከፍሉ ይደረጋል።

ግብር ከፋይ በግብር ዓመቱ መክፈል ያለባቸው = በግብር ዓመቱ መክፈል ያለበት ግብር መጠን ባለፈው የግብር ዓመት መሰረት ተደርጎ የተከፈለው ግብር መጠን ተቀንሶ ዜሮ መሆን አለበት። ግብር ከፋዩ ባለፈው ግብር ዓመትን መሰረት ተደርጎ የከፈለው የግብር መጠን በግብር ዓመቱ መክፈል ካለበት የበለጠ ወይም ያነሰ ከሆነ እንደቅደም ተከተሉ ቀሪውን ለግብር ከፋዩ ተመላሽ ይደረግለታል ወይም ለመንግስት እንዲከፍል ይደረጋል።

### ሌሎች አዳዲስ ይዘቶች

ከቤት ኪራይና ንግድ ስራዎች የሚገኘን ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢ መሰረት በማድረግ ግብር ከፋዮች በአዋጅ ቁጥር 1395/2017 ደረጃ 'ሀ' እና ለ' ተብለው ተመድበዋል። በእያንዳንዱ ደረጃ ውስጥ ያለ ግብር ከፋይ ያሉትን መብትና ግደታ ለመለየት፣ ከመቼ እስከ መቼ ግብርን መክፈል እንዳለባቸው ለመለየት ነው። ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ የፌዴራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 1395/2017 የሚከተሉትን ይዘቶች ያካተተ ነው።

### ለአነስተኛ ንግድ ስራዎች ቀላል የግብር ስርዓት መዘርጋት

ዓመታዊ የሽያጭ ገቢያቸው ከብር ሁለት ሚሊዮን በታች የሆነ አነስተኛ የግብር ከፋዮች ግብር የሚከፍሉበት በዓመታዊ ጠቅላላ የሽያጭ ገቢያቸው ላይ እንዲሆን የሚያስችል ቀለል ያለ ስርዓት ተዘርግቷል።

በዚህ መሰረት አነስተኛ የንግድ ስራዎች ከዚህ በፊት ከነበረው እጅግ የተወሳሰበ የቁርጥ ግብር ስርዓት ተላቀው ዓመታዊ የሽያጭ ገቢያቸው ላይ ተመስርቶ በአነስተኛ ምጣኔ ከ2%-9% ግብር እንዲከፍል ይደረጋል።

ይሁን እንጂ በሙያ ስራ ላይ የተሰማሩ ግብር ከፋዮች አዕምሯቸውን ተጠቅመው በአነስተኛ ወጪ ስራቸውን የሚያከናውኑ በመሆኑ እቃ ገዝተው ለሚሸጡ የተዘጋጀው በጠቅላላ ሽያጭ ላይ የተመሰረተው የማስከፈያ ምጣኔ ለሙያ ስራ ተፈፃሚ እንዲሆን ማድረግ ፍትሐዊ ስላልሆነ፣ የሙያ ስራ የሚሰሩ መዝገብ አቅርበው ግብር የመክፈል ግደታ አለባቸው።

### ኀላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማሕበር ላይ የሚጣለውን የተደራራቢ ግብር ማስከፈል ስርዓትን ማስቀረት

ኃላፊነታቸው የተወሰነ የሽርክና ማሕበራት አደረጃጀታቸውን እና ገቢ የሚከፋፈሉበትን መንገድ ከግምት ውስጥ ያስገባ የግብር ስርዓት ያልተዘረጋላቸው በመሆኑ ለተደራራቢ ግብር ተጋልጠዋል። የሕግና የሌሎች ሙያዎች ባለቤቶች በዚህ መልክ ተደራጅተው መስራታቸው በዓለም አቀፍ ደረጃ የተለመደ እና ውጤት የሚያስገኝ ስለሚሆን አደረጃጀቱ ለተጨማሪ የግብር ጫና የሚዳርግ ሊሆን አይገባም። ይህንን ግምት ውስጥ በማስገባት እና የሌሎችን ሀገራትን ልምድ በማየት ማህበራቱ ከግብር ነፃ ሆነው ማሕበሩ ትርፉን ለአባላቱ በሚከፋፈልበት ጊዜ በሰንጠረዥ 'ሐ' መሰረት ግብሩን ቀንሶ ለታክሱ ባለስልጣን ገቢ የሚያደረግበትን አሰራር የሚዘረጋ ድንጋጌ ተካትቷል።

### ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት የሚያስችሉ ማሻሻያዎች ማድረግ

አንዳንድ ድርጅቶች የግለሰቦችን ሀብት በማሰባሰብ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ (ኩባንያ) በማቋቋም ይህንን ገንዘብ የካፒታል እጥረት ባለባቸው ድርጅቶች ውስጥ በኢንቨስትመንት ስራ ላይ ያውላሉ። እነዚህ ኩባንያዎች በራሳቸው የንግድ ስራ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚገቡ ባለመሆኑ በአብዛኞዎቹ የዓለም ሀገሮች ከታክስ አከፋፈል ረገድ የተለየ ስርዓት ይዘረጋላቸዋል። በሀገራችንም የዚህ ዓይነት ድርጅቶች ኢንቨስትመንትን በማገዝ ረገድ ጠቀሜታ ስላላቸው ተመሳሳይ የሆነ ስርዓት በፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 1395/2017 ተካትቷል።

### የአክስዮን ትርፍ ድርሻን መልሦ ቃል ለተገባ አክስዮን ማዋልን ከግብር ነፃ ማድረግ

ባለአክሲዮኖች የሚያገኙትን የትርፍ ድርሻ ወስደው ለፍጆታ ከሚውለው ኩባንያው ውስጥ ስራ ላይ እንዲውል በማድረግ የኩባንያውን አቅም እንዲያሳድጉ ማድረግ በመሆኑ የዚህ ዓይነቱ ኢንቨስትመንትም ሊበረታታ እንደሚገባ ታምኖበታል። በዚህ መሰረት ባለአክሲዮኖች ያገኙትን የትርፍ ድርሻ ቃል የገቡትን የኩባንያውን አክስዮን ዋጋ ለመክፈል ካዋሉ የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ግብር እንደማይጠየቁ የሚገልፅ አዲስ ድንጋጌ ተካትቷል።

### በተለያዩ ሕጎች የተሰጡ የግብር ማበረታቻዎች በአንድ ሕግ ማካተት

መንግስት ኢንቨስትመንትን፣ ፈጠራን፣ በማህበር ተደራጅቶ መስራትን ወዘተ ለማበረታታት የግብር ማበረታቻዎች ይሰጣል። በእነዚህ ማበረታቻዎች ምክንያት የማይሰበሰበው የመንግስት ገንዘብ ተሰብስቦ የመንግስትን የፍላጎት ቅደም ተከተል በጠበቀ አኳኋን ስራ ላይ ሊውል የሚችል በመሆኑ እንደታክስ ወጪ የሚቆጠር ነው። የዚህ ዓይነት ወጪ በጥንቃቄ ካልተመራ የመንግስትን የገቢ አቅም የሚያዳክም ስለሚሆን ሊታጣ የሚችለውን ገቢ ከግምት ውስጥ ያስገባና በጥናት ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይገባል።

ከዚህ በተጨማሪ መንግስት በሰጠው ማበረታቻ ምክንያት የተገኘው ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጥቅም እንዲሁም የታጣው ገቢ መጠን እየተለካ የሚፈፀም ካልሆነ ለከፍተኛ ብክነት የሚዳርግ ይሆናል። በመሆኑም ከግብር ነፃ በማድረግ የሚሰጥ ማበረታቻ ወጥነት ባለው በአንድ የታክስ ማበረታቻ ሕግ እንዲመራ ማድረግ የሚያስችል ድንጋጌ በአዋጁ ተካትቷል።

## እንኳን ለ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ! አደረሰን!

የአዲስ አበባ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን እንኳን ለኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ እያለ ውድ የምግብ፣ የጤና እና ጤና ነክ ተቋማት ባለቤቶችና ነጋዴዎች በሙሉ የተቋማችሁን የጤና ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የምታድሱበት ጊዜ በበጀት ዓመቱ ከሐምሌ 1 እስከ ታህሳስ 30 መሆኑን እና ከጥር 1 እስከ የካቲት 30 ባለው ጊዜ ውስጥ ካላደሱ፣ ከመደበኛ ክፍያ በተጨማሪ 50% ቅጣት መሆኑን በመመሪያ ቁጥር 121/2014 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 8 ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም በተቀመጠው ጊዜ መጥታችሁ እንድታድሱ ባለስልጣኑ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡



በአዲስ አበባ የምግብና መድኃኒት ባለስልጣን
AAFDA



## መልካም በዓል!

ወ/ሮ ሙሉእመቤት ታፈሰ
የአዲስ አበባ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን
ዋና ስራ አስኪያጅ



ቦሌ ክ/ከተማ አስተዳደር
Bole Sub City

## እንኳን ለኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ!

የኢሬቻ በዓል የኦሮሞ ሕዝብ ከክረምት ወደ በጋ፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን ላሸጋገረው ፈጣሪ ምስጋናውን የሚያቀርብበት ታላቅ የምስጋና በዓል ሲሆን፣ ከሀገር አልፎ በዩኔስኮ በማይዳሰስ የዓለም ቅርስነት የተመዘገበ የኢትዮጵያ እሴት ነው፡፡ የዘንድሮው የኢሬቻ በዓል የዘመናት የሕዝባችን ቁጭት የነበረውን በራሳችን ሀብት የመጠቀም መብታችንን ያረጋገጥንበት ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ተጠናቆ ለምረቃ በበቃበት ማግሥት የሚከበር በመሆኑ ልዩ ሥፍራ ይሰጠዋል፡፡

በመሆኑም የዘንድሮውን የኢሬቻ በዓል ስናከብር ወንድማማችነትና እህትማማችነትን፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችንን አጠናክረን ባሕላዊ እሴቶቻችንን በላቀ ደረጃ ከፍ የምናደርግበት ሊሆን ይገባል፡፡



## መልካም በዓል!

እሸቱ ለማ (ዶ/ር)
የቦሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ዋና ሥራ አስፈጻሚ





የካ ክፍለ ከተማ አስተዳደር
YEKA SUB CITY ADMINISTRATION
አዲስ አበባ - ADDIS ABABA

**እንኳን ለ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ፤ አደረሰን!**

በዓሉ የሰላም፣ የፍቅርና የብልፅግና እንዲሆንላችሁ በራሴና በየካ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ስም ልባዊ ምኞቴን እየገለፅኩ አስተዳደሩ በባለፈው በ2017 በጀት ዓመት በመንግስት ካፒታል በጀትና በህብረተሰብ ተሳትፎ በርካታ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሰው ተኮር ፕሮጀክቶችን በአጭር ጊዜና በጥራት ሰርቶ በማጠናቀቅ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ አድርጓል።

በተለይም በመልካም አስተዳደር፣ በስራ ዕድል ፈጠራ፣ በትምህርት፣ በጤና፣ በሰላምና ፀጥታ፣ በኮሪደርና ወንዝ ዳርቻ ልማት ስራዎች ከተማዋን ውብና ፅዱ እንዲሁም ለነዋሪዎቿ ምቹ ከማድረግ አንፃር አመርቂ ውጤቶችን አስመዝግቧል።

በተያዘው በጀት ዓመትም እነዚህን ስራዎች አጠናክረን እንደምናስቀጥል ለክፍለ ከተማችን ነዋሪዎች ቃል እየገባን አቅደን በምናከናውናቸው የልማት ስራዎች ላይ እንደከዚህ በፊቱ ከጎናችን ሆናችሁ የካን የብልፅግና ከፍታ ማሳያ እንድናደርጋት ጥሪዬን አስተላልፋለሁ፡፡

# መልካም በዓል!

**አቶ ፍፁም ኃይሌ የየካ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ዋና ስራ አስፈፃሚ**



**እንኳን ለ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ! አደረሰን!**

የሚለው የኦሮሚያ ውሃና ኢነርጂ ቢሮ በዓሉ የሰላም፣ የጤና የአንድነት እንዲሆን ልባዊ ምኞቱን ይገልጻል።

# መልካም የኢሬቻ በዓል

**ኢንጂኒየር ሚሊዮን በቀለ የኦሮሚያ ውሃና ኢነርጂ ቢሮ ሃላፊ**

Siinqee
EMPOWERED. TOGETHER BANK



እንኳን ለኢሬቻ በዓል
በሰላም አደረሳችሁ!

ሲንቄ ባንክ እንኳን ለኢሬቻ በዓል
በሰላም አደረሳችሁ እያለ፤
በዓሉ የፍቅር፣ የአብሮነት እና
የሰላም እንዲሆንላችሁ ይመኛል!

መልካም
የኢሬቻ በዓል



በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ዳኞች አስተዳደር ጉ/ጽ/ቤት በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ በጣም ትልቅ ቦታ ያለው ለፈጣሪ ምስጋና የሚቀርብበት እና የአንድነታችን፣ የአብሮነታችን መገለጫ ለሆነው ለኢሬቻ በዓል እንኳን በሠላም አደረሰን እያለ ጽፈት ቤታችን በሁሉም በወረዳ ለሚገኙ የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች የድጋፍ እና የክትትል ሥራዎችን አበክሮ ይሠራል፡፡ ፍርድ ቤቶቹ ለከተማው ነዋሪ ተደራሽ እና ቀልጣፋ የዳኝነት አገልግሎት በመስጠት በነዋሪው ላይ ሊደርስ የሚችለውን የሀብት እና የጊዜ ብክነት ማስቀረት የተቋቋሙበት ዋነኛ ዓላማ ነው፡፡

እነዚህ ፍርድ ቤቶች ግምታቸው ከ5,000 ሺህ ብር ያልበለጡ የንብረትና የገንዘብ ክርክሮችን እንዲሁም ከኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ከአንቀጽ 815 እስከ 862 ውስጥ የሚገኙ 22 የደንብ መተላለፎች መሠረት የሚቀርቡላቸውን አቤቱታዎች ተመልክተው ውሳኔ በመስጠት ህብረተሠቡ በመኖሪያ አካባቢው ከጊዜና ከሀብት ብክነት ተጠብቆ ጥራት ያለው የዳኝነት አገልግሎት እንዲያገኝ የበኩላቸውን ሚና እየተወጡ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም በአዲስ አበባ ከተማ ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን የደንብ ጥሰትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር አዲስ በወጡት ደንብ ቁጥር 150/2015 እና በተሻሻለው ደንብ ቁጥር 167/2016 መሰረት የሚቀርቡለትን ጉዳዮችን አከራክሮ በመወሰን የዳኝነት አገልግሎት እየሰጡ ይገኛል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ የማህበራዊ ፍ/ቤት ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት ለመላው ህዝባችን የ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል የሠላም፣ የጤና እና የግብልጽግና እንዲሆንልዎ ይመኛል፡፡

**አቶ ገ/እግዚሐብሄር ገ/ማሪያም**
**የአዲስ አበባ ከተማ የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ዳኞች**
**አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት ፕሬዝዳንት**



# የምገባው ትሩፋት

• ምገባው የተማሪዎች አዕምሯዊና አካላዊ እድገት የተሻለ እንዲሆን አስተዋፅኦ እያደረገ መሆኑ ተጠቁሟል



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል
በመሃል ግንፍሌ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የምገባ አገልግሎት ሲያገኙ




ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል
በትምህርት ቤት ምገባ ተጠቃሚ የሆኑ ተማሪዎችን ቁጥር የሚያሳይ ግራፍ

**በፋንታነሽ ተፈራ**

ለአንድ ሀገር እድገትና ብልፅግና ቁልፍ ሚና የሚጫወተውን ብቃት ያለው የሰው ሀይል ለማፍራት እውቀት በሚገበይባቸው ትምህርት ቤቶች ላይ የሚሰራው ስራ ወሳኝ ነው፡፡ በትምህርት ቤቶች ለልጆች የተመጣጠነ ምግብ ማቅረብ ጤናማ፣ በትምህርታቸው ውጤታማ፣ አዳዲስ ሀሳቦችን ማፍለቅና በጥልቀት በማሰብ ችግሮችን መፍታት የሚችሉ ዜጎችን ለማፍራት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡

የዓለም ምግብ ፕሮግራም እ.ኤ.አ በ2017 ዓ.ም Master of Card Foundation ጋር በመሆን በኢትዮጵያ ያጠናው ጥናት እንደሚያሳየው፣ በሀገር በቀል ምገባ አማካይነት በአንድ ልጅ የትምህርት ዘመን ላይ ፈሰስ የምትደረግ እያንዳንዷ ዶላር የልጁን/ቷን ትምህርት፣ ጤና እና ምርታማነት በማሻሻል በአማካይ የ7 ነጥብ 2 የአሜሪካን ዶላር ትርፍ ታስገኛለች፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ በተለይ ዝቅተኛ የኢኮኖሚ አቅም ያላቸው ወላጆች፤ ለልጆቻቸው አስፈላጊውን ምግብ እንዲሁም የትምህርት ቁሳቁስ አሟልቶ መላክ ፈተና ሆኖባቸው ቆይቷል፡፡ በዚህም የተነሳ ቁርሳቸውን በአግባቡ ሳይመገቡ፣ ባዶ የምሳ ሳህን ቋጥረው ወደ ትምህርት ቤት የሚሄዱ ተማሪዎች ቁጥር ቀላል አልነበረም፡፡

የከተማ አስተዳደሩም ይህንን ችግር በመቅረፍ የትምህርት ተሳትፎና ውጤታማነትን ለማሳደግ የቅድመ አንደኛና የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎችን የትምህርት ቤት ምገባ መርኃ ግብርን ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ በማድረግ የመጪው ትውልድ ግንባታ ላይ እየሰራ ይገኛል፡፡

የዝግጅት ክፍላችንም ተማሪዎች በትምህርት ቤት ምገባ መርኃ ግብሩ ላይ የተመጣጠነ ምግብ መመገባቸው ጤናማ፣ ንቁ እና ጠንካራ ከመሆን ባሻገር የትምህርት አቀባበላቸው ላይ ምን ውጤት እያመጣ እንደሚገኝ በተለያዩ ትምህርት ቤቶች ቅኝት አድርጓል፡፡

ቅኝት ካደረግንባቸው ትምህርት ቤቶች መካከል የካራማራ ሌተናል ኮሎኔል አብዲሳ አጋ እና ቀበሌ 37 ቅድመ አንደኛ፣ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አንዱ ነው፡፡ በትምህርት ቤቱ የ8ኛ ክፍል ተማሪ የሆነችው ቅድስት ውድማጣስ የትምህርት ቤት ምገባ ከመጀመሩ በፊት ቁርሷን ሳትመገብ ወደ ትምህርት ቤት ትሄድ እንደነበር ታስታውሳለች፡፡ በዚህም "አቅም አንሶኝ ወድቄ አውቃለሁ፤ ክፍል ውስጥም ስመለስ ስለምመገበው እንጂ ስለትምህርት ምንም ዓይነት ትኩረት ሰጥቼ አላውቅም፡፡" ስትል ምግብ ሳይመገቡ ትምህርትን መከታተል ምን ያህል ፈታኝ እንደሆነ ትናገራለች፡፡

"ምገባ ከተጀመረ በኋላ ከቤቴ ስወጣ 'ምሳ ምን ይቋጠርልኛል' ብዬ ሳልጨነቅ ትምህርት ቤት ቁርሴንም ምሳዬንም እየተመገብኩ ነው፡፡ የተመጣጠነ ምግብም እያገኘሁ ነው፡፡ አሁን ትኩረቴ ትምህርቴ ላይ ብቻ ሆኗል፡፡ በዚህም አማካኝነት በክፍል ውስጥ ደረጃዬን አሻሽያለሁ፡፡ በዚህ ዓመት ደግሞ በተለየ ሁኔታ ከዚህ በፊት ያልነበሩ ፍራፍሬ፣ እንቁላል እና የመሳሰሉ የምግብ አይነቶችን እንድንመገብ ተደርጓል፡፡" ስትልም ሀሳቧን አጋርታለች፡፡

በመንግስት ትምህርት ቤቶች ምገባ ከመጀመሩ በፊት የተማሪዎች የትምህርት አቀባበል አጥጋቢ እንዳልነበረ የሚናገሩት ደግሞ በትምህርት ቤቱ የቋንቋ መምህር የሆኑት እንግዳወርቅ በቀለ ናቸው፡፡

በአሁኑ ወቅት ሁሉም ተማሪዎች የምገባው ተጠቃሚ መሆናቸው በሰዓቱ ትምህርት ገበታቸው ላይ እንዲገኙ፣ በክፍል ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉና ትኩረታቸው ትምህርታቸው ላይ እንዲሆን እድል ፈጥሯል፡፡ ምገባው የተመጣጠነ ምግብን ጭምር ያካተተ መሆኑ ደግሞ የአዕምሮ እድገትን በማፋጠን የትምህርት አቀባበላቸው የተሻለ እንዲሆን ማድረጉን ከበፊቱ ጋር እያነፃፀሩ ገልፀውልናል፡፡

በትምህርት ቤቱ የምግብ ጥራትና ቁጥጥር ባለሙያ የሆኑት አቶ አወቀ ደምሴም የመምህሩን ሀሳብ ያጠናክራሉ። በምገባ መርኃ ግብሩ የተካተቱት የተመጣጠኑ፣ ገንቢ፣ ሃይልና ሙቀት ሰጪ፣ በሽታ ተከላካይ እና ማዕድናትን የያዙ ምግቦች ናቸው፡፡ ተማሪዎች የተመጣጠነ ምግብ መመገባቸው ለአካላዊና አዕምሯዊ ዕድገታቸው ከመርዳቱ በተጨማሪ በሽታ የመከላከልና የመቋቋም አቅምን የሚፈጥር በመሆኑ በንቃትና በደስታ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ እያገዘ እንደሚገኝ አብራርተዋል፡፡

የተማሪዎች የተመጣጠነ ምግብ አለማግኘት በአካል ብቻ ሳይሆን በአዕምሮም መቀንጨር ያስከትላል። በትምህርታቸው ውጤታማ የመሆን እድላቸው ዝቅተኛ እንዲሆን ያደርገዋል ያሉት አቶ አወቀ፤ በትምህርት ቤቱ በ2018 የተዘጋጀው የምግብ ዝርዝር (ሜኑ) ልዩ ፍላጎትን ጨምሮ ለእድገታቸው ወሳኝ የሆኑና በንጥረ ነገር ይዘታቸው የተሟሉ ምግቦችን ያካተቱ ናቸው፡፡ ከሂደቱ ጀምሮ በምግብ ዝርዝሩ (ሜኑ) መሰረት ተዘጋጅቶ ተማሪው ጋር እንዲደርስ የቁጥጥርና የክትትል ስራም እየተከናወነ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

ምገባው ተማሪዎች በሰዓት ተገኝተው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ እና ውጤታማ እንዲሆኑ ያደረገ መሆኑን የሚገልጹት የካራማራ ሌተናል ኮሎኔል አብዲሳ አጋ እና ቀበሌ 37 ቅድመ አንደኛ፣ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ዘላለም ተስፋዬ በበኩላቸው፤ ለዚህ በማሳያነት የሚያነሱት በ2017 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የ8ኛ ክፍል የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ ወደ 9ኛ ክፍል ማለፋቸውን ነው፡፡

በትምህርት ቤቱ የተመጣጠነ ምግብ ለተማሪዎቹ በወጣው የምግብ ዝርዝር፣ በንፅህና እና በጥራት እንዲቀርብ የስነ ምግብ ባለሙያ በመቅጠር እንዲሁም ከትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ኮሚቴ በማዋቀር የድጋፍ፣ የቁጥጥር እና ክትትል ስራ እንደሚሰራ ነግረውናል፡፡

መንግስት የተመጣጠነ ምግብ ማቅረብ መቻሉና የትምህርት ቁሳቁስ ማሟላቱ በትምህርት አቀባበላቸው ላይ ከሚያሳድረው በጎ ተፅዕኖ በተጨማሪ ሀገር ወዳድ ትውልድም ለማፍራት ትልቅ ድርሻ እንዳለው ርዕሰ መምህሩ አያይዘው አንስተዋል፡፡

ሌላኛው ቅኝት ያደረግንበት ትምህርት ቤት በመሃል ግንፍሌ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ በትምህርት ቤቱ የ6ኛ ክፍል ተማሪው ሳምሶን ዮሐንስ በምገባ መርኃ ግብሩ ደስተኛ እንደሆነ ይናገራል፡፡ "የሚሰጠንን የክፍል ስራ እሰራለሁ፤ በክፍል ውስጥም ተሳትፎ አደርጋለሁ፤ ትምህርት ቤት አላረፍድም። የምንመገባቸው ምግቦች አንዳንድ ጊዜ ቤታችን ውስጥ የማይሟሉልን ጭምር ናቸው፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ ትምህርታችንን በንቃት እንድንከታተል አድርጎናል" ሲል ምገባው ምን ያህል ትምህርቱን በአግባቡ ለመከታተል እንዳገዘው ያስረዳል፡፡

መምህርት ፀደይ ሃይሉም የምገባ መርኃ ግብሩ ከመጀመሩ በፊት ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ቁርስም ሳይመገቡ፤ ምሳም ሳይቋጥሩ ወደ ትምህርት ቤቱ ይመጡ እንደነበር ይናገራሉ፡፡ ይህም ክፍል ውስጥ ራሳቸውን ስተው የመውደቅና ደስተኛ ያለመሆን ችግሮችን ሲያስከትል ቆይቷል። ምገባው ከተጀመረበት ወቅት አንስቶ ደስተኛ ሆነው እንዲማሩ፣ ትኩረት ሰጥተው እንዲከታተሉና በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ትልቁን አስተዋጽኦ አድርጎል ይላሉ፡፡

ዝቅተኛ የኢኮኖሚ አቅም ያላቸው ወላጆች ለልጆቻቸው ምግብ ማቅረብ የሚቸገሩ ሲሆን ልጆች በትምህርት ቤት የተመጣጠነ ምግብ ማግኘታቸው አዕምሯቸውና ሃሳባቸው ትምህርታቸው እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ይህም የትምህርት አቀባበላቸው የተሻለ እንዲሆን ያደረገና ወላጆች 'ለልጆቼ ምሳ ምን ልስራላቸው' ከሚል ጭንቀት የገላገለ፣ በደስታ ወደ ትምህርት ቤት የሚልኩበትን እድል ያመቻቸ መሆኑን ገልፀውልናል፡፡

በትምህርት ቤቱ መጋቢ እናት የሆኑት ወይዘሮ ፈትለወርቅ ጥዑመልሳን መንግስት ባዘጋጀው የምግብ ዝርዝር መሰረት ለተማሪዎቹ ምግብ የማዘጋጀት ስራ ይሰራሉ፡፡ ከዚህ በፊት ተማሪዎቹ ባዶ ምሳ እቃ እና ምንም ሳይመገቡ ይመጡ እንደነበር የሚያስታውሱት ወይዘሮ ፈትለወርቅ፣ ምገባ ከተጀመረ በኋላ በተለየ ሁኔታ ምግቡ የተመጣጠነ መሆኑ እና የአዕምሮ እድገት ውስንነት ላለባቸው ተማሪዎች ደግሞ ወተት፣ እንቁላል፣ ስጋ እና ሙዝ እንዲመገቡ በምግብ ዝርዝሩ ውስጥ መካተቱ እንደ እናት እንደሚያስደስታቸው ተናግረዋል፡፡

ለቁርስ ጨጨብሳ፣ ቅንጬ፣ ሳንዱች እና ዳቦ በእንቁላል ቅቅል የሚዘጋጅላቸው ሲሆን፣ ለምሳ ደግሞ ምስር፣ ሽሮ፣ አትክልት እና ሩዝ የምግብ አይነቶች ይቀርብላቸዋል፡፡ ተማሪዎች ምግብ ሲቀርብላቸው ለመመገብ እንደሚደሰቱት ሁሉ ትምህርታቸውንም ደስ ብሏቸው እንዲከታተሉ ያደርጋቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ ለውጤት እንዲበቁ ያግዛቸዋል ሲሉም ገልጸዋል፡፡

የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር የሆኑት ዱጋሳ ባይሳም ምገባው በተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ላይ አዎንታዊ አስተዋፅኦ እያበረከተ እንደሚገኝ አብራርተዋል፡፡ ሳይመገብ እና የተመጣጠነ ምግብ ሳያገኝ ወደ ክፍል የሚገባ ተማሪ፤ የተሻለ ምግብ ከሚያገኘው

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ምገባ ኤጀንሲ
Addis Ababa City Administration
Feeding Agency

## እንኳን ለ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ!

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምገባ ኤጀንሲ እንኳን ለኢሬቻ በዓል በሠላም አደረሳችሁ፤ እያለ በዓሉ የሰላም እና የፍቅር እንዲሆን ይመኛል። ኤጀንሲያችን ባለፍት 6 ዓመታት ሰፊ ሰው ተኮር ተግባራት እየሠራ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን፤ ለ900,000 በላይ ተማሪዎች በቀን ሁለት ጊዜ /ቁርስና ምሳ/፣ ለ1,210,694 የደንብ ልብስ፣ ለ11,864,024 ተማሪዎች የመማሪያ ደብተር በማቅረብ የህብረተሰቡን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን በመፍታት እፎይታን እየሰጠ ይገኛል። ከዚህ በተጨማሪ ከመመገብ ባሻገርም ለመጋቢ እናቶች የስራ ዕድል በመፈጠሩ ከ16ሺህ በላይ ስራ አጥ ለሆኑ እናቶች የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡

ኤጀንሲያችን በክብርት ከንቲባ ወ/ሮ አዳነች አቤቤ ሃሳብ አመንጭነት እና አስተባባሪነት ባለሃብቶችን በማወያየትና በማነሳሳት በ26 የተስፋ ብርሃን ምገባ ማዕከላት ከ36,600 በላይ የዕለት ጉርስ የሌላቸውን አቅመ ደካማ አራጋዊያን፣ ጧሪ ደጋፊ የሌላቸውን አካል ጉዳተኞች፤ ለሀገር ውለታ የሰሩ እና አቅም የሌላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎችን እየመገበ ይገኛል፡፡

**"ከነዋሪዎች እፎይታ እስከ ብቁ ትውልድ ግንባታ"!**



ወ/ሮ ጸዳለች ሚካኤል
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ምገባ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር




**መልካም በዓል!**
**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምገባ ኤጀንሲ!**

AMN CONSTRUCTION PLC

P.BOX. 9176
0115226999 / 0115227359
0945408348 / 0919912526
amnconstructionplcamn@gmail.com
nchibssa@gmail.com

## እንኳን ለ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል በዓል በሰላም አደረሳችሁ!

ኤኤምኤን አስመጪና ላኪ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ማንኛውንም የኮንስትራክሽን እና የግብርና እቃዎች ከተለያዩ ሀገራት አስመጥተን ባሉበት ቦታ እናቀርባለን!

**የምንሰጣቸው አገልግሎቶች**

- ✓ የቀላል እና ከባድ ተሽከርካሪዎች ሽያጭ፣
- ✓ ጀኔሬተሮች እና ኮምፕረሰሮች ከነ መለዋወጫቸው፣
- ✓ የጉድጓድ ቁፋሮ እቃዎች እና መለዋወጫዎች፤
- ✓ የማንኛውም ተሽከርካሪ ጎማዎች፣ ባትሪዎች፣ ፊልተሮች እና ወ.ዘ.ተ የመረጡትን እቃ ለማዘዝ በ 0945408348 ወይም 0919912526 ይደውሉ!
- ✓ የእርሻ እና ግንባታ ማሽኖች፣
- ✓ የግንባታ እቃዎች፣ የትራክተር እና የማሽነሪዎች ጎማ

ከድርጅታችን ጋር አብሮ ለመስራት ከፈለጉ በማንኛው ጊዜና ሰዓት ወደ ቢሮአችን በመምጣት አልያም በመደወል ማናገር የሚችሉ መሆኑን ስንገልጽ በደስታ ነው፡፡ እኛ ዘንድ ከመጡ ኪሳራ ብሎ ነገር አይታሰብም፡፡ ይህንን ዓላማችሁን ለማሳካት ወደ ኤ.ኤም.ኤን ኮንስትራክሽን ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ይደውሉ፤ ያሉበት ቦታ ድረስ መጥተን ፍላጎታችሁን እናሟላለን፡፡

**A.M.N Construction PLC**

Car spare parts
1. Tractor spare parts
2. Excavator and it's spare parts
3. Different Machineries Lubricants
4. Generators spare parts
5. All kinds of Battery.......

+971508589125 +8615626207446
P.BOX. 9176
amnconstructionplcamn@gmail.com
nchibssa@gmail.com
http://www.amnplc.com
https://t.me/AMNGeneralspare
https://t.me/AMNimportexport
Telegram (https://t.me/AMNGeneralspare)

**ለበለጠመረጃ:-**
0115582353 / 0115227359 0945408348 / 0919912526
+971508589125 P.BOX. 9176






የመንግስት ንብረት አስተዳደር ባለሥልጣን
አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
GOVERNMENT PROPERTY ADMINISTRATION AUTHORITY
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION

## መልካም የኢሬቻ በዓል!!

**አቶ የሱፍ ኢብራሂም ሽፋው**
**የመንግስት ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን**
**ዋና ስራ አስኪያጅ**

# እንኳን ለ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል አደረሳችሁ! አደረሰን!

ለመላው ኢትዮጵያውያን እንኳን ለ2018 ዓ.ም የሆራ ፊንፊኔ እና ሆራ አርሰዲ ኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ። በዓሉ የሰላም፣ የጤና እና የአብሮነት እንዲሆን የመንግስት ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን መልካም ምኞቱን ይገልጻል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ መልከዓ ምድሯ ያሸበረቀ፣ ባህሏ ቀለመ ብዙ፣ የበርካታ ቋንቋ ተናጋሪዎች ስብጥር ሀገር ናት። በርካታ ማንነቶች ያሏት፣ ህዝብ በእኩልነትና በፍቅር የሚኖሩባት፤ አንዳችን የሌላችንን እያከበርን በፍቅርና በሠላም የምንኖርባት ሀገር ነች፡፡

ኢትዮጵያ የራሷ የዘመን አቆጣጠር ያላት፣ የሰው ዘር መገኛ ድንቅ ባህል ያለው ህዝብ መኖሪያ የሆነች የጥንት ስልጣኔ ባለቤትም ነች።
በሀገራችን ከዘመን አቆጣጠር አንፃር የወራት መጀመሪያ ተደርጎ የሚታወቀው የመስከረም ወር ነው። በዚህ ወር የዘመን መለወጫ ብቻ ሳይሆን ትልልቅ ሀይማኖታዊ እና ህዝባዊ የአደባባይ በዓላት የሚከበርበትም ነው። ከምናከብራቸው የአደባባይ በዓላት ውስጥ ኢሬቻ አንዱ ነው፡፡

ኢሬቻ የኦሮሞ ሕዝብ የገዳ ስርዓት አንዱ አካል የሆነ ህዝባዊ በዓል ነው። ክረምቱ አልፎ ብርሀን ሲሆን ተፈጥሮን የፈጠረ ፈጣሪ የሚመሰገንበት የምስጋና በዓል ነው። የኦሮሞ ሕዝብ ጥልና ጥላቻን በይቅርታ ተሻግሮ፣ በንጽህና ፈጣሪውን ምህረት የሚጠይቅበት ጊዜ እና መጪው ጊዜ የሰላምና ፍቅር እንዲሆን ፈጣሪውን የሚለምንበት በዓል ነው።
እንደ ኢሬቻ አይነት የአደባባይ በዓላት በሕዝቦች መካከል መቀራረብን፣ መተሳሰብን፣ መረዳዳትን፣ ሕብረብሔራዊ ወንድማማችነትና እህትማማችነት እንዲያብብ ያደርጋሉ፡፡
የአደባባይ በዓላት የደስታና የምስጋና በዓላት ብቻ ሳይሆኑ ለኢኮኖሚው መነቃቃትም የራሳቸው ፋይዳ ያላቸው በመሆናቸው ለከተማችን እድገት የራሱ አዎንታዊ ድርሻ ያበረከታሉና የኢሬቻ በዓል በልዩ ልዩ ዝግጅት በድምቀት መከበሩ ይቀጥላል።

በመሆኑም ኢሬቻ ብዙ ህዝብ ወደ አደባባይ ወጥቶ የሚያከብረው በዓል እንደመሆኑ ሁላችንም በፍቅር፣ በመተሳሰብ፣ በአብሮነት እና በአንድነት ማክበር ይገባናል።



ለሚ ኩራ ክ/ከተማ - አዲስ አበባ
KUTAA MAGAALAA LAMMII KURAA
- FINFINNEE -

## እንኳን ለ2018 ዓ.ም ለሆራ ፊንፊኔ እና ለሆራ አርሰዴ የኢሬቻ በዓል አደረሳችሁ!

እንኳን ለ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል በሰላም እና በጤና አድረሳችሁ፣ አደረሰን የሚለው የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በ2017 ዓ.ም ትኩረት ሰጥቶ ከሰራቸው ተግባራት መካከል የአገልግሎት አሰጣጥና መልካም አስተዳደርን ማሻሻል፣ የወጣቶች፣ ሴቶች፣ አርሶ አደሮችና ነዋሪዎች ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣ የልማት ስራዎች፣ የፕሮጄክት አፈጻጸም፣ ሰው ተኮርና የበጎ ፍቃድ ስራዎች፣ ከተማ ግብርናና ሌማት ትሩፋት፣ በድህነት ቅነሳና ዘላቂ ልማት፣ ሰላም ግንባታ፣ በሀገራዊና ከተማዊ ተልዕኮዎች እና እንደ ከተማ አስተዳደሩ ትኩረት የተደረገበት የኮሪደር ልማት ስራ በተጨማሪም በራስ አቅም ህብረተሰቡን በማሳተፍ የተሰሩ ስራዎች የክፍለ ከተማውን ገጽታ ከመቀየራቸው በተጨማሪ የበለጠ ውበትን ለከተማችን አበርክተዋል፡፡

የተከበራችሁ የክፍለ ከተማችን ነዋሪዎች እንዲሁም በየደረጃው ያላችሁ አመራሮችና ባለሙያዎች 2018 ዓ.ም እንደ አደይ በመልካም ስራዎቻችን የምንደምቅበት፣ የመልካም አስተዳደር ስራዎቻችንን የምናጠናክርበት፣ በአዲስ አገልግሎት አሰጣጥ የተገልጋዮችን እርካታ የምናሳድግበት እና የልማት ስራዎቻችንን በትጋት ከህብረተሰባችን ጋር የምናከናውንበት፤ በአጠቃላይ ሁሉንም ተግባሮቻችንን በአፈጻጸም ወደ ተሻለ ስራ የምናልቅበት ብሩህ የደስታ፣ የብልፅግና፣ የብርሃን፣ የማንሰራራትና የከፍታ ዓመት የምናሳልፍበት እንዲሆን ከልብ እየተመኘሁ፤ በዓሉ የሰላም፣ የደስታ፤ የአብሮነትና የፍቅር እንዲሆንልን ልባዊ ምኞቴን እገልፃለሁ።



# መልካም በዓል!!

አቶ አድማሱ ደቻሳ
የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ አስተዳደር
ዋና ስራ አስፈጻሚ

በመጀመሪያው የእትዮ ሪል እስቴት አዋርድ ላይ ተሸላሚ የሆነው

# ቴምር ፕሮፐርቲስ

Temer PROPERTIES

በ2008 ዓ.ም በሁለት ባለ ራዕዮች ሀሳብ ትልቁን ጉዞ የጠነሰሰ፣ ከ500 በላይ ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን የመኖሪያ አፓርታማዎችንና የንግድ ሱቆችን ለደንበኞቹ በጥራት እና በተመጣጣኝ ዋጋ አጠናቅቆ ያስረከበ ቴምር ፕሮፐርቲስ ትልቅ ጉዞን የጠነሰሰ በእድገት አጎልብቷል።

ቤትን እንደ ዳቦ ለብዙሃን ለማድረስ ተልሞ የተነሳው ቴምር፣ ለመጀመሪያ ጊዜ በተዘጋጀው የኢትዮ ሪል ስቴት አዋርድ ላይ፣ በተመጣጣኝ ዋጋ የመኖሪያ ቤት እና የንግድ ሱቆችን ገንብቶ በማቅረብ ዘርፍ ብቸኛ አሸናፊ የሆነው ቴምር ፕሮፐርቲስ፣ አሁን ላይ በተደራጀ መዋቅር ከ 800 በላይ ሰራተኞችን ከእህት ኩባንኛዎቹ ጋር በመተባበር በጥራት እና በፍጥነት ገንብቶ በማስረከብ ግንባር ቀደም ሆኗል።

በትልቅ ራዕይ የጀመረው ቴምር ፕሮፐርቲስ፣ የሪል ስቴት ዘርፋን ሽያጭን በአዲስ ዘርፋን ሽያጭ አቅጣጫ በማስቀየር እንዲሁም የተለያዩ ቴክኖሎጂ እና ፕላትፎርምዎችን በመጠቀም ለነባርም ሆነ ለአዲስ ደንበኞቹ ምቹ የሆነ ያሰራር ሂደት መዘርጋታችን ተመራጭ ያደርገናል።

በከተማችን በተለያዩ ቦታዎች ላይ ጥራት ምቾት ዋጋን አገናዝቦ በተቀመጠላቸው ጊዜ የሚደርሱ የመኖሪያ ቤት እና የንግድ ሱቆችን ለማቅረብ ሙሉ ዝግጅቱን ጨርሶ ደንበኞቹን በመጠባበቅ ላይ ይገኛል።

ተጨማሪ ማብራሪያዎችን እና መረጃዎችን ለማግኘት የነፃ ስልክ መስመራችን **6033** ወይም በስልክ ቁጥር **+251 975 666 699**

እንዲሁም **www.temerproperties.com** ይጎብኙን

የአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን
ADDIS ABABA ENVIRONMENTAL PROTECTION AUTHORITY

የዘንድሮውን የኢሬቻ በዓል የምናከብረው የዚህ ትውልድ ዳግማዊ አድዋ የሆነውን ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን በተባበረ ክንዳችን አጠናቅቀን በማስመረቅ ሀገራችን በቀጠናዋ ያላትን ጂኦስትራቴጂካዊ ቁመናችንን ማደስ በጀመርንበት ማግስት መሆኑ ልዩ ያደርገዋል።

ህዳሴ ግድባችን የባዕዳን ቀረርቶና ሽለላ በኢትዮጵያዊያን ጀግንነትና ትብብር ድል የተደረገበት፣ የአበዳሪ ድርጅቶችና ሀገራት ፊት መንሳት በዜጎቻችን እልህና ቁጭት የተሳካበት በራስ አቅም የመልማት ዓቅማችንን ለዓለም ያሳየንበት ዓመት ነዉ።

የዘንድረውን የኢሬቻን በዓል ሲናከብርም በህዳሴ ግድብ ያሳየነውን ትብብራችንን በማጠናከር የሰው ልጅ በተፈጥሮ ያለውን አንድነት እና አብሮ መኖርን እያደነቀ ለፈጣሪው ምስጋና የሚያቀርብበት ልዩ በዓል በጋራ በማክበር አንድነታችንን ዳግም የሚናሳይበት መሆን አለበት፡፡ የኦሮሞ ማህበረሰብ ከገዳ ሥርዓት በወረሰው እሴት ክረምቱ አልፎ በጋ ሲገባ ፈጣሪውን የሚያመሰግንበት በዓል ነዉ፡፡ የኦሮሞ ህዝብ በወርሃ መስከረም መጨረሻ ላይ በየዓመቱ የሚያከብረዉ የኢሬቻ በዓል የክረምቱን ጨለማ አሳልፈህ፣ እህልን አብቅለህ፣ ማሳውን አሳምረህ፣ የበጋውን ብርሃን ስላሳየኸን ፈጣሪ ምስጋና ይግባህ ብሎ አምላኩን ያመሰግናል፡፡



በዚህም የመልካም ነገር ምኞት መግለጫ የሆነውን እርጥብ ሳር ይዞ "መሬሆ ... መሬሆ" እያለ ወደ መልካ (ወንዝ) በማቅናት የኢሬቻ ሥርዓትን የሚያከናውንበት ነዉ፡፡ ለዚህ ልዩ በዓል እንኳን በሰላም አደረሳችሁ እያለ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ መልካም ምኞቱን ይገልፃል፡፡

**ለመላው የኦሮሞ ህዝብና ኢትዮጵያዊያን በሙሉ እንኳን**
**ለዚህ ታላቅ የምስጋና በዓል በሰላም አደረሳችሁ!**
**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን**

# የመዲናዋ ኪነ ጥበባዊ መረጃዎች






ፎቶ ከገፀ ድር

ከመዲናዋ ጥበባዊ መረጃዎች በከፊል

**በአብርሃም ገብሬ**

የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች እና አዳዲስ ኪነ ጥበባዊ ስራዎች ባለፉት ቀናት በመዲናዋ አዲስ አበባ ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል፡፡ ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም የተለያዩ ጥበባዊ መሰናዶዎች ይደረጋሉ፡፡ ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናት ከተሰናዱ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች መካከል የአዳዲስ መጻሕፍት ህትመት፣ የሥዕል አውደ ርዕይ፣ የቴአትር መርኃ ግብር እና ሌሎች መሰናዶዎች ይገኙበታል። ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡

### መጻሕፍት

የወጣቷ ገጣሚ መንበረ ሐይሉ የግጥም መጽሐፍ ለንባብ ሊበቃ ነው። ከዚህ ቀደም ‘የቃል ሰሌዳ’ እና ‘የጊዜ ሰሌዳ’ በተሰኙ የግጥም መጻሕፎቿ የምትታወቀው ገጣሚ መንበረ አሁን ደግሞ ሦስተኛ የሆነውን ‘የውበት ሰሌዳ’ መጽሐፍ ለተደራስያን ልታደርስ ነው። በቅድመ ሽያጭ ዘዴ በማህበራዊ የትስስር ገጾች አስቀድሞ ለገበያ የቀረበው መጽሐፉ፣ ገጣሚዋ በአዳዲስ ይዘቶችና ቅርጾች በተለያየ ጊዜ የጻፈቻቸው የግጥም ስብስቦችን አካትቶ ለገበያ መቅረቡ ተሰምቷል፡፡ መጽሐፉ ለህትመት ከመብቃቱ በፊት ከገጣሚዋ እጅ መግዛት እንደሚቻል በማህበራዊ የትስስር ገጿ አሳውቃለች፡፡

ከገበያ ጠፍቶ የነበረው ‘ጊዜ...ወይን... ጨረቃ...’ የተሰኘው የግጥም መጽሐፍ ተሻሽሎና አርትኦት ተሰርቶበት ሁለተኛ ዕትም ለንባብ ቀረበ፡፡ ፍቅር፣ ተፈጥሮና ህይወትን የሚያንጸባርቁ ጭብጦችን የያዙ የግጥም ስብስቦች የያዘው መጽሐፉ በተለያዩ የመጻሕፍት መደብሮች ይገኛል።

### ሙዚቃ

የጆኒ ራጋ የሙዚቃ አልበም ተለቀቀ። የድምጻዊ ጆኒ ራጋ “ውሃ እና እሳት” የተሰኘ ሁለተኛ አልበም ከ20 ዓመታት በኋላ ባሳለፍነው ሳምንት መስከረም 21 ቀን 2018 ዓ.ም በጆኒ ራጋ ዩቲዩብ ቻናል በኩል ለአድማጮች ቀርቧል። ጆኒ ራጋ 16 ሙዚቃዎችን በያዘው አዲስ አልበሙ ከአንጋፋ እስከ ወጣት ድምጻውያን እንደተሳተፉበት ኢቨንት አዲስ ሚዲያ ዘግቧል፡፡ ከእነዚህም መካከል አንጋፋው ሙዚቀኛ ባህታ ገብረሕይወት፣ ኤደን አይሸሹምና ዮሴፍ ኤቢሶ በጆኒ ራጋ አልበም የተሳተፉ ሙዚቀኞች ናቸው፡፡

የ“ውሃ እና እሳት” አልበም ግጥም፣ ዜማ እና ቅንብር በራሱ በጆኒ ራጋ የተሰናዳ ሲሆን ፍቅር፣ ትዝታ፣ የጾታ እኩልነት እና ሕይወት በውሃ እና እሳት አልበም ከተነሱ ጭብጦች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው። በዚህ የሙዚቃ አልበም አንጋፋው ሙዚቀኛ ቶሚ ቲ (ቶማስ ጎበና) አሻራውን ያሳረፈበት ሲሆን፤ እንደቀድሞ ሥራው ሁሉ በመላው ዓለም በጥራት መደመጥ እንዲችል ሚክሲንግ እና ማስተሪንጉ የተለያዩ ሀገሮች በሚገኙ የተመረጡ ስቱዲዮዎች መቀረፁ ተሰምቷል።

### ሥዕል

“የተመለሱ እይታዎች” አውደ ርዕይ በመታየት ላይ ነው፡፡ የሠዓሊ ኪሩቤል ተፈሪ የሥዕል ስራዎች የቀረቡበት “የተመለሱ እይታዎች” የተሰኘ የሥዕል አውደ ርዕይ በያዝነው ወር መስከረም 7 ቀን 2018 ዓ.ም ጀምሮ፣ ሐያት ሪጀንሲ ሆቴል ውስጥ በሚገኘው ፈንድቃ የባህል ማዕከል ውስጥ እየታየ ይገኛል። የሰዓሊው የተለያዩ ጥበባዊ የፈጠራ ሥራዎች የቀረበበት የሥዕል አወደ ርዕይ እስከ መጪው ጥቅምት 3 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ ይቆያል ተብሏል።

### ቴአትር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሁድ የተለያዩ ቴአትሮች ይታያሉ፡፡ 12ቱ እንግዶች የተሰኘው ቴአትር ቅዳሜ 8:30 ሰዓት በብሔራዊ ቴአትር ቤት ይታያል። 11፡30 ሰዓት ደግሞ ባሎችና ሚስቶች የተሰኘው ቴአትር በዚያው በብሔራዊ ቴአትር ይታያል፡፡ እሑድ በ8፡30 ሰዓት ደግሞ ንጉሥ አርማህ ቴአትር፣ እንዲሁም እምዬ ብረቷ የተሰኘው ቴአትር ደግሞ በዚሁ በብሔራዊ ቴአትር 11፡30 ሰዓት ላይ ይታያል፡፡

በሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት ደግሞ እሑድ በ8:00 ሰዓት የደመና ዳንኪረኞች የተሰኘው ቴአትር ይታያል፡፡ በተጨማሪም በቀጣይ ቀናት በብሔራዊ ቴአትር የሚታዩት ማክሰኞ በ11፡30 ሰዓት ሦስቱ አይጦች፣ ረዕቡ በ11፡ 30 ሰዓት የቅርብ ሩቅ ቴአትር፣ ሐሙስ ቀን 11:30 ሰዓት ሸምጋይ ቴአትር፣ አርብ በ11፡30 ሰዓት የሕይወት ታሪክ በብሔራዊ ቴአትር ለጥበብ አፍቃሪያን ለዕይታ ይቀርባሉ፡፡

## የቁጥር ጨዋታ

### የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር። የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል። በመጀመሪያ ከቀኝ በኩል በስተጎን ያለውን ቁጥር ከታች ካለው ቁጥር ጋር እንደምራለን፡፡ ልክ እንደዚሁ በግራ በኩል በስተጎን ያለውን ቁጥር ከላይ ካለው ቁጥር ጋር እንደምራለን፡፡ ከዚያ በኋላ መጀመሪያ ደምረን ያገኘነውን ውጤት፣ በኋላ ላይ ደምረን ካገኘነው ውጤት ጋር እናካፍለዋለን፡፡ አካፍለን ያገኘነው ውጤት የመሃለኛውን ቁጥር መምጣት አለበት፡፡ ለአብነትም የመጀመሪያው ክብ ላይ ያለው የጥያቄ መልስና አሰራር እንዴት እንደሆነ አብረን እንስራው።

54 + 16 = 70 ከዚያ በኋላ 18 + 17= 35 ፤ 70 ÷ 35 = 2 ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት 55 + 35 = 90 ከዚያ በኋላ 26 + 19 = 45 ይሆናል፤ 90 ÷ 45 = 2 ይሆናል፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ መልስ **ሁለት (2)** ይሆናል፡፡




### የዚህ ሳምንት የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት ዕትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# ለኪነ ጥበባዊ ፈጠራ ዕድል የሚሰጠው በዓል

• ኢሬቻ መነሻው ይቅር መባባል፣ ፈጣሪን ማመስገንና ከተፈጥሮ ጋር መስተጋብር መፍጠር በመሆኑ ለኪነ ጥበባዊ ፈጠራዎች ትልቅ መነሻ እንደሆነ ተገልጿል



ፎቶ-ከፋይል

የኢሬቻን እሴቶች በመጠቀም ከተሳሉ ስዕሎች ጥቂቶቹ

በአብርሃም ገብሬ

ወርሃ መስከረም ተፈጥሮ ውበቷን የምትገልጽበት እና ራሷን አጉልታ የምታንጸባርቅበት ወቅት ነው፡፡ የደፈረሱ ወንዞች በመስከረም ይጠራሉ፡፡ ጭጋግ የሸፈናቸው መስኮች በመስከረም ፀአዳ አረንጓዴ ይለብሳሉ፡፡ ምድር በአበቦች ታጌጣለች፡፡ ሰማይ ነጭና ሃምራዊ ልብሷን አገልድማ ትታያለች፡፡

በመስከረም ፈገግ የምትለው ተፈጥሮ፣ ፈገግታዋ ወደ ሰውም ይጋባል፡፡ ይህቺ ተፈጥሮ በሰው ልብ ውስጥም ተስፋን ትጭራለች፡፡ አዲስ ዕይታና አዲስ መሻትን ትፈነጥቃለች። አሮጌውን በመሸኘት የአዲስ ዘመን መምጣትን ታውጃለች፡፡ ተራርቀው የቆዩ ቤተ-ዘመዶችን በማገናኘት፤ የተነፋፈቁ ወዳጆች ናፍቆታቸውን እንዲወጡ ዕድል ታመቻቻለች፡፡

የመስከረም ወር ልዩ ነች፡፡ ተፈጥሮ ዳግም የሚታደስባት፣ ብዙ አይነት ተፈጥሯዊ ቀለሞች የሚታዩባት ናት። በዚሁ ወር የሚከበረው ኢሬቻም ከተፈጥሮ እና ከማህበረሰቡ ህይወት ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች ኢሬቻና በዓሉ የሚከበርበት ወቅት በራሱ ተፈጥሮን፣ ህይወትን፣ ባህልንና ታሪክን መሰረት አድርገው ለሚጠበቡ ከያኒያን ትልቅ መነሳሳትን ይፈጥራል። በዚህ አጭር ዓምድም የኢሬቻ ዕሴቶች ለኪነ ጥበባዊ የፈጠራ ሥራዎች ያላቸው ዕምቅ አቅምና ከያኒያን ይህን ዕሴት በጥበብ ስራዎቻቸው እንዴት ማንጸባረቅ እንደሚችሉ በጨረፍታ ልናስቃኛችሁ ወድደናል፡፡

## ኢሬቻን በጨረፍታ

በኦሮሞ ባህል ጥናት ውስጥ ተመራማሪ የሆኑት መምህር ጌታቸው አበራ ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት አስተያየት፣ የኢሬቻ በዓል የመልካም ነገሮች ሁሉ ምንጭ ለሆነው ለፈጣሪ ምስጋና የሚሰጥበት ቀን ነው። በዚህ ቀን ሕዝቡ ለተደረጉለት መልካም ነገሮች ሁሉ ከልብ የመነጨ ምስጋና ለፈጣሪው ያቀርባል። የተጣሉ ሰዎች እርቅ ያደርጋሉ፡፡ ከዚህ አንጻር በዓሉ የሰላም፣ የፍቅርና የእርስ በእርስ ትስስራችንን የምናጠናክርበት ነው ብለዋል፡፡

በሃሮማያ ዩኒቨርስቲ የታሪክ ተመራማሪ መሐመድ ሐሰን (ዶ/ር) ከዚህ ቀደም ለአዲስ ልሳን ዝግጅት ክፍል በሰጡት አስተያየት፣ ኢሬቻ የሚከበርበት ምክንያት፣ በክረምት ዝናብና የወንዝ ሙላት ተለያይተው የከረሙ ቤተሰቦች የሚገናኙበት እና ፈጣሪውን የሚያመሰግንበት ወቅት በመሆኑ ነው ብለዋል፡፡

እንደ መሐመድ (ዶ/ር) ገለጻ፣ ኢሬቻን በቂምና በጥላቻ ሳይሆን፣ ይቅር በመባባል እና በንፁህ ልብ የሚከበር ነው፡፡ የሰላም፣ የፍቅር፣ የደስታ፣ የህብረትና የአንድነት በዓል ነው፡፡ ቡቃያው አሸቶ፣ ጎምርቶና አዝመራው ደረስኩ ደረስኩ የሚልበት ወቅት ስለሚከበር የተስፋ ጊዜ ነው፡፡

መሐመድ (ዶ/ር) አክለውም፤ “ኢሬቻም ሆነ ሌሎች የአደባባይ በዓላት በባህርያቸው ዜጎችን በአንድ መድረክ የሚያሰባስቡ ናቸው፡፡ ዜጎች በዓሉን ለማክበር በአንድ መድረክ ላይ ሲገናኙ ይበልጥ መገነዛዘብ ይጀምራሉ። የባህል ልውውጥ ከማድረጋቸውም በላይ ኢትዮጵያ በተለያዩ ባህሎች ያሸበረቀች ውብ ሀገር መሆኗን ይረዳሉ። ይሄ ደግሞ በሂደት ይበልጥ የእኔነትን ስሜት አዳብረው፣ በሀገራቸው ባህሎች መኩራት ይጀምራሉ፡፡ ይህ ማለት ሰሜን ውስጥ ያለውን ባህል ደቡብ፤ ደቡብ ውስጥ ያለውንም ደግሞ ሰሜኑ የበለጠ ያውቀዋል፡፡ ልክ እንደዚሁ ምስራቅ ውስጥ ያለው ባህል ምዕራቡ፤ ምዕራብ ውስጥ ያለው ደግሞ የምስራቁ የበለጠ ይገነዘበዋል፡፡ ይሄ ደግሞ በሂደት የእርስ በእርስ ትስስርን ያጎለብታል፡፡ አብሮነትን ያሳድጋል፡፡ ከዚህም አልፎ በሂደት መሰል በዓላት ለማሳደግ እያንዳንዱ ዜጋ ሃላፊነቱን ለመወጣት በራሱ ተነሳሽነት ዕገዛ ያደርጋል” ብለዋል፡፡

## ኢሬቻና ኪነ ጥበብ

የኢሬቻ በዓል መነሻው ይቅር መባባል፣ ፈጣሪን ማመስገንና ከተፈጥሮ ጋር መስተጋብር መፍጠር በመሆኑ ኪነ ጥበባዊ ለሆኑ የፈጠራ ሥራዎች ትልቅ መነሻ ነው፡፡ ከያኒያን የማህበረሰቡ አንድ አካል በመሆናቸው፣ ማህበራዊ ጉዳዮችን ይመለከታቸዋል፡፡ በዚህ ምክንያት የባህል ዕሴቶች የፈጠራ ሥራቸው አካል አድርገው ለመጠቀም ያስችላቸዋል፡፡

በኢሬቻ ሰሞን ብርሃናማ ቀለሞች በብዛት ይታያሉ፤ አደይ አበባ በመስኩ እና በጋራው ላይ ይፈካል። የሰው አለባበስም በቀለምና ጥበብ ያሸበረቀና የደመቀ ይሆናል፡፡ ወንዞች ንጹህ ይሆናሉ፡፡ በዙሪያችን የምናየው ሁሉም ነገር ውብ እና የተለያየ ቀለም ያለው ነው። በመሆኑም የኢሬቻ በዓል አከባበርና የተፈጥሮ ሁኔታ ለከያኒያን ለጥበባዊ ፈጠራቸው መነሻ መሆን ይችላል፡፡

መምህር ጌታቸው በማብራሪያቸው፣ “ኢሬቻን በብዙ መልኩ ሊገለጹ የሚችሉ እሴቶች አሉት፡፡ የኪነ ጥበብ ሰዎችም የበዓሉን መልከ ብዙ እሴቶችና ፋይዳዎች በኪነ ጥበባዊ ሥራዎቻቸው አጉልተው ለማሳየት ምቹ ነው፡፡ ለአብነትም አንድ ዲዛይነር የሆነ ሰው፣ የኢሬቻን መልከ ብዙ እሴቶችን የሚያሳዩ የአልባሳት ዲዛይኖችን መስራት እንደሚችል ሁሉ በዓል ሲከበር ያለው ድባብም ለጥበብ ሰዎች የፈጠራ ስራ ትልቅ መነሻ መሆን ይችላል” ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በ“ሪያሊዝም” የአሳሳል ዘይቤ የሚታወቀው ሰዓሊ ግርማ ቡልቲ ኢሬቻን በኪነ ጥበባዊ ስራዎች ማሳየት የቻለ ከያኒ ነው፡፡ ሰዓሊ ግርማ ከተማሪነቱ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ኢሬቻን የተመለከቱ በርከት ያሉ የስእል ስራዎችን አበርክቷል። የሳላቸውን ስዕሎችም ለዕይታ ማብቃት ችሏል፡፡ የባለፈው ዓመት የኢሬቻ በዓል ለእይታ በቅቶ በነበረው የሥዕል አውደርእይ ላይም አዳዲስ ስራዎችን አቅርቧል፡፡ ስራዎቹም በብዛት ባህል፣ መተሳሰብ፣ ይቅርታ፣ ፍቅር፣ ሰላምና የማህበረሰቡ አጠቃላይ መስተጋብር ላይ የሚያጠነጥኑ ናቸው፡፡ ሰዓሊ ግርማ፤ በኢሬቻ ሰሞን ልዩ አይነት ቀለም፣ ባህል፣ ተፈጥሮ፣ አለባበስ እና ሌሎች ሁነቶች ስለሚታዩ ዕውናዊ የአሳሳል ዘይቤ “Realism Painting” ላይ ትኩረታቸውን አድርገው ለሚሰሩ ሰዓሊያን እና ለሌሎችም ከያኒያን ትልቅ የሃሳብ ምንጭ አድርገው ሊጠቀሙት እንደሚችሉ ለዝግጅት ክፍላችን ተናግሯል፡፡

ሰዓሊ ግርማ በገለጻው፣ እንደ ኢሬቻ ያሉ በዓላት፣ ባህላዊ እና ታሪካዊ የስእል ስራዎች ሲሰሩ ጥናቶች ተደርገው ነው። ጥናቱ ደግሞ ማህበረሰቡን ሙሉ በሙሉ የሚገልጽ መሆን አለበት። ለዚህም ቦታው ላይ በመሄድ ጥናት በሚሰራበት ጊዜ ምእናባዊውን ሳይሆን እውነተኛውን መልክአ ምድር፣ የማህበረሰቡን አለባበስ፣ አመጋገብ፣ በዓል አከባበርና የእለት ተእለት አኗኗር መረዳት ይቻላል፡፡

መምህር ጌታቸውም የሰዓሊ ግርማን ሃሳብ የሚያጠናክር አስተያየት ለዝግጅት ክፍላችን ተናግረዋል፡፡ የኢሬቻን መልከ ብዙ ሀገራዊ ፋይዳዎቹን በመገንዘብ ጥናቶች እየተደረጉ ነው ያሉት መምህር ጌታቸው፣ ለኪነ ጥበባዊ የፈጠራ ሥራዎችና የጥበብ ሰዎች መነሻ ሊሆን የሚችል “ኢሬቻ” የተሰኘ መጽሐፍ በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ተጽፎና በጥናት ማዕከሉ አማካይነት ታትሞ ለንባብ በቅቷል፡፡ መጽሐፉን በቀጣይ በአማርኛና በእንግሊዘኛ ቋንቋዎች አሳትሞ ለተደራሲያን ለማቅረብ ታቅዷል፡፡ ይሄ አይነት የምርምር ስራዎች ማድረግና ማሳተም ኪነ ጥበብን ጨምሮ በሌሎች ዘርፎችም ይቀጥላል ብለዋል፡፡

በኢሬቻ ጊዜ በተለይ በገጠራማ አካባቢዎች የማይለበስ የልብስ አይነት የለም፡፡ ሁሉም ሰው በተለይ በኦሮሚያ ክልል ለበዓሉ ብሎ የሚሰራ ልብስ አለ። በዚህ ልብስ ላይ የሚታዩ ጥበቦችና ቀለሞች በጣም ማራኪ ናቸው፡፡ እነዚህ አልባሳት በራሳቸው ለጥበባዊ ስራዎች መነሻ ናቸው፡፡

ከአልባሳት ባለፈ ዝግጅቱ የሚከበርበት መልካ ወይም ወንዝ አለ። ኢሬቻ መልካ የሚከበረው በወንዝ ዳርቻ ነው። የበጋው ኢሬቻ ወይም ኢሬቻ ቱሉ ደግሞ በተራራ ላይ የሚከበር ነው፡፡ ሁለቱም አንድ የሚያደርጋቸው የምስጋና ቀን መሆናቸው ነው፡፡ ይህ አጋጣሚ ለጥበብ ሰዎች የበዓሉን አከባበር፣ ድባብና በዓሉ የሚከበርበት አካባቢ ተፈጥሮን በማሰናኘት የኢሬቻን ሌላኛው ገጽ ለማሳየት እጅግ ምቹ ነው።

ኢሬቻ ሰላምና መቻቻልን ዓብይ ትኩረቱ በማድረግ በአደባባይ የሚከበር በዓል ነው፡፡ በዓሉ፤ ከማህበራዊ፣ ሃይማኖታዊና ኪነ ጥበባዊ ፋይዳው ባለፈ፤ የቱሪስት መስህብ በመሆን ኢኮኖሚው ላይ የራሱን ሚና መጫወት እንደሚችል ሙያተኞች ይናገራሉ። ከዚህ አንጻር የኢሬቻን መልከ ብዙ ፋይዳዎች በኪነ ጥበባዊ ሥራዎችና በሌሎች ዘዴዎችም አጉልቶ ማሳየት ያስፈልጋል፡፡

# ልጆች፤ ስለ ኢሬቻ ምን ያህል ታውቃላችሁ?



ፎቶ ከገፀ ድር
የኢሬቻ በዓል አከባበር በከፊል

በለይላ መሀመድ

ኢሬቻ በዓመት ሁለት ጊዜ ይከበራል:: ከዚህ ውስጥ ዛሬ በአዲስ አበባ እየተከበረ ያለው ሆረ ፊንፊኔ፣ ነገ ደግሞ በቢሾፍቱ የሚከበረው ሆረ አርሰዴ አንዱ ነው:: እኛም በዚህ ጽሁፍ ስለምንነቱ እና የአከባበር ሂደቱ አንድ ባለሙያ ጋብዘናል፤ ለእናንተ ለልጆች የሚከተለውን ማብራሪያ ሰጥተዋል::

ልጆች እንዴት ናችሁ? አቶ ጌታቸው አበራ እባላለሁ:: በኦሮሞ ባህል ጥናትና ምርምር የሥነ ትውፊት (የፎክሎር) ባለሙያ ነኝ:: የኢሬቻ በዓል ሰማይንና ምድርን እንዲሁም ሁሉንም ፍጥረታት ለፈጠረዉ አንድ አምላክ (ዋቃ) ምስጋና የሚቀርብበት ስርዓት ነው። በክረምት ወራት ተራርቆ ሳይገናኝ የቆየ ዘመድ አዝማድ መስከረም ላይ ይገናኛል። በበዓሉ የሚታደመው ሕዝብም “ክረምቱን በፈጣሪ ፍቃድ የሞላው ውሃ ጎድሎ ከዘመድ አዝማድ አገናኘን” ብሎ ምስጋና ያቀርባል።

ልጆች የኢሬቻ በዓልን ለማክበር የሚወጣው ታአዳሚ እንደ ሳር ወይም አበባ ያለ እርጥብ ነገር በእጁ በመያዝ ነው። እርጥብ ነገር ተይዞ የሚወጣው “ፈጣሪያችን ሆይ አንተ ያጸደቅከው ነው አብቦ ፍሬ ያፈራው:: ለዚህም እናመሰግንሃለን” ለማለት ነው:: ለዚህም ነው የኢሬቻ በዓል በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ “የምስጋና ቀን” በመባል የሚታወቀው::

ልጆች፤ ኢሬቻ የሰላም እና የእርቅ በዓልም ነው:: በኢሬቻ በዓል ላይ የኦሮሞ ሕዝብ ለመላው የሰው ልጅ ሰላምና ደህንነት ፈጣሪውን (ዋቃን) ይለምናል። የተጣላ ታርቆ፣ ቂሙን ትቶ፣ በንፁህ ልቦና ፈጣሪ ንጹህ ወዳደረገው መልካ (የውሃ አካል) ይሄዳል። ለዚህም ነው ኢሬቻ ቀልብ ወይንም ልቦና የሚጸዳበት ልዩ በዓል ተደርጎ የሚታመነው:: ኢሬቻ ፍቅር የሚገለጽበት፣ አንድነት የሚሰበከበት፣ ሁሉንም በእኩል የሚያቅፍ፣ ማንኛውም ሰው መጥቶ ማክበር የሚችለው በዓል ነው::

በዓሉ የሚከበረው ደግሞ በዓመት ሁለት ጊዜ ነው። እነዚህ ሁለት ጊዜ የሚከበሩት የኢሬቻ በዓላት መልካ እና ቱሉ በመባልም ይታወቃሉ:: የመጀመሪያው የክረምት ወራት እንዳበቃ የሚከበረው ኢሬቻ መልካ ሲሆን፤ ይህም በውሃ አካል ዳርቻ የሚከበር ነው:: ኢሬቻ መልካ የኦሮሞ ህዝብ ከጨለማ ወደ ብርሃን ላሸጋገረው አምላክ (ዋቃ) ምስጋና የሚያቀርብበት የምስጋና በዓል ነው::

በዓመቱ አጋማሽ ላይ የሚከበረው የኢሬቻ በዓል ደግሞ፤ ኢሬቻ ቱሉ የሚባል ሲሆን፤ በተራራማ ቦታ ላይ የሚከበር ነው። ኢሬቻ ቱሉ የበጋው የፀሐይ ሃሩር በርትቶ ሰው እና ከብት በሚያቃጥልበት ጊዜ ዝናብ ወቅቱን ጠብቆ እንዲዘንብ የኦሮሞ ሕዝብ ወደ ተራራ ወጥቶ ፈጣሪውን የሚለምንበት ነው:: “ይህን ተራራ የፈጠርከ ፈጣሪ ወቅቱን የሰላም አድርግልን፣ የሰላም ዝናብ አዝንብልን፣ ጎርፍን ያዝልን፣ የተዘራው ፍሬ ያፍራ” እያለ በኢሬቻ ቱሉ ላይ ፈጣሪውን ይለምናል።

ልጆች የኢሬቻ በዓል የራሱ የሆነ የአከባበር ሥርዓት አለው:: ይህም የመልካም ነገር ምኞት መግለጫ የሆነውን እርጥብ ሳር ተይዞ በዝማሬ “መሬሆ ... መሬሆ” እየተባለ ወደ መልካ (ወንዝ) በማቅናት ስርዓቱ ይከናወናል። በዚህ የኢሬቻ ክብረ በዓል ልጆች፣ አባ ገዳዎች፣ ሀደ ስንቄዎች ለበዓሉ የሚለበሱ የባህል አልባሳትን ለብሰው ይወጣሉ::በዓሉ ወደሚከበርበት መልካ (ወንዝ) በሚኬድበት ወቅት መንገድ ላይ በአንድነትና በመከባበር ነው:: ታናሽ ታላቁን እያከበረ የሚጓዝበት ነው::

ልጆች ይህንን ስርዓት በደንብ ማወቅ ይኖርባችኋል:: ለዚህ ደግሞ ስለኢሬቻ ቤተሰቦቻችሁን መጠየቅ፤ የተለያዩ ጽሁፎችንም ማንበብ አለባችሁ እያልን መልካም በዓል ተመኘሁላችሁ::

## 10 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**እራሱ ሳይቀምስ የቆረሰውን ለሌላ ያጎርስ**

**መልስ፡-** ሀ.እጅ

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**ቀይ ሙሽራ፤ በነጭ አጥር ታጥራ**

ሀ. ቪላ

ለ. ምላስ

ሐ. ሆቴል

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ::**


Yabebal Addis
Bureau Head
እንኳን ለ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ!
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ቢሮ ለአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች እና የበዓሉ ታዳሚዎች እንኳን ለ2018 ዓ.ም ኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ እያለ ህብረተሰቡ በዓሉን ምክንያት በማድረግ በሚኖረው የመጓጓዝ ፍላጎትም ሆነ በሚያደርጋቸው ማንኛውም እንቅስቃሴዎች ራሱንና ወገኖቹን ከትራፊክ አደጋ በመከላከል፣ በተለይ አሽከርካሪዎች ኃላፊነት ወስዳችሁ እንድታሽከረክሩ፤ እግረኞችም ተጠንቅቃችሁ በመንቀሳቀስ የትራፊክ አደጋን መከላከል እንደሚገባ እያሳሰበን፤ በዓሉ የሰላም፣ የፍቅር፣ የደስታ እንዲሆን በቢሮውና በራሴ ስም መልካም ምኞቴን እገልፃለሁ፡፡
አቶ ያብባል አዲስ
በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊ


Baankii Hibrat
Hibret Bank
Gamtaan Haa Guddannu!
BAGA AYYAANA
IRREECHAAN
NAGAAN ISIN GAHE!
እንኳን ለኢሬቻ በዓል በሠላም አደረሳችሁ!
FOLLOW US
hibretbank.com.et

# እንኳን ለ2018 ለሆራ ፊንፊኔ እና ለሆራ አርሰዴ የኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ! አደረሰን!



የኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ኢሬቻ በዓል የጋራ ልማታችንንና ሁለንተናዊ ብልፅግናችን የሚፋጠንበት፣ ሰላማችን የሚሰፍንበት፣ የቆየው የመረዳዳትና የአብሮነት ባህላችን የሚጎለብትበትና ለነገ ውብ ተስፋችንና ብልፅግናችን የማይናወጥ መሠረት የምንገነባበት እንዲሆንልን በመመኘት ነው!

የኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ባለፉት ዓመታት እንደ ሆራ ፊንፊኔና ሆራ አርሰዴ ያሉ ባህላዊና ሀይማኖታዊ የአደባባይ በዓላት ፍፁም ሰላማዊ ሆነው እንዲከበሩ በማድረግ ክፍለ ከተማችንን ከፍ ያደረጉና ለህዝባችን ተጨማሪ የገቢ እና የኢኮኖሚ ምንጭ እንዲሆን ከማድረግ በተጨማሪ የህዝብ ለህዝብ ትስስርን የሚያጠናክሩ፣ ብዝሀነትን የኢትዮጵያ ጌጥ የሚያደርጉና ዘላቂ ልማትን በማፋጠን የህዝባችን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ስራዎችን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ።

ውድ የከታማችንና የክፍለ ከተማችን ነዋሪዎች ወንድማማችነትን፣ እህትማማችነትን እና አብሮነትን በሚያጎለብት መልክ ማክበር መቻላችን በጽናት ቆመን አድዋን ድል እንዳደረግነው፣ ሀሳብ የነበረውን የህዳሴ ግድብ በጋራ ገንብተን ለፍሬ እንዳበቃነው፣ በበጀት ዓመቱ የጀመርነው የተስፋ ጉዞና ለህዝባችን የገባነው ቃል ኪዳን እንዲሳካ እንደ ወትሮው ሁሉ ከጎናችን ሆናችሁ ታግዙን ዘንድ ጥሪዬን እያስተላለፍኩ፤ የሆራ ፊንፊኔ እና ሆራ አርሰዴ በዓል የሰላም፣ የጤና የአብሮነትና የብልፅግና እንዲሁም ሁለንተናዊ ሉዓላዊነታችን ተረጋግጦ የሀገራችን እምርታና ማንሰራራት የምናበስርበት እንዲሆንልን እመኛለሁ!!



## መልካም በዓል!

**አቶ ቴዎድሮስ ወልደሚካኤል**
**የኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ዋና ስራ አስፈፃሚ**





አዲስ አበባ አመራር አካዳሚ
ADDIS ABABA LEADERSHIP ACADEMY

# እንኳን ለ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ! አደረሰን!

የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ በ2017 በጀት ዓመት በከተማዋ ስር የሚገኙ ተቋማትን የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም በስልጠና፣ በምርምር፣ በማማከርና በማህበረሰብ አገልግሎት በመገንባት በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል።

በ2018 በጀት ዓመት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ጎሮ አካባቢ እያስገነባ ባለው አዲስ ህንፃ የአቅም ግንባታ ስራውን አጠናክሮ ለማስቀጠልና አዳዲስ አሰራሮችን በመቀየስ ከወትሮው በተለየ መልኩ ዝግጅቱን አጠናቋል። በመሆኑም በከተማዋ የሚገኙ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንድትሆኑ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

**እንኳን ለኢሬቻ ሆራ ፊንፊኔና ለሆራ አርሰዴ፣ የምስጋና በዓል በሰላም አደረሳችሁ።**

**መልካም የኢሬቻ በዓል!**
**የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ**

# ኢሬቻ ለሀገር ማንሰራራት!

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን እንኳን ለ2018 ዓ.ም የይቅርታ፣ የመተሳሰብ ምሳሌ ለሆነው የኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ እያለ መልካም ምኞቱን ይገልፃል።

ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ በከተማ አስተዳደሩ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት በከተማዋ የሚፈጸሙ የደንብ መተላለፎችን እና ህገ-ወጥ ተግባራት በመከላከል፣ መቆጣጠር እና ህጋዊ እርምጃ በመውሰድ ከተማችን ለነዋሪዎቿ ምቹ፣ ማራኪና ሰላማዊ እንድትሆን የማድረግ ስራ አጠናክሮ እየሰራ ይገኛል፡፡

በክብረ በዓሉ ላይ ታዳሚዎች ለከተማችን መልካም ገጽታ ሲባል በልማት ኮሪደሮች፣ በፓርኮች እንዲሁም በተለያዩ አረንጓዴ ቦታዎች ጉዳት እንዳይደርስ ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ የበኩሉን ኃላፊነት በመወጣት እና በቦታው ላይ ለሚገኙ የጸጥታ አካላትና የበዓሉ አስተባባሪዎች በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት ተገቢውን ትብብር በማድረግ የሰላም፣ የፍቅርና የእርቅ መገለጫ የሆነውን የኢሬቻ በዓል በአንድነት እናክብር።





## መልካም በዓል!

ለማንኛውም የደንብ መተላለፎች ጥቆማ ነፃ የስልክ መስመር 9995 ይጠቀሙ!

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለስልጣን



# ትውልዱ

## “መንግስት ሊሰራቸው ያሰባቸውን ሜጋ ፕሮጀክቶች በሁለንተናዊ መልኩ መደገፍ ይገባዋል”

**የታሪክ ተመራማሪው ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ**



ፎቶ- ከገፀ ድር
የታሪክ ተመራማሪ ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ

**በሄለን ጥላሁን**

ኢትዮጵያ በትውልድ ቅብብሎሽ እየተገነባች የመጣች ሀገር ናት፡፡ ሀገሪቱን አሁን ካለችበት ደረጃ ለማድረስ በየዘመኑ የነበረው ትውልድ የራሱን አሻራ አሳርፎአል፡፡ ሆኖም የሀገር ግንባታ ሂደት በመሆኑና በአንድ ትውልድ ብቻ ተሰርቶ ስለማያልቅ ቀጣይነት ያለው ስራ መስራት አስፈላጊ መሆኑን ምሁራን ይስማሙበታል፡፡

የትውልድ ድምር ውጤት በሆነችው ኢትዮጵያ፤ የዛሬው ትውልድ የትላንት ወራሽና ባለአደራ ብቻ መሆን የለበትም። የተሻለ ዛሬና ነገን የመፍጠር ኃላፊነት አለበት፡፡ ስለዚህ ያለፈውን ታሪክ ከመዘከር ባለፈ ለተተኪው የተሻለች ሀገር ለማስተላለፍ በሁለንተናዊ መልኩ መስራት ይጠበቅበታል፡፡

በጥበብ እድገት ቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተወካይ ምክትል ርዕሰ መምህር እሱእንዳለ በቀለ ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት አስተያየት፣ ኢትዮጵያ በቀድሞ ታሪኳ የምትዘከር ብቻ መሆን የለባትም፡፡ የድል አድራጊነት ጉዞዋን በተለያዩ አግባቦች ማስቀጠል ያስፈልጋል፡፡ የዛሬ አስራ አራት ዓመት ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን አንድ ብለን መሰረት ስንጥል የይቻላል መንፈስን በማንገብ በሀሳብ፣ በጉልበትና በገንዘብ ድጋፍ አድርገናል፡፡ በውጤቱም ዳግም ዓድዋን የማጣጣም እድሉን አግኝተናል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

“ግድቡ የኔም ነው” በሚል ስሜት በርካታ ልጆች ወላጆቻቸው ከሚሰጧቸው ገንዘብ ቆጥበው ቦንድ ገዝተዋል፡፡ ይህ አይነቱ ሀገራዊ ስሜት በቀጣይ የጋራ ጉዳዮቻችን ላይም ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አክለዋል።

የስልክ መሸጫ ሱቅ ከፍቶ እየሰራ የሚገኘው ሌላኛው አስተያየት ሰጪ ወጣት ሃይሉ ደቻሳ በበኩሉ፣ “ሀገራችን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የጀመረችው የልማት ስራ እጅግ የሚያበረታታ፤ ‘እንዲህም ይቻላል እንዴ’ የሚል ስሜት የጫረ ነው፡፡ ሰርቶ የሚያሰራ መሪ ካለን እኛም የሱን አሻራ የመከተል ሃላፊነት አለብን፡፡ ትውልድም ጥሩ አርዓያ የሚሆነው ካገኘ በተከፈተው በር ለመቀጠል የሚቸግረው ነገር አይኖርም የሚል እምነት አለኝ” ሲል ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ማጠናቀቅ መቻሉን በማሳያነት በማንሳት ተናግሯል።

የአሁኑ ትውልድ ያለፈውን ታሪክ ከመዘከር ባለፈ አሁን ላይ ምን እየሰራ ነው? በቀጣይስ ምን ይጠበቅበታል? በሚሉ ነጥቦች ዙሪያ የታሪክ ተመራማሪው ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ ለዝግጅት ክፍላችን ሀሳባቸውን አጋርተውናል፡፡ በማብራሪያቸው፣ “በታሪክ ሂደት ውስጥ ኢትዮጵያውያን በመተባበራቸው ያስመዘገቧቸው የተለያዩ ድሎች አሏቸው፡፡ በተደጋጋሚ የተቃጣባቸውን የውጪ ወረራ ‘አሻፈረኝ’ በማለት ለመላው ጥቁር ህዝቦች የነጻነት ተምሳሌት መሆን ችለዋል፡፡ በዚህም በህዝቦች መተባበርና መደጋገፍ ለሀገራቸው ነጻነት የተዋደቁባቸውን ድንቅና አኩሪ ድሎች በታሪክ መዝገብ ጽፈዋል፡፡ ህዝቦቿ የቱንም ያህል የፖለቲካ ልዩነት ቢኖራቸውም የጋራ በሚሏቸው እሴቶቻቸው ላይ ፅኑ አቋም አሏቸው፡፡

የጋራ ትርክቶቻችን ከሆኑት መካከል የዓድዋ ድል አንዱ ነው፡፡ በዚህ የሀገርን ሉዓላዊነትና ነፃነት የመጠበቅ ሃላፊነት ውስጥ ሁሉም የየድርሻውን በመወጣት ድል ማስመዝገብ ተችሏል። ያለፉ ታሪኮቻችንን መዘከር ከፊታችን ለሚጠብቁን ትላልቅ ሀገራዊ ጉዳዮች ብርታት ይሆነናል፡፡

የአሁኑ ትውልድ ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት አንስቶ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገኙ ተማሪዎች ለህዳሴ ግድብ የአቅማቸውን ድጋፍ ማድረግ ችለዋል፡፡ የሀገርን ሰላም ለማስጠበቅ ብሎም እርስ በእርስ ያለንን ግንኙነት የተሻለ በማድረግ በንግግር የሚያምን ማህበረሰብ የመፍጠር ትልም እውን እንዲሆን ሀገራዊ ምክክር መድረክ ተጠቃሽ ነው፡፡ ሂደቱን የሚያስተባብረው የኢትዮጵያ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ በተለያዩ ክልሎች በማቅናት ሃሳቦችን ብሎም ቅሬታ የፈጠሩ ጉዳዮችን አጀንዳ አሰባስቧል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ወጣቱ ቀጥተኛ ተሳታፊ በመሆን ሀገር ለወጠነቻቸው ትላልቅ አጀንዳዎች መፈፀም ቀኝ እጅ መሆን ይጠበቅበታል” ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ምረቃ ላይ ንግግር ያደረጉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፤ “ታሪክ ሰምተናል፤ ታሪክ አይተናል፤ ታሪክ ተምረናል፤ ዛሬ ፈጣሪ የመረጠው ትውልድ መሆን ስለቻልን ታሪክ ሰርተን፤ ታሪክ ላይ ቆመን ለማውራት በቅተናል” ብለዋል፡፡ የትላንትናውን ታሪክ በመናገር ጊዜ አናባክንም፤ የህዳሴን ፋይል በመዝጋት በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት ሌሎች በርካታ ስራዎች ለመከወን እንዳቀዱም ጠቁመዋል፡፡

የህዳሴ ግድብን የሚስተካከል ለሠላማዊ ዓላማ የሚውል የኑክሌር ማብላያ ስራ እንደሚጀመር የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በአፍሪካ ግዙፍ የአየር መንገድ ግንባታ ስራም እንደሚከናወን ገልፀዋል፡፡ በጥቂት ሳምንታት የነዳጅ ፋብሪካ ምረቃ በማካሄድ፤ በዕለቱ አስር እጥፍ የሚሆነው 2ኛው የጋዝ ፋብሪካ ግንባታን በማስጀመር የነዳጅ ባለቤት የመሆን የዘመናት ህልማችን እውን የሚሆንበት የነዳጅ ማጣሪያ ስራ እንደሚጀምር መግለፃቸው ይታወሳል፡፡

እንዲሁም የማዳበሪያ ፋብሪካ ግንባታ ስራ፤ በቀጣይ አምስት ዓመት 1 ነጥብ 5 ሚሊየን ቤቶች ግንባታ፤ በድምሩ ከ30 ቢሊየን በላይ ዶላር ወጪ የሚጠይቁ፣ አፍሪካውያንን ቀና የሚያደርጉ እና የኢትዮጵያን ብልፅግና የሚያበስሩ ሜጋ ፕሮጀክቶች እንደሚሰሩ ገልፀዋል፡፡

ረዳት ፕሮፌሰር አህመድም፤ “በተገፋን መጠን የማንገፋ፣ በተጫነብን መጠን የማንሸነፍ አይነት ሰው መሆን ያስፈልጋል። ክብራችንን አሳልፈን የማንሰጥ ሰዎች መሆን አለብን። የትውልድ ቅብብሎሽን እውን ለማድረግ ሲታሰብ ኃላፊነቱ የብዙሃኑ ነው፡፡ ትውልድን የመገንባት ኃላፊነት ለአንድ አካል ብቻ የሚተው አይደለም። ጉዳዩ ለመንግስት፣ ለመምህራን፣ ለሐይማኖት ተቋማት አልያም ለወላጅ ብቻ የሚተው ኃላፊነት አይደለም፡፡ ሁሉም የሚሳተፍበት እና ፍሬውን አብሮ የሚያጣጥምበት መሆን ይገባል” ሲሉ አስረድተዋል፡፡

የትውልድ ግንባታ ከቤተሰብ ይጀምራል፡፡ አንድ ህፃን ወላጆቹ የሚያደርጉትን አተኩሮ ይመለከታል። ለምሳሌ ያክል ወላጆቹ አንባቢ ከሆኑ እሱም ለማንበብ ጥሩ ፍላጎት ይኖረዋል። በሌላ በኩል ቤተሰቦቹ ሱሰኛ ከሆኑ እርሱም ያንኑ ለማድረግ ይሻል፡፡ ከዚህ አኳያ ቤተሰብ ልጆቹ በስነ ምግባር የታነፁ፣ ጠንካራ ሰራተኛና ሀገራቸውን የሚወዱ እንዲሆኑ ግዴለሽነት ሳያሳይ በትዕግስት መስራት እንደሚጠበቅበት ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ ያነሳሉ፡፡

ትውልዱ የተሻለ ታሪክ ሰሪ እንዲሆን በማንነቱ የሚተማመንና የሚኮራ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ለዚህም በራስ አቅም ለሚሰሩ ስራዎች ዋጋ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ በተለይ ሀገር በቀል እውቀቶችን ጥቅም ላይ በማዋል ሁሉንም ጉዳይ ባለቤት እንዲኖረው ማስቻል ያስፈልጋል፡፡ በእድሜ የገፉ አባቶች ለታዳጊዎች የህይወት ተሞክሯቸውን የሚያስረዱበት አግባብ እንዲኖር ማመቻቸት እንዲሁም ደግሞ በስራ የሚያምን ትውልድ እንዲኖር የፈጠራ ስራዎችን ከማበረታታት ባሻገር ስራ ጠባቂ ትውልድ እንዳይኖር መንገዶች ቢመቻቹ መልካም እንደሚሆን አብራርተዋል፡፡

> **ትውልዱ የተሻለ ታሪክ ሰሪ እንዲሆን በማንነቱ የሚተማመንና የሚኮራ መሆን ይጠበቅበታል። ለዚህም በራስ አቅም ለሚሰሩ ስራዎች ዋጋ መስጠት ያስፈልጋል**

ከአሁኑ ትውልድ ሀገራችን በርካታ ነገር ትጠብቃለች የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ፤ ድህነትን የሚጠየፍ ትውልድ በሚማረው ትምህርትና በሚሰራው ስራ ውጤታማ ለመሆን ፅኑ አቋም ሊኖረው ይገባል፡፡ የመመረቂያ ጥናታዊ ፅሁፎች መደርደሪያ ከማሞቅ በዘለቀ በትክክል መሬት ላይ ወርደው ጥቅም እንዲሰጡ ማድረግ እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

እንደ ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ ገለፃ፤ ትውልዱ ዘመኑ ከሚያስገኛቸው የሳይንስና ቴክኖሎጂ ግኝቶች ጋር በመናበብ ዓለም የደረሰባቸውን የፈጠራ ስራዎች ወደራስ በማምጣት ለማህበረሰቡ ችግር ፈቺ ተግባራትን መከወን ይጠበቅበታል፡፡ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ግኝቶች ለበርካታ ዜጎች እፎይታን የፈጠሩ ናቸው፡፡ ጊዜን፣ ጉልበትን እንዲሁም የሀብት ብክነትን የሚቀንሱ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ተደራሽ በተደረጉ ልክ ወደ ሌሎች የልማት አጀንዳዎች ትኩረት ለማድረግ እድል ይፈጥራል፡፡

በተጨማሪም ለሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ግብዓት የሚሆኑ ሃሳቦችን በመሰንዘር እንዲሁም በቀጣይ የኮሚሽኑ አጀንዳ ላይ ንቁ ተሳትፎ የማድረግ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ እንደ ሀገር ያስመዘገብናቸውን ድሎች ተከትሎ መንግስት በቀጣይ ለመስራት ያሰባቸውን ሜጋ ፕሮጀክቶች፣ የባህር በር የማግኘት ጉዳይን ትውልዱ በሁለንተናዊ መልኩ መደገፍ እንደሚገባው ሃሳባቸውን አጋርተዋል፡፡

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርብ

# የመንገድ ሀብቶችን ለመጠበቅ ምን እየተሰራ ነው?

**በላዋይሽ ቢተው**

የመንገድ መሰረተ ልማት መስፋፋት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ከማሳደግ ባሻገር የህብረተሰቡን ማህበራዊ ግንኙነትን ለማጠናከር እና የግለሰቦች የእለት ከእለት እንቅስቃሴ ውጤታማ እንዲሆን በማድረግ ረገድ የማይተካ ድርሻ አለው። መንገዶችን ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ ለማድረግ በታላቅ ትጋት እየሰራ የሚገኘው የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን ባለፉት ዓመታት ከፍተኛ በጀት በመመደብ ትላልቅ የመንገድ ፕሮጀክቶችን ገንብቶ ለአገልግሎት በማብቃት የህበረተሰቡን የመንገድ መሰረተ ልማት ጥያቄዎች ሲመልስ ቆይቷል፡፡

ይሁንና የሚገነቡ የመንገድ መሰረተ ልማቶችን በተገቢው ሁኔታ መጠቀምና በአግባቡ በመንከባከብ ረገድ ግን ክፍተቶች ይታያሉ፡፡ በግለሰቦች ቸልተኝነት እና ህገወጥ ተግባራት ሳቢያ በከፍተኛ በጀት የተገነቡ የመንገድ መሰረተ ልማቶች ለጉዳት ሲዳረጉ ይስተዋላል። የትራፊክ አደጋ፣ በመንገድ ላይ ንግድ፣ የመኪና እጥበት፣ የጋራዥ ስራዎች፣ ጭነታቸውን በአግባቡ ሳይሸፍኑ እና ከተፈቀደላቸው የክብደት መጠን በላይ በመጫን የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች ለመንገድ መሰረተ ልማቶች መጐዳት አስተዋፅዖ ከሚያደርጉት ዋንኞቹ ናቸው።

በተመሳሳይ በድሬኔጅ መስመሮች ላይ ደረቅ ቆሻሻዎች መጨመር ሌላኛው ህገወጥ ተግባር ሲሆን መስመሮቹ በአግባቡ አገልግሎት እንዳይሰጡ እንቅፋት እየፈጠረ ይገኛል፤ ይህም በከተማ ላይ አልፎ አልፎ ለሚከሰተው የጎርፍ አደጋ መንስኤ እየሆነ ይገኛል፡፡

በ2017 በጀት ዓመት በተለያዩ ምክንያቶች ባለስልጣኑ በሚያስተዳድራቸው የመንገድ ሀብቶች ላይ ጉዳት የደረሰ ቢሆንም በትራፊክ አደጋ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል፡፡ በበጀት ዓመቱ በመንገድ ሀብት ላይ 195 የትራፊክ አደጋ ደርሷል፤ ከደረሰው አደጋ 154 በቀለበት መንገዶች ላይ ሲሆን 41 ከቀለበት መንገድ ውጪ ባሉ የመንገድ መሰረተ ልማቶች ላይ መድረሱን የባለስልጣኑ የመንገድ ሀብት ዳታቤዝ ሪፖርት ይጠቁማል። በአጠቃላይ በደረሰው አደጋ ግምት 6 ነጥብ 7 ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ የመንገድ ሀብት ላይ ደርሷል፡፡ በተለይም በመንገድ አጥር ብረት ላይ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ጉዳት መመዝገቡን የባለስልጣኑ



ከመንገዶች ባለስልጣን
በአሽከርካሪዎች ቸልተኝነት እና ህገወጥ ተግባራት ሳቢያ የመንገድ መሠረተ ልማቶች ለጉዳት ይዳረጋሉ



ከመንገዶች ባለስልጣን
በማንሆል ክዳን ላይ የደረሰ ጉዳት



ከመንገዶች ባለስልጣን
በመንገድ ላይ ውሀ እየለቀቀ የሚጓዝ ሚክሰር የጫነ ተሽከርካሪ

የመንገድ ሀብት የዳታ ቤዝ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በመንገድ መሰረተ ልማቶች ላይ የሚደርስ ጉዳት በህብረተሰቡ እንቅስቃሴ ላይ ተፅዕኖ ከመፍጠሩ ባሻገር በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንደሚያደርሱ በባለስልጣን መ/ቤቱ መንገድ ሀብት አስተዳደር መከትል ዋና ዳይሬክተር ኢንጅነር መህመድ አወል ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም የመንገድ ሀብት ደህንነት ለመጠበቅ ባለስልጣኑ የተለያዩ የመፍትሔ እርምጃዎች በመውሰድ የመንገድ መሰረተ ልማቶችን ከጉዳት ለመከላከል ከሚያከናውናቸው ተግባራት መካከል ከባቢያዊ ቅኝት፣ የመንገድ ደህንነት ጥናት እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ዝግጅቶች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በቀጣይ የመንገድ አጠቃቀም መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ከባቢያዊ ቅኝት የመንገድ መሰረተ ልማቶች ያሉበትን ሁኔታ ለማወቅ የሚያግዝ ሲሆን በመንገድ ሀብት ዘርፍ ስር ባሉ አምስት ቅርንጫፍ ቢሮዎች ባሉ መሀንዲሶች አማካኝነት በየሳምንቱ ለተወሰኑ ቀናቶች የሚደረግ ነው፡፡ የመስክ ምልከታው በመንገድ መሰረተ ልማቶች ላይ ጉዳት የሚያደርሱ አካላት ላይ ቁጥጥር ለማድረግ፣ ጉዳት እየደረሰ ከሆነ ማስጠንቀቂያ ለመስጠት እና መቀጣት ያለባቸውን ለሚመለከተው አካል ለማሳወቅ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

በተመሳሳይ ባለስልጣኑ በየጊዜው የመንገድ ዳሰሳ ጥናት በማከናወን መንገዶች ያሉበትን ሁኔታ ይከታተላል። በክትትሉ መሰረት የመንገዶችን የጉዳት መጠን በመለየትና ለከፋ ጉዳት ሳይዳረጉበፍጥነት ጥገና እንዲደረግላቸው በማድረግ አገልግሎት እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡

የግንዛቤ ማስጨበጫ ዝግጅቶች ባለስልጣኑ የመንገድ ሀብት ደህንነትን ለማስጠበቅ ከሚያከናውናቸው ስራዎች መካከል ተጠቃሽ ነው። በዝግጅቶቹም ባለስልጣኑ ህብረተሰቡ ለመንገድ መሰረተ ልማቶች እንክብካቤና ጥበቃ እንዲያደርጉ ተገቢውን ግንዛቤ ለመፍጠር ይጠቀምባቸዋል፡፡ ለዓላማው መሳካት ባለስልጣኑ ከክፍለ ከተሞች እና ሌሎች አካላቶች ጋር በቅንጅት በመስራት የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮችን ያዘጋጃል፡፡ እንደ ማሳያ "አዲስ አበባ ውብ እና ፅዱ መንገድ እንዲኖራት እንሰራለን" በሚል መሪ ቃል ባለስልጣኑ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ደጋፊዎች ማህበር ጋር በመተባበር ያከናወነው የመንገድ ጽዳት መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህ መሰሉ መድረክ በህብረተሰቡ ዘንድ በመንገድ ደህንነት ዙሪያ ግንዛቤ ለመስጠት ጠቀሜታው የላቀ በመሆኑ በቀጣይም ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡ በመሰል ተግባራቶች ላይ ህብረተሰቡን ተሳታፊ በማድረግ ለመንገድ መሰረተ ልማቶች ደህንነት መጠበቅ በባለቤትነት እንዲሰራ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን ኢንጂነር መህመድ ይናገራሉ፡፡

ባለስልጣኑ የግንዛቤ ሰጪ ዝግጅቶችን ከማከናወን ባሻገር የተለያዩ የሚዲያ አማራጮችን በመጠቀም በመንገድ ሀብት አጠቃቀም ላይ መልእክቶችን ለማህበረሰቡ ተደራሽ ያደርጋል፡፡ በተለይ በበዓላት ወቅት በመንገድ ሀብት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ሊደረጉ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች ላይ በመገናኛ ብዙሀን መረጃ በመስጠት በየጊዜው ግንዛቤ መፍጠር መቻሉንም ነው ኢንጂነር መህመድ የሚናገሩት፡፡

ደንብ በመተላለፍ በመሰረተ ልማቶች ላይ ጉዳት በሚያደርሱ አካላት ተገቢውን እርምጃ በደንብ ማስከበር ባለስልጣን እየተወሰደባቸው መሆኑን የሚናገሩት ኢንጂነር መህመድ ናቸው፡፡ በቀጣይ ባለስልጣኑ በሚያስተዳድራቸው የመንገድ መሰረተ ልማቶች ላይ ጉዳት የሚያደርሱ አካላትን በራሱ መቅጣት የሚችልበትን የመንገድ ሀብት አጠቃቀም ደንብ ባለስልጣኑ አዘጋጅቶ በፍትህ ቢሮ ምልከታ እየተደረገበት እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ "ደንቡ ሲፀድቅ መንገዶች ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች ባለስልጣኑ በራሱ ለመቅጣት ፍቃድ ስለሚያገኝ ለሚያከናውነው የመንገድ መሰረተ ልማቶች ደህንነትን የቁጥጥር ስራ ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል ብለዋል"፡፡ "የመንገድ መሰረተ ልማቶችን ደህንነት ለመጠበቅ ባለስልጣኑ ከሚወስዳቸው እርምጃዎች በተጨማሪ የህብረተሰቡን ንቁ ተሳትፎ ይፈልጋል፡፡ ህብረተሰቡ በመንገድ መሰረተ ልማቶችን በመጠበቅ ሀላፊነቱን ሊወጣ ይገባል" የሚሉት ኢንጅነር መህመድ የመንገድ ተደራሽነት ከፍ ለማድረግ በመንገድ ግንባታ ስራዎች ላይ ንቁ ተሳትፎ ሊያደርግ እንደሚገባም ነው የገለፁት።

የመንገድ መሰረተ ልማቶች በህዝብ ሀብት የሚገነቡ እንደመሆናቸው መጠን ህብረተሰቡ በመንገዶች ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ተግባራት ሲፈፀሙ ሊከላከል እና ለሚመለከተው የህግ አካላት ጥቆማ ሊደርግ ይገባል ሲሉም ኢንጅነር መህመድ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡





አዲስ አበባ
Addis Ababa
The Vibrant Hub of Africa

## የእንኳን ለ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል አደረሳቹሁ! አደረሰን!

ለከተማችን ነዋሪዎች እንዲሁም ለመላው ኢትዮጵያውያን በሙሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቱሪዝም ኮሚሽን እንኳን ሕብረ ብሔራዊነት የሚንፀባረቅበት ሁሉም በአንድነትና በእኩልነት ለሚያከብረው ታላቁ የኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ፣ አደረሰን እያለ መልካም ምኞቱን ይገልፃል፡፡

የአዲስ አበባ ቱሪዝም ኮሚሽን ከተማችንን የሚመጥን አለም አቀፍ ተወዳዳሪ መሆን የሚያስችል የመዳረሻ ልማትን እና የኮንፈረንስ ማዕከላትን በማልማትና በማስፋፋት የሀገር ውስጥና የአለም አቀፍ ቱሪስቶች መናኸርያ እንድትሆን፤ የከተማችን ነዋሪ ከዘርፉ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ በትኩረት ይሰራል፡፡

መዲናችን አዲስ አበባ የኮንፈረንስና የቢዝነስ ቱሪዝም ማዕከል እንድትሆን፣ ከጊዜው ጋር የሚሄድ አገልግሎት የመስጠት፣ በቴክኖሎጅ የታገዘ የግብይትና ፕሮሞሽን ስራ በመስራት የቱሪስት ቁጥርና ገቢ እንዲጨምር ኮሚሽናችን በትኩረት እየሰራ ይገኛል፡፡

ስለሆነም ሀገራችን ኢትዮጵያ የብዙ ባህሎችና እሴቶች ውበት ማሳያ ባለቤት መሆኗ በዓሉን ለማክበር የሚመጡ ቱሪስቶች በኢትዮጵያዊ የእንግዳ አቀባበል ጨዋነት ተቀብለን ባህሎቻችንን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር የምናስተዋውቅበት መድረክ ይሆናል ፡፡

ኢሬቻ ለሀገር ማንሰራራት!

**መልካም በዓል!**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቱሪዝም ኮሚሽን ኮሚሽነር ሁንዴ ከበደ**



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ
BUREAU OF JUSTICE

## እንኳን ለ2018 ዓ.ም ለኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ፡፡

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትሕ ቢሮ ኢሬቻ የአንድነት፣ የመተሳሰብ፣ የወንድማማችነት እና የእህትማማችነት መገለጫ በዓል በመሆኑ ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል በዓሉ የሰላም፣ የጤና፣ የፍቅር እንዲሆን ይመኛል!**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

**ፍትሕ ቢሮ**



## እንኳን ለሆራ ፊንፊኔ ኢሬቻ በዓል በሠላም አደረሳችሁ!

በዓሉ ያለአደጋ ክስተት ተከብሮ እንዲያልፍ ኮሚሽናችን በሁሉም አገልግሎቶቹ በቂ ዝግጅት ማድረጉን እየገለጽኩ መላው የበዓሉ ታዳሚያዎች ከኮሚሽን መስሪያ ቤታችን እየተላለፉ የሚገኙ የጥንቃቄ መልዕክቶችን እንዲተገብር አሳስባለሁ።

**አህመድ መሀመድ**
**የእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር**

**ለእሳትና ለሌሎች ድንገተኛ አደጋዎች**
**እንዲሁም ለአንቡላንስ አገልግሎቶች በ939 ፈጥነው ያሳውቁ!**

## እንኳን ለ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ! አደረሰን!

የኦሮሚያ ልማት ማህበር የአረንጓዴ አሻራ ፓርኮችን በማቋቋምና በርካታ ችግኞችን በመትከል ያለበትን ሀላፊነት እየተወጣ ይገኛል።

በተጨማሪም የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እንዲሁም ሌሎች በርካታ ስራዎችን ለበርካታ ዓመታት ሰርቷል። አሁንም በተለያዩ የልማት ዘርፎች ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረገ የሚገኝ ሲሆን የኢሬቻ በዓል የሰላም፣ የደስታና የፍቅር እንዲሆን ይመኛል።



# መልካም የኢሬቻ በዓል
# የኦሮሚያ ልማት ማህበር

## እንኳን ለ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል አደረሳችሁ! አደረሰን!

**ከሁሉ አስቀድሜ የሰላም፣ የእርቅና የአብሮነት መገለጫ ለሆነው የኢሬቻ በዓል እንኳን በሰላም እና በጤና አደረሳችሁ/አደረሰን ለማለት እወዳለሁ።**

ኢትዮጵያ የራሷ እሴትና ትውፊት ያላት፤ በርካታ ሀገር በቀል እምነቶችና ጥንታዊ ሀይማኖቶች ተቻችለው በአንድነት የሚኖሩባት የብዝሃነት ምድር እንደሆነች ይታወቃል።

ኢሬቻ የኦሮሞ ሕዝብ ከዘመን ወደ ዘመን በሰላም ላሸጋገረው አምላክ ምስጋና የሚያቀርብበት ልዩ በዓል ነው። ኦሮሞ ከገዳ ስርዓት በወረሰው እሴት መሠረት ክረምቱ አልፎ መስከረም ሲጠባ የክረምቱን ጨለማ አሳልፈህ ማሳውን አሳምረህ፣ ብርሀን ስላሳየኸን ፈጣሪ ምስጋና ይግባህ ብሎ እርጥብ ሳር በመያዝ ወደ መልካ(ወንዝ) በማቅናት ኢሬቻን ያከብራል።

የለውጡ መንግስታችን ባለፉት ሰባት ዓመታት ኢሬቻና መሰል ጠቃሚ በዓላት ህብረ-ብሔራዊ አንድነታችንን በሚያጠናክር መልኩ ትውፊታቸውን ጠብቀው ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲሸጋገሩ ለማድረግ ከህዝቡ ጋር በመተባበር በልዩ ሁኔታ ሲሰራ ቆይቷል/እየሰራም ይገኛል።

ሁላችንም እንደምናውቀው በዓሉን ለማክበር በ100ሺዎች የሚቆጠሩ ህዝቦች ወደ ከተማችን ገብተው በሚወጡበት ጊዜ በሆቴልና ንግድ ዘርፍ ከተሰማራው ጀምሮ በተለያዩ የገቢ ማስገኛ ተግባራት ላይ የሚገኙ የከተማችን ነዋሪዎች በንግዱ ዘርፍ ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል።

የዘንድሮው ሆራ ፊንፊኔ በዓል ታላቁ የህዳሴ ግድባችንን በተባበረ ክንዳችን አጠናቀን ባስመረቅንበትና በዚህም ሀገራችን ኢትዮጵያ በቀጠናው ያላትን ጂኦ-ስትራቴጂካዊ ቁመና ማደስ በጀመረችበት ማግስት የሚከበር መሆኑ የተለየ ያደርገዋል። ይህም የማንሰራራታችን መገለጫ የሆነው የህዳሴ ግድባችንን ማጠናቀቃችን ኢሬቻና መሰል በዓላት ህብረ-ብሔራዊ አንድነታችንን በማጎልበት ጠንካራ ሀገረ-መንግስት ለመገንባት የሚኖራቸው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑን ከግምት ውስጥ አስገብተን በዓላቱን ይበልጥ ለማስተዋወቅ ጠንክረን እንድንሰራ ያደርገናል።

ሌላው የዘንድሮውን ኢሬቻ በዓል የተለየ የሚያደርገው በሁለት ዙር በተከናወነው የኮሪደር ልማትና የወንዝ ዳርቻ ልማት ከተማችን አዲስ አበባ ለነዋሪዎቿ ምቹ፣ ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጪ ሀገር ጎብኚዎች ደግሞ ምርጧ የቱሪስት መዳረሻ ከተማ ማድረግ በቻልንበት ጊዜ ላይ የሚከበር መሆኑ ለበዓሉ ልዩ ድባብ እና ምቾት የሚፈጥር መሆኑ ነው።

የዘንድሮው የኢሬቻ በዓል ልክ እንደ ሁልጊዜው ህብረ-ብሔራዊ አንድነታችንን የምናጠናክርበትና አብሮነታችንን አጉልተን የምናሳይበት የሰላም፣ የዕርቅና የብልፅግና እንዲሆንልን እመኛለሁ።




**አቶ ታረቀኝ ወርቅነህ**
**የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈጻሚ**



## መልካም በዓል!




እንኳን ለ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል
በሰላም አደረሳችሁ!
አደረሰን!

የሚለው የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ
ከተማ በዓሉ የሰላም እና የፍቅር
እንዲሆን ይመኛል

**ወ/ሮ ካባ መብራቱ**
**የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ**

## የመሻገር... ከገጽ 19 የዞረ

እስከ ደቂቅ፣ ብሔር፣ ሃይማኖት፣ የፖለቲካ አመለካከትና ሌሎች ልዩነቶች ሳይገድቧቸው ገንዘብ በማዋጣት፣ በጉልበት፣ በሞራልና በዲፕሎማሲ ታይቶ የማይታወቅ ተሳትፎ አድርገዋል፡፡

ሌላው ባለፉት ዓመታት በትኩረት የተሰራበትና ለውጥ የመጣበት የስንዴ ልማት ነው፡፡ ለዘመናት ኢትዮጵያ የስንዴ ፍላጎቷን የምታሟላው ከውጭ በመሸመት፣ በእርዳታና ልመና ነበር፡፡ ግርማ (ዶ/ር) እንደሚገልፁት፤ በስንዴ ልማት ህዝብን በሰፊው በማሳተፍ በመሰራቱ ከውጭ የሚሸመተውን ስንዴ ማስቀረት ተችሏል። ቀላል የማይባሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ህይወትም መቀየር ተችሏል፡፡

አዳዲስ የቱሪዝም መዳረሻዎችን በማልማት፣ በአረንጓዴ አሻራ፣ በኮሪደር ልማት ከተሞችን ለስራና ለኑሮ ምቹ እንዲሆኑ ለማድረግ በተደረጉ ጥረቶች ውጤት ማምጣት ተችሏል፡፡ የተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያላቸው ፕሮጀክቶችን በአጭር ጊዜ ማከናወን ተችሏል፡፡

አዲስ አበባ፣ አርባምንጭ፣ ባህርዳር፣ ጎንደር፣ ሀዋሳና ሌሎች ከተሞችን ብናይ የዛሬ ሁለት ዓመት የሚያውቃቸው ሰው ዛሬ ቢያያቸው አያውቃቸውም፡፡ በኮሪደር ልማት ውብ፣ ፅዱና ለኑሮ ምቹ ሆነዋል። ይህም በቀን ብቻ ሳይሆን በሌሊትም ጨምር መስራት በመቻሉና የስራ ባህልን በመቀየር የተገኘ ነው፡፡ በየጊዜው እያደገ እንዲሄድ ቢደረግ ከዚህም በላይ ውጤት ማምጣት እንደሚቻል ግርማ (ዶ/ር) ያስረዳሉ፡፡

የፎክሎር መምህርና ተመራማሪው ግርማ (ዶ/ር) እንደሚገልፁት፤ ሰዎች ኢሬቻንና የተለያዩ በዓላትን በነቂስ ወጥተው በመሰባሰብ እንደሚያከብሩት ሁሉ፤ ለልማትና አንድነት እንዲነሳሱ ማቀድ ያስፈልጋል፡፡ የአንድ ሀገር ህዝቦች ከትንሽ እስከ ትልቅ ከተባበሩ፣ በአንድነት ከቆሙ፣ ያላቸውን ሀገር በቀል እውቀት፣ ክህሎትና አስተሳሰብ ካቀናጁ፣ ልክ እንደኢሬቻ በአደባባይ አውጥተው ሲጠቀሙና ሲተባበሩ በአንድ ሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን ለጎረቤትና ለዓለም ሀገራት የሚጠቅም ስራ መስራት ይችላሉ። በመተባበር የማይለወጥ የነበረና የገዘፈ ችግር አይኖርም፡፡

ዘላቂ ሰላምን ከማረጋገጥ አኳያም ኢትዮጵያውያን ያለቻቸው “ኢትዮጵያ” የምትባል ሀገር ናት፡፡ ያለፈው ትውልድ በበጎም ሆነ በመጥፎ ሀገሪቱ አሁን ላለችበት ደረጃ የበኩሉን ድርሻ ተወጥቷል። አሁን ያለው ትውልድ ደግሞ የተሻለች ሀገር ለመፍጠር በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚና ፖለቲካው መስክ የሚታዩ ፈተናዎችን ለመሻገር ምክክርን ማስቀደም ይኖርበታል። ፍቅርና ምክክር ካለ ሰላም ይኖራል፡፡ ፍቅርና ሰላም ደግሞ ከቤት የሚጀምር በመሆኑ ሁሉም የድርሻውን መወጣት እንደሚጠበቅበት ግርማ (ዶ/ር) ያስገነዝባሉ፡፡

በኢሬቻ ከሰው ልጆች፣ እንስሳት፣ ዕፅዋት ጋር ሰላም መፍጠር ከፍተኛ ዋጋ ይሰጠዋል፡፡ ሰላምና እርቅም ከልብ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ በተለያዩ ሀገራዊ ጉዳዮች ተከፋፍለን መቆየታችን ልክ እንደ ክረምቱ ጨለማ የሚታይ ነው፡፡ በኢሬቻ ከጨለማ ወደ ብርሃን ሽግግር እንደሚደረግ ሁሉ በሀገራዊ ምክክርም ወደ አንድነትና ብሔራዊ መግባባትን ማምጣት ይቻላል፡፡ የሰላም፣ እርቅ፣ አንድነት መንፈስን በመያዝ ሀገራዊ ምክክር ማድረግ ከተቻለ ሀገራዊ መግባባት የማይፈጠርበት ምንም ምክንያት እንደማይኖር ግርማ (ዶ/ር) ያስረዳሉ፡፡ የሀገራዊ ምክክሩ ዓላማ ሁሉም ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በእኩልነት፣ በሰላም፣ በአንድነት የሚኖሩባት ኢትዮጵያን መፍጠር ነው፡፡ ምክክርን ዋጋ ከሰጠነው በሀገራችን ሁለንተናዊ እድገት ማምጣት እንደሚቻልም ያክላሉ፡፡

## “ዜጎች... ከገጽ 20 የዞረ

አገልግሎት) ነው፡፡ ይህንን አስመልክቶ በወቅቱ በጥናቱ ላይ የተሳተፉት በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የሶፍትዌር ኢንጂነሪንግ ትምህርት ክፍል ረዳት ፕሮፌሰር፤ የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስና ሮቦቲክስ ልህቀት ማዕከል ኃላፊ የነበሩት ቱሉ ጥላሁን (ዶ/ር) ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ጋር በነበራቸው ቆይታ እንዳብራሩት፤ ስማርት ገቨርናንስ (ስማርት የመንግስት አገልግሎት) ማለት፤ ነዋሪዎች የሚያገኟቸውን የመንግስት አገልግሎቶች ፈጣንና ቀልጣፋ ማድረግን የሚመለከት ነው፡፡ ተገቢውን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ሰልፍን መቀነስ፣ ከሰው ንክኪ ውጪ አገልግሎት በመስጠት ግልጽነትን መፍጠርና ብልሹ አሰራርን ማስቀረትን ዓላማው ያደረገ ነው፡፡

### ከአደረጃጀት አንፃር የተደረገው ዝግጅት

“አዲስ የአገልግሎት አድማስ” በሚል መሪ ሀሳብ በአደረጃጀት፣ በአሠራር ስርዓት እንዲሁም በሠራተኛ ስነ ምግባር ጠንከር ያለ ቁራጥ አቋም በመያዝ ወደ ሥራ መገባቱን የሚናገሩት ዋና ዳይሬክተሩ፣ ሠራተኞች በሥራ ቦታቸው ላይ ሆነው በተለያየ ነገር ሃሳባቸው እንዳይሰረቅ ብሎም ለብልሹ አሠራር ተጋላጭ እንዳይሆኑ ተንቀሳቃሽ ስልኮችን ይዘው ወደ ሥራ ክፍላቸው አይገቡም፡፡ ከዚህ ቀደም በሀገራችን ለበርካታ ዓመታት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ይነሱ የነበሩ ክፍተቶች እንዲታረሙ እና በዚህ ማዕከል እንዳይደገሙ በማዕከሉ የተዘረጋው የአሠራር ስርዓት ሁነኛ መፍትሔ እንደሚኖረው ይጠበቃል። በሠራተኛ የሥራ ስነ ምግባር ላይ ተጠባቂው ውጤት እንዲመጣ፤ ሠራተኞች ወደ ሥራ ከመግባታቸው አስቀድሞ ለ15 ቀናት በኢትዮጵያ አቬይሽን ዩኒቨርሲቲ ስልጠና ወስደዋል፡፡ ስለማዕከሉ የሥራ ስነ ምግባርም በጥልቀት ገለጻ እና ማብራሪያ መሰጠቱን ገልጸዋል፡፡

በቃሉ ታደሰ ይባላል፡፡ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢንፎርሜሽንና ቴክኖሎጂ የትምህርት ዘርፍ በ2017 ዓ.ም ተመርቋል። በአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት የሲቪል ምዝገባ እና ነዋሪዎች አገልግሎት ኤጀንሲ ውስጥ ባለሙያ ነው፡፡ የልደት ሰርተፍኬት፣ የሞት ምዝገባ፣ ጋብቻ፣ ጉዲፈቻ እና ፍቺ መሰል አገልግሎቶችን በአዲስ መሶብ ይሰጣል። ወደ ሥራ ከመግባቱ በፊት ከደንበኞች አልያም ከባለጉዳዮች ጋር ሊኖረው ስለሚገባ ግንኙነት በቂ ስልጠና አግኝቷል። ሙያውንም በተመለከተ እንዲሁ የስራው ባህሪ ላይ ምን እንደሚመስል ጭምር አውቆ ወደ ሥራ ስለመግባቱ ተናግሯል፡፡

ሰዎች አለአግባብ ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውንና ገንዘባቸውን እንዳያባክኑ የዘመኑ የአሠራር ስልቶችን ተግባራዊ ማድረግ ወሳኝ ሚና እንዳለው የሚናገረው ደግሞ በአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ውስጥ ሁሉን አቀፍ አገልግሎት ሰጪ ባለሙያ አዲሱ ፈንቴ ነው፡፡ “ሁሉንም አገልግሎት በአንድ ማዕከል ማግኘት መቻል መጉላላቶችን ብሎም አላስፈላጊ ትርምሶችን የሚቀንስ ነው፡፡” ሲል ገልጿል፡፡

ይህን ሀሳብ በማዕከሉ ያገኘናቸው ተገልጋዮችም ያጠናክሩታል፡፡ ወጣት መንግስቱ ተስፋው፤ ነዋሪነቱ በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 1 ነው፡፡ የፋይዳ መታወቂያ ለማውጣት ወደ አዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት የመጣ ሲሆን፤ ቀልጣፋ እና ምቹ የአሠራር ስርዓት በተቋሙ ስለማግኘቱ ተናግሯል። ማህበረሰቡን ለምሬትና ለእንግልት የሚዳርጉ የአሰራር ስርዓቶችን አስቀርቶ የከተማን እድገት ለማፋጠን መሰል ሁነኛ መላዎችን ማስፋት ያስፈልጋል ሲልም አክሏል፡፡

የተለያዩ ጉዳዮችን በፍጥነት ለማስፈፀም እንሰራለን የሚሉ ህገ ወጥ ደላሎች እጃቸውን እንዳያስገቡ ብሎም ከተቋሙ ሰራተኞች ጋር ፍፁም ግንኙነት እንዳይፈጥሩ ማስቻል ከማዕከሉ የሚጠበቅ እንደሆነ የጠቆሙት የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አቶ ዮናስ፤ ለዚህ የሠራተኛውን ግንዛቤ የማሳደግ፣ የሥራ ላይ ስነ ምግባር መርህና ህግን የማሳወቅ እንዲሁም በቴክኖሎጂ የታገዘ ክትትል የማድረግ ስራ ከተከናወኑት መካከል እንደሚጠቀሱ አብራርተዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም፤ በማዕከሉ በሆነ አግባብ ከተማዋን በሚመስል የሰው ሃይል ተደራጅቷል፡፡ አዲስ እና ነባር ሠራተኞችን ያካተተም ነው፡፡ የሠራተኞች ስብጥርን በተመለከተ ብቃታቸውን በምዘና በማረጋገጥ ከየተቋማቱ ነባር ሠራተኞች ወደማዕከሉ እንዲቀላቀሉ ተደርገዋል። ጥሩ ውጤት ያላቸውን አዲስ ምሩቅ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን በመፈተን አብላጫ ውጤት ያመጡትን ወደ ሥራ ለማስገባት ስለመቻሉም ገልፀዋል።

የማዕከሉ ሠራተኞች ሥራ ከመጀመራቸው አስቀድሞ የወሰዷቸው የስልጠና ኮርሶች አካዳሚው ለአየር መንገድ እና ሌሎች የደንበኛ ተኮር ዘርፎች የሚሰጠውን ዓለም አቀፍ ስታንዳርድ የጠበቀ ስልጠና ስለመሆኑ አቶ ዮናስ ገልፀዋል፡፡ አያይዘውም መስሪያ ቤቱ የሰራተኛ ስነ- ምግባርን በተመለከተ ጥብቅ የሆነ መመሪያ ያዘጋጀ ሲሆን ሰራተኞቹ ተቋሙን ከመቀላቀላቸው አስቀድሞ እጅግ ጥብቅ በሆነው የደንብ ልብስ አለባበስ እና የስራ ቦታ ህግጋቶች ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ተደርጓል። ይህን መሰል የአሰራር ስርዓት ለመከተል ምክንያት የሆነው ደግሞ የተገልጋይ እርካታን ለማሳደግ ብሎም ከዚህ ቀደም የነበረውን ችግር ለመቅረፍ በማሰብ ጭምር ስለመሆኑ አስረድተዋል፡፡

በወረዳ እና በክፍለ ከተማ የሚሰጡ አገልግሎቶች እንደተጠበቁ ሆኖ አንድ እና ከዚያ በላይ የተሳሰሩ አገልግሎቶችን ማግኘት የሚፈልግ ሰው አዲስ መሶብ ላይ መገልገል ይችላል፡፡ ከአንድ ተቋም ወደ ሌላ ተቋም አካባቢ ቀይሮ ከመንቀሳቀስ ይልቅ አንድ ቦታ አገልግሎቱን እንዲያገኝ የሚያስችል ነው። ተደራሽነትን ከማስፋት አንፃርም በርካታ ስራዎችን ለመስራት እንደታሰበ የሚገልጹት አቶ ዮናስ፣ በማዕከል ደረጃ ያለው የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ዋና መስሪያ ቤት ነው፡፡ ከሰሞኑ የቦሌ አዲስ መሶብ ቅርንጫፍ በይፋ ስራ ይጀምራል፡፡ በበጀት ዓመቱ በሁሉም ክፍለ ከተሞች አማካኝ በሆነ ቦታ ላይ የመሶብ አገልግሎት ለመጀመርም እቅድ አለ፡፡ ከ13ቱ ተቋማት በተጨማሪ ሌሎች አገልግሎቶችን በቴክኖሎጂ ለመስጠት ብቁ የሆኑትን ለማካታተም መታሰቡን ተናግረዋል፡፡

## የምገባው... ከገጽ 25 የዞረ

ጋር ተመሳሰይ የትምህርት አቀባበል አይኖረውም ያሉት ርዕሰ መምህሩ፤ ምገባው ተማሪዎች ትምህርታቸውን በትኩረት እንዲከታተሉ በማድረግ ከበፊቱ በተሻለ ውጤታማ እንዳደረጋቸው ተናግረዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምገባ ኤጀንሲ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ስንታየሁ ማሞ በበኩላቸው፤ የከተማ አስተዳደሩ ከሚሰራቸው ሰው ተኮር ስራዎች መካከል ከቅድመ መደበኛ እስከ 8ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች የሚካሄደው የምገባና የቁሳቁስ አቅርቦት አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ ይህ ተግባር ከስድስት ዓመት በላይ የሆነው ሲሆን ከዓመት ዓመትም የምገባ ተጠቃሚ የሚሆኑ ተማሪዎችን ቁጥር በማሳደግ እና የምገባ የአሰራር ስርዓቱን በማሻሻል እየተሰራ ነው፡፡

በ2012 ዓ.ም 375 ሺህ 93፣ በ2013 ዓ.ም 527 ሺህ 971፣ በ2014 ዓ.ም 624 ሺህ 272፣ በ2015 ዓ.ም 701 ሺህ፣ በ2016 ዓ.ም 779 ሺህ 231 እና በ2017 ዓ.ም 840 ሺህ 585 የሚሆኑ በአዲስ አበባ እና ሸገር ከተማ ከቅደመ አንደኛ ጀምሮ እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ ያሉ በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች የምገባ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል። በ2018 ዓ.ም ደግሞ 976 ሺህ 702 ለሚሆኑ ተማሪዎች በቀን ሁለት ጊዜ የምገባ አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ እየተሰራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

“ከመመገብ ባሻገር” በሚል መሪ ሀሳብ እየተከናወነ ያለው የተማሪዎች የምገባ መርኃ ግብር ተማሪዎች ትኩረታቸውን ትምህርታቸው ላይ ብቻ እንዲያደርጉ ከማድረግ ባሻገር አዕምሯዊና አካላዊ እድገታቸው የተሻለ እንዲሆን አዎንታዊ አስተዋፅኦ እያበረከተ ነው፡፡ የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙም ምገባው ከተጀመረ አንስቶ ስድስት የምግብ አይነት በማካተትና በየዓመቱ የምግብ ዝርዝር ማሻሻያዎችን በማድረግ እየተሰራ መሆኑን ወይዘሮ ስንታየሁ ያስረዳሉ፡፡

የምግብ ዝርዝር ማሻሻያ በማድረግ የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙ በመሰራቱ የተማሪዎች መጠነ ማርፈድና ማቋረጥ በእጅጉ እየቀነሰ እና ውጤታቸውም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መጥቷል፡፡ ለዚህም የ6ኛ ክፍል ከተማ አቀፍ ፈተና የወሰዱ 94 ከመቶ እና 8ኛ ክፍል ደግሞ 88 ከመቶ ተማሪዎች ወደ ቀጣዩ ክፍል ማለፍ መቻላቸውን ለማሳያነት አንስተዋል፡፡

ወይዘሮ ስንታየሁ እንደነገሩን፤ በትምህርት ቤቶች የቅድመ አንደኛ፣ ከ1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል እና የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን ማዕከል ያደረጉ ሶስት አይነት የምግብ ዝርዝሮች (ሜኑ) ይዘጋጃሉ። 1 ሺህ 269 የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ሲሆን እነዚህን ያማከለ እንደ እንቁላል፣ ሙዝ እና ቅንጬ የመሳሰሉ የምግብ አይነቶችን በማካተት የምግብ ዝርዝሩን በማዘጋጀት እየቀረበላቸው ይገኛል፡፡

ለአንድ ሀገር እድገትና ለውጥ መሰረቱ ትምህርት መሆኑን የሚናገሩት ምክትል ዋና ዳይሬክተሯ፤ ምገባው ተማሪዎች የተሻለ የትምህርት አቀባበል እንዲኖራቸውና ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያደርግና በትውልድ ግንባታ ላይ የሚውል መዋዕለ ንዋይ ነው፡፡ ወደፊትም ተማሪዎች በተማሩት ትምህርት ውጤታማ እንዲሆኑ የክትትልና ቁጥጥር ስራ፣ የመጋቢ እናቶችንም ማገዝ እና በተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ላይ እየመጣ ያለውን ለውጥ በየጊዜው ክትትል የማድረግ ስራዎችና ማሻሻያ የማድረግ ተግባራት እንደሚከናወኑ ጠቁመዋል፡፡

## በልደታ ክ/ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት የልደታ ሰላም አንደኛ እና መካ/ደረጃ ት/ቤት

### ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ

### ግዥ መለያ ቁጥር 001/2018 ዓ.ም

በልደታ ክ/ከተማ በወረዳ 1 ስር የሚገኘው የልደታ ሠላም የመ/ደ/ት/ቤት በ2018 ዓ.ም በጀት ዓመት የሚፈልጋቸውን :-

ሎት 1. የደንብ ልብስ የጨረታማስከበሪያ 7000.00

ሎት 2. ለአላቂ የቢሮ ዕቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ 3000.00

ሎት 3. ለህትመት የጨረታ ማስከበሪያ 2000.00

ሎት 4. አላቂ የህክምና ዕቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ 1000.00

ሎት 5. አላቂ የትምህርት ዕቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ 2000.00

ሎት 6. ለሌሎች አላቂ ዕቃዎችና አቅርቦቶች የጨረታ ማስከበሪያ 8000.00

ሎት 7. ልዩ ልዩ መሳሪያዎች የጨረታ ማስከበሪያ 2166.00

ሎት 8. ለፕላን ማሽነሪና መሳሪያዎች ጥገና የጨረታ ማስከበሪያ 800.00

ሎት 9. ለህንፃ፣ ለቁሳቁስ እና ለተገጣጣሚዎች ዕድሳት ጥገና 2000.00

ሎት 10. ለፕላንት፣ ማሽነሪ እና መሳሪያዎች መግዣ 3500.00

ሎት 11. ለህንፃ፣ ለቁሳቁስ ለተገጣጣሚዎች መግዣ 3000.00 ሎት 12. መሰተንግዶ 7000.00

መስሪያ ቤቱ ባወጣው ግልፅ ጨረታ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያማሉ ተጫራቾች መወዳደር ይችላሉ፤

1. በጨረታው ለመወዳደር ፍላጎት ላላቸው ተጫራቾች የታደሰ የንግድ ፍቃድ ያላቸው የዘመኑን ግብር የከፈሉ በመንግስት ግ/ን/አስ/ኤጀንሲ ድረ ገጽ በአቅራቢዎች ምዝገባ ዝርዝር የተመዘገቡ የቲንና የቫት ተመዝጋቢ የሆኑና የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፡፡
2. የተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ ቼክ /ሲፒኦ/ ከጨረታ ሰነዶቻቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው።
3. የጨረታ አሸናፊ 10% የጨረታ ዋስትና ማስያዝ ይኖርበታል፡፡
4. ተጫራቾች በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት ዕለት አንስቶ በተከታታይ አስር የስራ ቀናት የማይመለስ ብር 200.00 ሁለት መቶ ብር ብቻ) በልደታ ሠላም አንደኛ እና መካ/ደ/ት/ቤት በቢሮ ቁጥር 15 በመምጣት የጨረታ ሰነዱን መግዛት ይቻላል፡፡
5. ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዶቻቸውን በታሸገ ኤንቨሎፕ ማስታወቂያው ከወጣበት ዕለት ጀምሮ በተከታታይ 10 የሥራ ቀናት በልደታ ሠላም አንደኛ እና መካ/ደ/ት/ቤት ቢሮ ቁጥር 15 ለጨረታ በተዘጋጀው ሣጥን ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
6. ጨረታውን ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በ10ኛው ቀን ከቀኑ 10፡00 ሰዓት ታ ሽጎ በዛኑ ቀን ከቀኑ 10፡30 ሰዓት በልደታ ሠላም አንደኛ እና መካ/ደ/ት/ቤት በቢሮ ቁጥር 15 ይከፈታል። የመከፈቻው ቀን ቅዳሜ እና እሁድ (የበዓል ቀን) ከሆነ በሚቀጥለው የሥራ ቀን በተመሣሣይ ሰዓት ታሽጎ ይከፈታል ፡፡
7. ተጫራቾች የጨረታ ሣጥኑ ከመከፈቱ በፊት የተወዳደሩባቸውን ሎት 1 ሎት 2 ሎት 3 ሎት 4 ሎት 5 ሎት 6 ሎት 7 ሎት 9 ሎት 10 ሎት 11 እና ሎት 12 ናሙና ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
8. ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ባይገኙም ት/ቤቱ ጨረታውን የመክፈት መብቱ የተጠበቀ ነው።
9. ተጫራቾች የሚወዳደሩባቸውን ዕቃዎች ለእያንዳንዱ ከቫት ጋር ያለውን ዋጋ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል።
10. የዘገየ ጨረታና በጨረታ መክፈቻ ላይ ያልተነበበ ጨረታ ተቀባይነት የለውም፡፡
11. አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፏቸውን ዕቃዎች በራሣቸው ትራንስፖርት ግዥ ፈፃሚው መሥሪያ ቤት ድረስ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
12. መሥሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
13. ት/ቤቱ ዕቃዎችን 20% የመቀነስ 20% የመጨመር መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**አድራሻ፡- አዲሱ ደሴ ሆቴል በተሠራው መንገድ ወረድ ብሎ ልደታ ፀበል አካባቢ ነው።**

**ስልክ 0113690439/0113692257**

**አዲስ አበባ አስተዳደር በልደታ ክ/ከተማ ትም/ፅ/ቤት ልደታ ሰላም አንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት**

## ግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ

### የጨረታ ማስታወቂያ ቁጥር አቃ/ቃ/ገ/ጉ/ጤ/ጣ/ግ/ጨ/001/2018 ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃ/ቃ/ክ/ከተማ ጤና ጽ/ቤት የገላን ጉራ ጤና ጣቢያ የ2018 ዓ.ም በጀት ዓመት አገልግሎት ላይ የሚውል ዕቃ ግዥ

| | |
|---|---|
| ሎት 1. ቋሚ እቃ | ሎት 4. ደንብ ልብስ |
| ሎት 2. የጽህፈት መሳሪያዎች | ሎት 5. ልዩ ልዩ እቃዎች |
| ሎት 3. የጽዳት እቃ | ሎት 6. የህትመት ሰራዎች |

በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

በዚሁ መሰረት ተጫራቾች

1. የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያላቸው፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉ፣ በመንግስት ግ/ን/አስ/ኤጀንሲ ድህረ ገጽ ላይ በአቅራቢዎች ምዝገባ ዝርዝር የተመዘገቡ፣ የቲን እና የቫት ተመዝጋቢ የሆኑና የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፡፡ ጥቃቅንና አነስተኛ በራሳቸዉ ሰርተዉ ለሚያቀርቡ እቃዎች ብቻ የተፃፈ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
2. ተጫራቾች የሚወዳደሩባቸውን እቃዎች ለእያንዳንዱ ከቫት ጋር ያለውን ዋጋ ማስቀመጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡
3. ተጫራቾች የሚወዳደሩበት በመለየት ፖስታ ላይ በመግለፅ አሽገዉ ኦሪጅናልና ፎቶ ኮፒ ብለዉ በመፃፍ ለይተዉ የድርጅታቸዉን ማህተም እና ፊርማ በማድረግ በጤና ጣቢያው የግዢ ቡድን ቢሮ ቁጥር 300 (ሦስት መቶ ብር ብቻ ) ክፍያ የሚፈፀመው በቴሌ ብር መሆኑን እያሳወቅን የጫራታ ሰነድ በመግዛት ብሮ ቁጥር - 405 - ለጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
4. ይህ ጨረታ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ 10 ተከታታይ የስራ ቀናት አየር ላይ የሚውል ሲሆን የጨረታውን ሳጥን በ11ኛዉ ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ላይ ታሽጎ በዚሁ ቀን ከጠዋት 4፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸዉ በተገኙበት የሚከፈት ሲሆን ምናልባት 11ኛዉ ቀን የህዝብ በዓል ወይም ከመንግስት የስራ ሰዓት ዉጭ ከሆነ በሚቀጥለዉ የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት የሚከፈት የሆናል፡፡
5. በጨረታ ሰነዱ ላይ የተገለፀዉ ሙሉ ዝርዝር ሁኔታ የጨረታዉ መመሪያ ሆኖ ችግሮች ካጋጠሙ በጊዜዉ መመሪያ የሚዳኝ ይሆናል፡፡
6. ተጫራቾች ለሚጨረቱት እቃዎች ሙሉ በሙሉ ናሙና ማቅረብ እንዳለባቸው እናም በሚያቀርቡት ናሙና ላይ ምንም አይነት ምልክት ወይም ድርጅቱን የሚገልጽ ምልክትም ሆነ ማህተም መድረግ የለበትም፡፡ ተጨራቾች የሚያቀርቡት ናሙና ከሚያስገቡት እቃ ጋር ፍፁም የተለየ መሆን የለበትም ፡፡
7. ተጮራቾች ቋሚ እቃዎችን ሲጫረቱ አንድ ዓመት እና ከዚያ በላይ ዋስትና መስጠት አለባቸው፡፡
8. ተጨራቾች ሙሉ ሰነዱን ካልመለሱ ከጨረታ ውጪ ይሆናሉ፡፡
9. ሎት1. 40,000 ሎት 2. 20,000 ሎት.3 50000 ሎት4. 56000 ሎት5. 2400 ሎት6. 5000 CPO በዚህ ልክ እንዲያስገቡ።
10. የጨረታው ዋጋ የሚሞላው በተቀመጠለት መለኪያ ብቻ ሲሆን ከመለኪያው ውጭ የተሞላ ዋጋ እንዲሁም ስርዝ ድልዝ ወይም በፍሉድ የተነካካ ዋጋ ሙሉ በሙሉ ከጨረታው ውድቅ ይደረጋል፡፡
11. አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፈባቸውን እቃዎች በራሳቸው ትራንስፖርት ግዥ ፈጻሚው መስሪያ ቤት ድረስ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
12. ጨረታውን አሸናፊ ሆነው ከተገኙ በኃላ 10% ባሸነፉት ዕቃ መጠን የውል ማስከበሪያ ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
13. መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታዉን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነዉ፡፡ በተጨማሪ ለማብራሪያ ጥያቄ ለጨረታው ከቀረቡ የእቃዎች ዝርዝር ውስጥ መ/ቤቱ እስከ 25 በመቶ ለመጨመር ወይም ለመቀነስ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

<u>ለተጨማሪ ማብራሪያ</u>

በስልክ ቁ. 0901 25 94 01/ 0975 99 50 34 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡

<u>አድራሻ፡-</u> ወረዳ 10 አዳባባይ ገባ ብሎ

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ አቃቂ ቃሊት ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ገላን ጉራ ጤና ጣቢያ**

ቁጥር አው/ተ/ሁ/ሽ ሠደ-3/319/2018

## የግዢ ጨረታ ማስታወቂያ

የአውቶብስ ተራ ሁ/ሽ/ኃ/የተ/ህ/ሥራ ማህበር ለማህበሩ እና በውስጡ ለሚያስተዳድራቸው ተቋሞች አገልግሎት ላይ የሚውል፡-

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | መለኪያ | ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ኅልድ የኮምፒዩተር ወረቀት | ካርቶን | 30 | |
| 2 | ካርቦን አባሳደር 3000/H | እሽግ | 120 | |
| 3 | እስክሪፕቶ ቢክ | ፓኬት | 50 | |
| 4 | ጥቁርና ቀይ ሌክሲ እስክሪፕቶ | ፓኬት | 6 | |
| 5 | ፋስትነር | ፓኬት | 6 | |
| 6 | ግሉ | ደርዘን | 15 | |
| 7 | የብር ላስቲክ | ኪሎ | 8 | |
| 8 | የውሃና የሻራ ፕላስተር | በቁጥር | 6 | |
| 9 | የስቴፕለር ሽቦ | ካርቶን | 25 | |
| 10 | ትንሹ ማስታወሻ ደብተር | ደርዘን | 10 | |
| 11 | ክላሰር | እሽግ | 8 | |
| 12 | ፍሉድ | ደርዘን | 10 | |
| 13 | ስፒል | ፓኬት | 2 | |
| 14 | መቀስ | በቁጥር | 4 | |
| 15 | እርሳስ | ፓኬት | 2 | |
| 16 | ቦክስ ፋይል | በቁጥር | 400 | |
| 17 | መብሻ የወረቀት | በቁጥር | 8 | |
| 18 | ስቶክ ካርድ | እሽግ | 100 | |
| 19 | መዝገብ | በቁጥር | 15 | |
| 20 | ፕሮቶኮል መዝገብ ትልቁ | በቁጥር | 4 | |
| 21 | ካልኩሌተር | በቁጥር | 12 | |

ከላይ የተዘረዘሩትን የፅህፈት ዕቃዎች በጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

- እነዚህን የፅህፈት ዕቃዎች በጨረታው መሠረት መሸጥ የሚፈልግ በዕቃ ዋጋ ማቅረቢያ (ፕሮፎርማ) በፖስታ በማሸግ በማህበሩ ቢሮ ዘወትር በሥራ ሰዓት በማቅረብ መወዳደር የሚቻል መሆኑን እናስታውቃለን ፡፡
- ጨረታው አየር ላይ የሚውለው ከዛሬ 26/01/2018 ዓ/ም እስከ 03/02/2018 ዓ/ም ድረስ ለተከታታይ 7 የሥራ ቀናት ይሆናል፡፡ ጨረታው በሰባተኛው ቀን 6፡00 ሰዓት ተዘግቶ በዕለቱ 8፡00 ሰዓት አውቶብስ ተራ ሁ/ሽ/ኃ/የተ/ህ/ሥራ ማህበር ሽማች ቢሮ ወኪሎች በተገኙበት የሚከፈት ይሆናል።

- **ማሳሰቢያ፡-** ማህበሩ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
  - **አድራሻ፡-** አ/ከ/ክ/ከ ወረዳ 6/7 የቀድሞው ቀበሌ 30 አዲስ ከተማ ት/ቤት ጀርባ የሚገኘው የማህበሩ ጽ/ቤት፡፡
  - **ለተጨማሪ መረጃ ስልክ፡-** 0112 - 782072

0112 - 132166 ደውሎ መጠየቅ ይቻላል

### ህብረት ሥራ ማህበሩ

### በአ/ከ/ክ/ከ ወ/06/07 አውቶብስ ተራ ሁለገብ ሽ/ኃ/የተ/የህ/ሥ/ማ

በአቶ ደስታአለም ገ/ማሪያም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ወረዳ 01 ክልል ውስጥ የሚገኝ ይዞታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር 031263 ሴሪ ቁጥር 029516 የቦታው ስፋት 94.64 ካሬ ሜትር የሆነ ካርታ የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ እንዲታወጅ እየገለጽን በማንኛውም ምክንያት የጠፋውን ካርታ ይገፎዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከታወጀበት ዕለት ጀምሮ እስከ 20 ተከታታይ የስራ ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ካላቀረቡ በምትክ ሌላ ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

ቁጥር አው/ተ/ሁ/ሽ ሠደ-3/319/2018

## የግዢ ጨረታ ማስታወቂያ

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6/7 አስተዳዳር የሚገኘው የአውቶብስ ተራ ሁ/ሽ/ኃ/የተ/ህ/ሥራ ማህበር ለማህበሩ አገልግሎት የሚውል፡-

1. መጋረጃ ከነብረቱ አምስት አይነት ከለር ብዛት 10
2. የቢሮ ወንበር ተሽከርካሪ አስተኛ ብዛት 10
3. የእንግዳ መቀበያ ወንበር ብዛት 10
4. የቢሮ ጠረጴዛ ባዛት 7
5. ለቢሮ የሚሆን ትልቅ ቡፌ ብዛት 1
6. ለመሰብሰቢያ የሚሆኑ ፕላስቲክ ወንበሮች ብዛት 300

- እነዚህ ዕቃዎችን በጨረታው መሠረት መሸጥ የሚፈልግ በዕቃ ዋጋ ማቅረቢያ(ፕሮፎርማ) በፖስታ በማሸግ በማህበሩ ቢሮ ዘውትር በሥራ ሰዓት በማቅረብ መወዳደር የሚቻል መሆኑን እናስታውቃለን፡፡
- ጨረታው አየር ላይ የሚውለው ከዛሬ 26/01/2018 ዓ/ም እስከ 03/02/2018 ዓ/ም ድረስ ለተከታታይ 7 የሥራ ቀናት ይሆናል ጨረታው በሰባተኛው ቀን 6፡00 ሰዓት ተዘግቶ በዕለቱ 8፡00 ሰዓት አውቶብስ ተራ ሁ/ሽ/ኃ/የተ/ህ/ሥራ ማህበር ሽማች ቢሮ ወኪሎች በተገኙበት የሚከፈት ይሆናል፡፡

- **ማሳሰቢያ፡-** ማህበሩ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው ፡፡
  - **አድራሻ፡-** አ/ከ/ክ/ከ ወረዳ 6/7 የቀድሞው ቀበሌ 30 አዲስ ከተማ ት/ቤት ጀርባ የሚገኘው የማህበሩ ጽ/ቤት፡፡
  - **ለተጨማሪ መረጃ ስልክ፡-** 0112 - 782072

0112 - 132166 ደውሎ መጠየቅ ይቻላል፡፡

### ህብረት ሥራ ማህበሩ

### በአ/ከ/ክ/ከ ወ/06/07 አውቶብስ ተራ ሁለገብ ሽ/ኃ/የተ/የህ/ሥ/ማ

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 01 ዳዊት መሰለ የተመዘገበ ቤት ---በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ክልል ውስጥ በካርታ ቁጥር 017940 በሴሪ ቁጥር 002626 የተመዘገበው የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጁ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

ወ/ሮ ፍፁም ጌታቸው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 12 ካርታ ቁጥር ቦሌ17/115/4-176/00 ሴሪ ቁጥር 037908 ተመዝግቦ የነበረው ኦሪጅናል/ዋናው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋባቸው በተለያየ ምክንያት ይገፎዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባለው 20 ቀናት ውስጥ በቦሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ለይዞታ አገልግሎትና ማስተካከል ዳይሬክቶሬት ካልቀረበ በምትኩ ሌላ አዲስ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የቦሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

አቶ አርጋው ኃይሌ ሰሙ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 የካርታ ቁጥር ቦሌ03/296/12/3/00 ሴሪ ቁጥር 139292 የሆነው ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይገፎዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት አብድርቃድር ምትኩ አህመድ በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ በቀድሞ ቀበሌ- በአሁኑ ወረዳ 03 ቤት ቁጥር - ነዋሪ ሲሆኑ ከይዞታ አስተዳደር የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር ወ3/ው ዝ01/1500/23692/00 ሴሪ ቁጥር 071084 ኦርጂናሉ ተፈልጎ ሊገኝ ስላልቻለ በምትኩ ሌላ ካርታ እንዲሰጣቸው ይህንን ካርታ በዕዳ፣ በዋስትና ወይም ሌላ በማንኛውም ምክንያት ይገፎዋለሁ የሚል ካለ በ30 ቀን ውስጥ ኮ/ቀ/ክ/ከተማ ቀርቦ እንዲያሳውቅ ካላሳወቀ ግን በምትኩ ሌላ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

## ግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ

## የጨረታ መለያ ቁጥር 001/2018 ዓ.ም

በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ አንድ መስከረም አንድ ቅድመ አንደኛ፣ አንደኛና መካከለኛ ደ/ት/ቤት ለ2018 በጀት ዓመት ለመማር ማስተማር አገልግሎት የሚያስፈልጉ

ሎት 1. አላቂ የቢሮ ዕቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ ብር 30011

ሎት 2. አላቂ የፅዳት ዕቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ ብር 10000

ሎት 3. የደንብ ልብስና ጫማ የጨረታ ማስከበሪያ ብር 23823.4

ሎት 4. የደንብ ልብስ ስፌት የጨረታ ማስከበሪያ ብር 5000

ሎት 5. ለህትመት የጨረታ ማስከበሪያ ብር 5000

ሎት 6. ቋሚ ዕቃዎች ፈርኒቸር የጨረታ ማስከበሪያ ብር 15000

ሎት 7. ኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ ብር 15000

ሎት 8. የላብራቶሪ ዕቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ ብር 5000

ሎት 9. የሻይ ቡና አቅርቦት የጨረታ ማስከበሪያ ብር ያስገቡትን ዋጋ 2%

ሎት 10. የኤሌክትሮኒክስ ጥገና የጨረታ ማስከበሪያ ብር ያስገቡትን ዋጋ 2%

ሎት 11. የፈርኒቸር ጥገና የጨረታ ማስከበሪያ ብር ያስገቡትን ዋጋ 2%

ሎት 12. የጥገናና ዕድሳት የጨረታ ማስከበሪያ ብር ያስገቡትን ዋጋ 2%

ብቃት ያላቸውን በመስኩ የተሰማሩ ተጫራቾችን አወዳድሮ ግዥ መፈፀም ይፈልጋል፡፡

በዚህም መሰረት፡-

1. በጨረታው ለመወዳደር ፍላጎት ያላቸው ተጫራቾች የታዳሰ ንግድ ፍቃድ ያላቸው፤ የዘመኑን ግብር የከፈሉ፤ በመንግስት ግ/ን/አ/ኤጀንሲ ድህረ ገጽ ላይ በአቅራቢዎች ምዝገባ ዝርዝር የተመዘገቡ፤ የቲን ነምበር ያላቸው፤ ቫት ተመዝጋቢ የሆኑና የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ
2. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ /ሲ.ፒ.ኦ/ ከጨረታው ሰነድ ጋር አያይዘው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
3. ተጫራቾች ጨረታው በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት ዕለት አንስቶ ባሉት 10 ተከታታይ የስራ ቀናት የማይመለስ ብር 200 (ሁለት መቶ ብር) በመክፈል መስከረም አንድ ቅድመ አንደኛ፤ አንደኛና መካከለኛ ደ/ት/ቤት ቢሮ ቁጥር 5 በመምጣት የጨረታ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፡፡
4. ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዳቸውን በታሸገ ኤንቨሎፕ ማስታወቂያው ከወጣበት ዕለት አንስቶ ለተከታታይ 10 የስራ ቀናት መስከረም አንድ ቅድመ አንደኛ፤ አንደኛና መካከለኛ ደ/ት/ቤት ግዢ ክፍል ለጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
5. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በአስረኛው ቀን በ11፡00 ሰዓት ታሽጎ በማግስቱ ከቀኑ 4፡30 ሰዓት በት/ቤቱ የተማሪዎች መመገቢያ አዳራሽ ይከፈታል፡፡ የመክፈቻ ቀኑ ቅዳሜና እሁድ ወይም የበዓል ቀን ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ታሽጎ በተመሳሳይ ሰዓት ይከፈታል፡፡
6. ተጫራቾች የጨረታ ሳጥን ከመከፈቱ በፊት ለተወዳደሩባቸው ዕቃዎች ናሙና ለተጠየቀባቸው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
7. ተጫራቾች የሚወዳደሩባቸውን ዕቃዎች ለእያንዳንዱ ከቫት ጋር ያለውን ዋጋ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡
8. የዘገየ ጨረታና በጨረታ መክፈቻ ላይ ያልተነበበ ጨረታ ተቀባይነት የለውም፡፡
9. አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፉባቸውን ዕቃዎች በራሳቸው ትራንስፖርት ግዥ ፈፃሚው መስሪያ ቤት ድረስ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
10. ለጨረታ ከቀረቡት ዕቃዎች ዝርዝር ውስጥ ት/ቤቱ እስከ 20% ጨምሮ ወይም ቀንሶ የመግዛት መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡
11. መስሪያ ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ለበለጠ ማብራሪያ

- መስከረም አንድ ቅድመ አንደኛ፣ አንደኛና መካከለኛ ደ/ት/ቤት
- ስልክ ቁጥር 0115577296/ 0115579044
- አድራሻ፡- ልደታ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፊት ለፊት ገባ ብሎ

**በል/ክ/ከ/ት/ጽ/ቤት መስከረም አንድ ቅድመ አንደኛ፣ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት**

---

አቶ ክንፈርግብ ሐጎስ ተስፋዬ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 የካርታ ቁጥር ሊዝ/ዕጣ/1254/92 ሴሪ ቁጥር 4782 የሆነው ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

**ጉዳዩ፡- የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ።**

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በየካ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወረዳ 06 በ ፍሊንትስቶን ኢኒጂነሪንግ ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ የቤት ቁጥር KS -301 ባለቤትነት የይዞታ ካርታ ቁጥር የካ203793/09/180/8/1 የተሰጠበት ቀን 19/11/2015 ዓ/ም የሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንደጠፋባቸው በቀን 14/01/2018 ዓ/ም አመልክተው ይህንኑ ይዞታ በጋዜጣ ታውጆ በ 90 ቀናት ውስጥ በይዞታው ላይ መብት አለኝ የሚል እና ይህ ካርታ የጠፋ ስለሆነ ያገኘ ካለ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲያመጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ የይዞታ ካርታው መጥፋቱን በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣላቸው የተደረገ ሲሆን ካርታ መጥፋቱን የሚያውቅ ካለ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ እንዲያሳውቅ እየገለጽን ይህ ባይሆን ለአመልካቹ ምትክ ካርታ ተዘጋጅቶ የሚሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ዮሐንስ ከበደ ደስታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 የካርታ ቁጥር ቦሌ01/376/44-1787/00 ሴሪ ቁጥር 037613 የሆነው ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በተስፋዬ ሳህሌ ወራሳ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከ/ወረዳ 01 የሚገኘው የይዞታ/የቤቱ/ ልዩ መለያ /ካርታ/ ቁጥር AA000080123943 ሴሪ ቁጥር 0229486 በጽ/ቤታችን በስማቸው የተመዘገበ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት/ካርታ/ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 04 ክልል ውስጥ በካርታ ቁጥር 08715 በሴሪ ቁጥር 015758 በትዕግስት አበበ ቡታ ስም የተመዘገበው የቤት የባለይዞታነት እና ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጁ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው በእሸቱ ይትባረክ እና በዕፀገነት እሸቱ ስም በልደታ ክ/ማ ወረዳ በቀድሞ ምዕራብ ክ/ማ በከፍተኛ 04 በአዲሱ ወረዳ 03 የቤት ቁጥር 660፣ የቦታ ቁጥር 12478 የተመዘገበ ይዞታ ካርታ ጠፋብኝ ብለው በቀን 12/01/2018 ዓ.ም በማመልከቻ የጠየቁ ስለሆነ፣ በመሆኑም በጠየቁት መሰረት የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሱት ካርታ ቁጥሮች እና በባለጉዳይ ስም የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ኦርጅናል ካርታም ሆነ ኮፒውን/ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀጽ 72 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 14 የቤት ቁጥር አዲስ በ ኤፍሬም ፈለቀ እርገቱ ስም የተመዘገበው የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር የካርታ ቁጥር ኮ/ቀ/የማ/ን/መ/159/13146/00 የተሰጠበት ቀን 06/10/2000 ዓ.ም ሴሪ ቁጥር 042571 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ካርታ እንደጠፋባቸው በቀን 18/10/2017 ዓ.ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይዤዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 አስተዳደር ውስጥ በካርታ 053445 በሴሪ ቁጥር 1460797 በ አቶ ብሩ ሀይሉ ኡርጌሳ የተመዘገበ ኮንደሚንየም ማህደራቸው ከማህደር ክፍላችን መገኘት የነበረበት የጠፋባቸው ስለሆነ ማህደሩን የያዘ ግለሰብ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት በ20 ቀን ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ድረስ መጥተው ካላሳወቁ ማህደር በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# ተመልካችን ወደሜዳ የመለሰው የ‘ህዳሴ ዋንጫ’





ፎቶ- ከገፀ ድር

ለ19 ጊዜ እየተካሄደ የሚገኘው የዘንድሮ የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ (ሲቲ ካፕ) ህዳሴ ዋንጫ በሚል ስያሜ ከባለፈው እሁድ አንስቶ መካሄድ ጀምሯል

**በሳህሉ ብርሃኑ**

*መቀመጫቸውን* አዲስ አበባ ካደረጉ የእግር ኳስ ክለቦች በተጨማሪ በተጋባዥነት ከሚቀላቀሉ ቡድኖች መካከል የሚደረግ ውድድር ነው የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ (ሲቲ ካፕ)። ለአስራ ስምንት ጊዜ በተከናወነው ውድድር የቅዱስ ጊዮርጊስ እግር ኳስ ክለብ ሰባት ጊዜ አሸናፊ በመሆን ቀዳሚነቱን ሲይዝ የኢትዮጲያ ቡና እና ኢትዮ ኤሌክትሪክ እግር ኳስ ልለቦች ሶስት ሶስት ጊዜ የዋንጫው ባለድል ሆነዋል። የዳሽን ቢራ እና ባህር ዳር ከነማ እግር ኳስ ክለቦች ደግሞ ወደ መዲናዋ ውድድር በተጋባዥነት መጥተው ውድድሩን ያሸነፉ ክለቦች ስለመሆናቸው የሶከር ኢትዮጵያ መረጃ ያመላክታል።

ለ19ኛ ጊዜ እየተካሄደ የሚገኘው የዘንድሮው የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ (ሲቲ ካፕ) ‘ህዳሴ ዋንጫ’ በሚል ስያሜ ከባለፈው እሁድ አንስቶ መካሄድ ጀምሯል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ እግር ኳስ ፌዴሬሽን በየዓመቱ የሚያዘጋጀው ይህ ውድድር በስምንት ክለቦች መካከል እየተከናወነ ይገኛል። ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ኢትዮጵያ ቡና፣ መቻል፣ ኢትዮ ኤሌክትሪክ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ፋሲል ከነማ፣ አዳማ ከተማ እና ሸገር ከተማ ተሳታፊ የእግር ኳስ ክለቦች ናቸው። በምድብ ‘ሀ’ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ፋሲል ከነማ፣ አዳማ ከተማ እና መቻል፤ በምድብ ‘ለ’ ኢትዮጵያ ቡና፣ ኢትዮ-ኤሌክትሪክ፣ ሸገር ከተማ እና ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሁለት ምድብ ተደልድለው ነው ውድድሩ የተጀመረው።

በአዲስ አበባ ስታዲየም እየተካሄደ የሚገኘው የአዲስ አበባ ሲቲ ካፕ ዋንጫ ከውድድሩ ዓመት መግቢያ በፊት የሚካሄድ ቀላል የትዕይንት የፉክክር መድረክ ብቻ አይደለም። በተለይም ለዋና ከተማዋና ለአካባቢው ክለቦች፣ ለደጋፊዎች እና ለእግር ኳስ ማህበረሰቡ ትልቅ ፋይዳና አስፈላጊነት ከፍተኛ ነው። የአዲስ አበባ ሲቲ ካፕ ዋንጫ የመጀመሪያው እና ዋነኛው ጠቀሜታ ለአሰልጣኞችና ለክለቦች እንደ አቋም መለኪያ ያገለግላል። የኢትዮጵያ ቡና እግር ኳስ ክለብ ዋና አሰልጣኝ ዐቢይ ካሳሁን እንደሚሉትም ውድድሩ እንደ አቋም መለኪያ ጨዋታ እንደሚጠቅማቸውና በክረምት የዝውውር ወቅት ወደ ክለቦች የተቀላቀሉ አዳዲስ ተጫዋቾች በይፋዊ ጨዋታዎች ተፈትነው ብቃታቸው የሚመዘንበት ወሳኝ መድረክ ነው።

በውድድሩ ላይ እየተሳተፉ ያሉ ክለቦች አሰልጣኞች በሰጡት አስተያየት የተጫዋቾችን ከቡድኑ ጋር የመዋሃድ ፍጥነት፣ አቋምና ቁመና እንዲሁም በስልጠና ላይ ያሳዩትን ነገር ወደ ትክክለኛ የጨዋታ ሁኔታ የመቀየር ብቃት ለመመልከት ዕድል ይፈጥራል። የታክቲክ አደረጃጀቶች በፉክክር ውስጥ ሲሞከሩ፣ የቡድኑ ጥንካሬዎችና ድክመቶች በግልጽ ይታያሉ። ይህ ደግሞ አሰልጣኞች የዋናው ሊግ ከመጀመሩ በፊት ማስተካከያዎችን እንዲያደርጉና የሚፈልጉትን የመጨረሻ ተጫዋቾች ምርጫ ለመወሰን ይረዳቸዋል።

በተለይ ከታችኛው ሊግ ለተጨመሩ ወጣትና ተስፋ ለሚጣልባቸው ተጫዋቾች፣ በሲቲ ካፕ ላይ የሚታይ ልዩ ብቃት በቶሎ የብዙዎችን ቀልብ እንዲስቡ ይረዳል። በዋናው ሊግ ውስጥ ቦታ ለማግኘት የሚደረገውን ፉክክር ከፍ የሚያደርግ እና ተጫዋቾቹ ለራሳቸው ያላቸውን ግምት የሚያጎለብት ነውም ተብሎለታል የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ። እንደ አሰልጣኝ ዐቢይ ካሳሁን አስተያየት ከሆነም ሲቲ ካፑ በኢትዮጵያ እግር ኳስ ውስጥ የሚጫወተው ሚና ከመደበኛ የወዳጅነት ውድድር እጅግ የላቀ ነው። የቡድን ዝግጅት ማማሻ፣ የደጋፊ ስሜት መለኪያ እና ለታክቲክ ለውጦች መሞከሪያ ሆኖ ያገለግላል።

የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ መጀመር ይዞት የመጣው ሌላኛው ዜና ውድድሩ በተናፋቂው አዲስ አበባ ስቴዲየም መካሄዱ ነው፡፡ ለዓመታት በዕድሳት ላይ የቆየው የአዲስ አበባ ስታዲየም ለኢትዮጵያ ዋንጫ ፍጻሜ በሩን ከፍቶ የእግር ኳስ ተመልካቾችን አስተናግዷል። ሲቲ ካፑን እንደ ተሞክሮ በማየት የፕሪሚየር ሊግ ሼር ካምፓኒው የሚያዘጋጀው የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ውድድርም ወደ ቤቱ እንዲመለስ መንገድ ጠራጊ ስለመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ያስረዳል፡፡

በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ቡና እና ቅዱስ ጊዮርጊስ ያሉ የከተማዋ ተቀናቃኝ ክለቦች ሲገናኙ ትልቅ የደጋፊን ስሜት ያነቃቃልና እግር ኳሱ ከዓመታት ቆይታ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ስታዲየም መመለሱ በስፖርት ቤተሰቡ ዘንድ የፈጠረው የደስታ ስሜት ቀላል አይደለም። በእርግጥም የአዲስ አበባ ስታዲየም ከኮንክሪትና ብረት የተገነባ ሕንጻ ብቻ ሳይሆን፣ የሀገሪቱ የስፖርት ህያው ታሪክ፣ ለዓመታት የፍቅር፣ የፉክክርና የጋለ ስሜት መገለጫ ሆኖ ቆይቷል።

የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶች እና ስፖርት ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ዳዊት ትርፉ ደጋፊዎች ወደ ስታዲየም እንዲመለሱ በርካታ ስራዎች መከናወናቸውን ተናግረዋል። የአዲስ አበባ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ከብዙ ዓመታት በኋላ በአዲስ አበባ ስታዲየም ተመልካቾች ገብቶ እንዲመለከትና የሚወዱትን ክለብ እንዲደግፉ ለማድረግ እና ከስታድየም በሚገኝ ገቢ የፋይናንስ አቅማቸው እንዲያጠናክሩ ለማድረግ ብዙ ርቀት መሄዱ ይታወቃል።

> **በተለይ ከታችኛው ሊግ ለተጨመሩ ወጣትና ተስፋ ለሚጣልባቸው ተጫዋቾች፣ በሲቲ ካፕ ላይ የሚታይ ልዩ ብቃት በቶሎ የብዙዎችን ቀልብ እንዲስቡ ይረዳል**

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ መጠናቀቅን ተከትሎ የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ (ሲቲ ካፕ) ‘ህዳሴ ዋንጫ’ የሚል ስያሜ የተሰጠው ሲሆን በደመቀ ሁኔታ በተመልካቾች ታጅቦ ውድድሩ እየተካሄደ ይገኛል። የአዲስ አበባ ከተማ እግር ኳስ ፌዴሬሽን እንደገለፀው ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር የዲጂታል ቲኬቲንግ ስርዓትን በመጠቀም እንደ ከዚህ ቀደሙ ተመልካቾች ረጃጅም ሰልፎች ተሰልፈው ቲኬት የሚቆርጡበት ስርዓት እንዲቀየርም እየተከናወነ ይገኛል፡፡

19ኛው አዲስ አበባ ከተማ ‘ህዳሴ ዋንጫ’ በአዲስ አበባ ስታዲየም ሲጀመር የመቻል እግር ኳስ ክለብ የቅዱስ ጊዮርጊስ እግር ኳስ ክለብ አሸንፏል። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶች እና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ በላይ ደጀን ጨምሮ ተጋባዥ የክብር እንግዶች ያስጀመሩትን ጨዋታ መቻል 4ለ0 አሸንፏል። ካለን ኮፊ እና ዮሴፍ ታረቀኝ የመቻል ግቦች ባለቤት ሆነዋል። መቻል ተጨማሪ ግብ የሚያገኝበትን እድል ሞሃመድ አበራ ፍፁም ቅጣት ምት አምክኗል። በቅዱስ ጊዮርጊስ በኩል ግብ ጠባቂው ብክ ኩሄዝ በሁለት ቢጫ ቀይ ካርድ ተመልክቶ ከሜዳ ሲወጣ የመቻሉ ቸርነት ጉግሳ የጨዋታው ኮከብ ተብሎ በመመረጡ የ20 ሺህ ብር እና የክሪስታል ዋንጫ ሽልማት ተበርክቶለታል።

የአዲስ አበባ ከተማ ‘ህዳሴ ዋንጫ’ ቀጥሎ ሲካሄድ ኢትዮጵያ ቡና ኢትዮጵያ ንግድ ባንክን 3ለ1 አሸንፏል። ለኢትዮጵያ ቡና እግር ኳስ ክለብ ሱራፌል ሹም በዛ እና አማኑኤል አድማሱ በጨዋታ ዲቫይን ዋቹኩዋ በፍፁም ቅጣት ምት ሶስቱን ግቦች ከመረብ አሳርፈዋል። አዲስ ግደይ የንግድ ባንክን ብቸኛ ግብ ሲያስቆጥር የኢትዮጵያ ቡናው ዲቫይን ዋቹኩዋ የጨዋታው ኮከብ ተብሎ በመመረጡ የ20 ሺህ ብር ሽልማት ተበርክቶለታል።

ከትላንት በስተያ በተከናወነው እና አምስት ግቦች በተቆጠሩበት ጨዋታ የቅዱስ ጊዮርጊስ እግር ኳስ ክለብ ፋሲል ከነማን ያሸነፈ ሲሆን፣ በቀጣይ ቀናትም ውድድሮች እንደሚቀጥሉ የእግር ኳስ ፌዴሬሽኑ መረጃ ያሳያል፡፡